## የሕፃናት ዓይን ሕክምናን የማስፋት ጅምር

ገጽ 8



## እጆች ሲዝሉ...

ገጽ 16







# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 301 ሐምሌ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ቅዳሜ ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# በአፍሪካ ምቹ የንግድ ሥራ እንዲኖር ሀገራት የፖሊሲ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይገባል

- **የአፍሪካ የሥራ ዕድል ፈጠራ ፎረም ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ተካሂዷል**

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአፍሪካ የንግድ ሥራን ምቹ ለማድረግ ሀገራት የፖሊሲ ማሻሻያ ሊያደርጉ እንደሚገባ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የአፍሪካ ኤሌክትሮኒክስ ትሬድ ግሩፕ ሊቀመንበር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ገለጹ። የአፍሪካ የሥራ ዕድል ፈጠራ ፎረም ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

"በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና ገበያ የሥራ ፈጠራ፣ የዲጂታልና የፋይናንስ አካታችነትን ማፋጠን" በሚል የአፍሪካ የሥራ ፈጠራ ፎረም በትናንትናው ዕለት በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል።


በፎረሙ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የአፍሪካ ኤሌክትሮኒክስ ትሬድ ግሩፕ ሊቀመንበር ኃይለማርያም ደሳለኝ እንደተናገሩት፤ በአህጉሪቱ አስከፊውን ድህነት ለማጥፋት መሰረት የሚጥሉ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። በአፍሪካ በቀጣይ ዓመታት የህዝብ ቁጥሩ እየጨመረ በሚሄድበት ወቅት የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ ይህን ሊመጥን የሚችል የሥራ ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል።

በአፍሪካ ምቹ የንግድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል












ዶክተር ተገኔ ረጋሣ

## የጤናው አውደ ርዕይ ከ70 ሺ በላይ በሚሆኑ ሰዎች ተጎብኝቷል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ሀገር አቀፉ የጤና አውደ ርዕይ እስካሁን ከ70 ሺ በላይ በሚሆኑ ሰዎች መጎብኘቱን ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የአውደ ርዕዩን የ17 ቀናት ቆይታ አስመልክቶ

የጤናው አውደ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በክልሉ ከ600 ሺህ በላይ ወጣቶች በዘንድሮ የክረምት በጎ ፍቃድ መርሀ-ግብር ይሳተፋሉ

- **ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ይድናል**

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል በ2015 ዓ.ም የክረምት ወራት የወጣቶች በጎ ፍቃድ መርሀ-ግብር ከ600 ሺህ በላይ ወጣቶች እንደሚሳተፉ እና ከዚህም ይወጣ የነበረ ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ማዳን እንደሚቻል የክልሉ ሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስታወቀ።

የሲዳማ ክልላዊ መንግሥት ሴቶች ፣ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የወጣቶች ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደስታ ለገሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በዘንድሮ የክረምት የወጣቶች በጎ ፍቃድ መርሀ-ግብር ሐምሌ 1ቀን 2015 ጀምሮ የሚካሄድ ሲሆን፤ ከክልሉ የተውጣጡ 612 ሺህ 763 ወጣቶች ይሳተፋሉ።

አቶ ደስታ በዚህ የወጣቶች የክረምት ወራት የበጎ ፍቃድ መርሀ ግብር 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን፤ ከማህበረሰብ እና ከመንግሥት ይወጣ የነበረን 731 ሚሊዮን ብር በላይ ማዳን እንደሚቻል

በክልሉ ከ600 ሺህ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ደስታ ለገሰ




## የሳይበር ጥቃትን የመከላከል አቅም 96 በመቶ ደርሷል

ገጽ 4








አቶ ዳዊት ቀኖ

# ሂጅራ ባንክ የሀብት መጠኑ ሰባት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ደረሰ

- የቅርንጫፎቹ ቁጥር 72 ደርሷል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ሂጅራ ባንክ አጠቃላይ የሀብት መጠኑ ሰባት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር መድረሱንና አምስት ቢሊዮን ብር ተቀማጭ ገንዘብ መሰብሰብ መቻሉን ገለጸ። ባንኩ የቅርንጫፍ ቁጥሩን 72 ማድረሱንም አስታውቋል።

ባንኩ በአንድ ዓመት ውስጥ ያከናወናቸውን ሥራዎች አስመልክቶ በትናትናው ዕለት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ንግግር ያደረጉት የባንኩ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት አቶ ዳዊት ቀኖ እንደገለጹት፤ ባንኩ የሀብት ምጣኔውን ወደ 207 በመቶ በማሳደግ የሀብት መጠኑን ሰባት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ማድረስ ችሏል። የተቀማጭ ገንዘብ መጠኑንም አምስት ቢሊዮን ብር አድርሷል።

በተጨማሪም ሂጅራ ባንክ በአዲስ አበባ 20 ቅርንጫፎችን እንዲሁም በክልል 52 ቅርንጫፎችን በአጠቃላይ 72 ቅርንጫፎችን መክፈት መቻሉን አስረድተው፤ የደንበኞችን ቁጥር በማሳደግ ላይ እንደሚገኝ እና ከ12 ሺህ በላይ ባለአክሲዮኖችም እንዳሉት አስረድተዋል።

የሂጅራ ባንክ የቦርድ ሰብሳቢ አብዱሰላም ከማል በበኩላቸው፤ ባንኩ ከስኬት መድረስ የቻለው በኢንዱስትሪው ከፍተኛ ውድድር በሚስተዋልበት ወቅት መሆኑ ስኬቱን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል ብለዋል። ሂጅራ ባንክ በአንድ ዓመት የጥቅል ትርፍ መጠኑን 162 በመቶ ማሳደጉንም አስገንዝበዋል።

ሂጅራ ባንክ ይህንን ስኬት ያስመዘገበው በሀገሪቱ ከወለድ ነፃ ባንክ ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በተከተለው የኢንቨስትመንት አማራጭ መሆኑን የተናገሩት የቦርድ ሰብሳቢው፤ ባንኩ ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነፃ ተደርጎ የበለፀገ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሸሪዓ መርህ ጋር የተመጣጠነ ቴክኖሎጂ እየተጠቀመ ያለ ባንክ መሆኑን አብራርተዋል።

ባንኩ ከ165 በላይ ከሆኑ ዓለም አቀፍ ከወለድ ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች የሚገለገሉበትን የአይማል ኮር ባንኪንግ ሲስተም በአጭር ጊዜ ሥራ ላይ ያዋለ ባንክ መሆኑንም የቦርድ ሰብሳቢው አስረድተዋል።

የባንኩ የሸሪዓ አማካሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ በበኩላቸው፤ ሁሉንም ማህበረሰብ ያሳተፈ የፋይናንስ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲዘረጋ መደረጉ ሂጅራ ባንክንና ደንበኞችን ተጠቃሚ እንዳደረገ ገልጸዋል።

ባንኩ በኢኮኖሚ ጠንካራ፣ ተወዳዳሪና ብቁ ለመሆን እንዲሁም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ድርሻውን ለመወጣት ይተጋል ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ ብሔራዊ ባንክ ላደረገው ድጋፍ አመስግነው በቀጣይም ለባንኩ ተመሳሳይ ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

ሂጅራ ባንክ በቀጣይ ዓመት ተጨማሪ አዳዲስ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ እስካሁን ሲሰጣቸው ከነበሩት የወለድ ነጻ አገልግሎቶች ተጨማሪ አዳዲስ አገልግሎቶችን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እንደሚያደርግ አክለው ተናግረዋል።

ሂጅራ ባንክ ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነፃ ባንክ በመሆን ነሐሴ 29 ቀን 2013 ዓ.ም ሥራ መጀመሩ የሚታወስ ነው።

# ኦልማ ኅብረተሰቡን የሚለውጡ ሥራዎችን እያከናወነ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዳማ:- ኦሮሚያ ልማት ማህበር ኅብረተሰቡን የሚለውጡ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ ገለጹ። ማህበሩ በአዳማ ከተማ ያስገነባውን የኦዳ አዳማ ከምድር በታች ባለሶስት ወለል እና ባለ 11 ፎቅ ሕንፃ ትናንት አስመርቋል።

በምረቃ ሥነሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ እንደገለጹት፣ በኦሮሚያ ክልል በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች ተከናውነዋል። በተለይ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች በርካታ ሥራዎችን በመስራት ብልጽግናን እውን ለማድረግ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ከፍተኛ ሥራ እየሠራ ነው።

በክልሉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት በተለይ የትምህርት፣ የጤናና የመንገድ አገልግሎትን የማስፋፋት ሥራ በስፋት እየተሰራ መሆኑን የገለጹት አቶ አወሉ፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የኅብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል በልዩ ትኩረት የልማት ሥራዎች እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በ54 ቢሊዮን ብር 29 ሺህ ፕሮጀክቶች ተሰርተው ለህዝብ አገልግሎት ክፍት ሆነዋል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ ከ19 ሺህ በላይ የሚሆኑት ፕሮጀክቶች በመንግሥት፣ በአጋር አካላትና በህዝብ የተሰሩ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ ከ14 ሺህ የሚልቁት ፕሮጀክቶች በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የኦሮሚያ ልማት ማህበር ሲቋቋም ጀምሮ በርካታ ፈተናዎች እንደነበሩበት ገልጸው፤ ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ ችግሩን አልፎ ለኦሮሞ ህዝብ ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጡ የልማት ሥራዎች እየሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል። በትምህርት ዘርፍ እየሠራ ያለው ሥራ ለሀገር የሚጠቅሙ ዜጎችን እያፈራ መሆኑን የገለጹት አቶ አወሉ፤ የኦሮሚያ ልማት ማህበር ለኅብረተሰብ ለውጥ እየሠራ ያለውን ከፍተኛ ሥራ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባና የኦሮሚያ ልማት ማህበር ምክትል ሰብሳቢ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኦሮሚያ ልማት ማህበር የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አመርቂ ሥራ እየሠራ ነው። ወደፊትም ብዙ ውጤታማ ስራዎች መስራት ይጠበቅበታል፤ የኦሮሚያ ህዝብ ያለበትን ሰፊ ችግር ተረድቶ ሰፊ የልማት ሥራዎችን መሥራት ይኖርበታል ሲሉ ገልጸዋል።

በትምህርት ተወዳዳሪ የሆነ ትውልድን በማፍራት ረገድ የሠራውን ሥራ አድንቀው፣ ከአዳሪ ትምህርት ቤቱ የሚወጡ ልጆች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እየሆኑ ነው ብለዋል።

የኦሮሚያ ልማት ማህበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ደጀኔ ኢተቻ እንደገለጹት፤ ህንጻው የኦሮሚያን ባህል ተላብሶ የተሰራ ሲሆን ከ251 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎበታል።

ህንጻው በልማት ማህበሩ አባላት የተገነባ ሲሆን G3+11 ወለል አለው። ለብዙ ወጣቶችም የሥራ እድል ይፈጥራል።

የልማት ማህበሩ ሰፊ የልማት እቅዶች እንዳሉት የገለጹት ዳይሬክተሩ፣ በቀጣይ ትውልድን በትምህርት መገንባት፣ የጤና ተቋማትን በማሻሻል የእናቶችን ሞት መቀነስና የመንገድ ሥራዎችን እንደሚያከናውን ገልጸዋል።

# መምህራን አንድነትን በማስተማር ሀገር ተረካቢ ትውልድ ማፍራት ይጠበቅባቸዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- መምህራን በተማሪዎች ዘንድ ከመለያየት ይልቅ አንድነትን በማስተማር ሀገር ተረካቢ ትውልድ ማፍራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ጀማሉ ጀንበሩ ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ማህበረሰብ የአረንጓዴ አሻራ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር በትናንትናው እለት የትምህርት አመራሮች፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በጨፌ ትምህርት ቤት አቅራቢያ ተከናውኗል።

በማስጀመሪያ መርሀ ግብሩ ላይ የተገኙት በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ጀማሉ ጀንበሩ እንደተናገሩት፤ መምህራን በተማሪዎች ዘንድ ከመለያየት ይልቅ ስለአንድነት በማስተማር ሀገር ተረካቢ ትውልድ በማፍራት ኢትዮጵያ የጀመረችውን የእድገት ጉዞ እውን ማድረግ እንዲቻል መሰረት ሊጥሉ ይገባል።

አረንጓዴ አሻራ ከውበት ይልቅ ለትውልድ ትልቅ መሰረት የምንጥልበት ተግባር ነው ያሉት አቶ ጀማሉ፤ በተለይ ከተሞች አረንጓዴ ሲሆኑ ለኑሮ ተስማሚ እንደሚሆኑና ከዛ ባሻገርም አረንጓዴ ስፍራዎች በስፋት ባሉበት አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች በአካልና በአዕምሮ ጠካራና ጤናማ የመሆን እድላቸው የሰፋ ነው ብለዋል።

የዓለማችን ፈተና የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ከሚያስከትላቸው አደጋዎች ትውልድና ሀገርን ለመከላከል አረንጓዴ ስፍራዎች አስፈላጊ ናቸውም ነው ያሉት።

ዶክተር ጀማሉ አያይዘውም የከተማዋ ነባራዊ ሁኔታ በርካታ ኢንዱስትሪዎችና ተሽከርካሪዎች በካይ ጋዝ የሚለቁበት ሁኔታ በመኖሩ ለቀጣይ ሀገር ተረካቢ ዜጎች ተስማሚ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲኖር ለማድረግ ዛሬ ላይ የምንተክላቸው ችግኞች ትልቅ ፋይዳ አላቸው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ጀማሉ ገለጻ፤ ከዘንድሮው መርህ ቃል መረዳት እንደምንችለው ዛሬ የምንተክላቸው ችግኞች ለነገ ሀገርና ትውልድ መሰረት ናቸው። ትምህርት ቤቶችም የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልዶች የምናፈራባቸው ተቋማት በመሆናቸው ዛሬ የምናከናውናቸው ተግባራት ለነገው ትውልድ መሰረት የሚጥሉ ናቸው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ በበኩላቸው፤ በመዲናዋ እየተከናወነ የሚገኘው የዘንድሮው አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ተማሪዎችንና መምህራንን ጨምሮ ሁሉንም የትምህርት ማህበረሰብ የሚያሳትፍ መሆኑን በመግለጽ ሰኔ 30 ሲታሰብ በአዕምሮአችን የሚመጣው ውጤት የምናይበትና ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ የምንሻገርበት እለት ነው ብለዋል።

ይህ እለት የትምህርት ዘመኑን በማጠናቀቅ ለሚቀጥለው የትምህርት ዘመን የምንዘጋጅበት በመሆኑ አረንጓዴ አሻራ ደግሞ ለቀጣይ ትውልድ ምቹና ጽዱ የሆነች ሀገር ለማስረከብ ያለመ መሆኑን የቢሮው ኃላፊው ጠቁመዋል።


አያይዘውም "ኢትዮጵያን ለቀጣይ ዘመን የምትመች፣ ሁሉንም ማስተናገድ የምትችል ሀገር ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህም ነገን የምትረከቡት እናንተ በመሆናችሁ ጠንክራችሁ ሥሩ" በማለት ለተማሪዎች መልዕክት አስተላልፈዋል።

በትናንትናው እለት በተከናወነው በዚህ የማስጀመሪያ መርሀ ግብር ከ15 ሺ በላይ ችግኞች እንደሚተከሉ ተጠቁሟል።

# "የኢፕድ ስልጠና ተቋማችን የያዘውን እቅድ ለማሳካት በአዲስ መንፈስ ለሥራ እንድንነሳሳ አስችሎናል"

*- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሠራተኞች*

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- በኢፕድ የስልጠና ማዕከል የተሰጣቸው የሥራ ላይ ማነቃቂያ ስልጠና በ2016 በጀት አመት ተቋማችን የያዘውን እቅድ ለማሳካት በአዲስ መንፈስና በመልካም አስተሳሰብ ለሥራ እንድንነሳሳ አስችሎናል ሲሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሠራተኞች ገለጹ።

በኢንዱስትሪ ፕላንና ክትትል መምሪያ ከፍተኛ ባለሙያው አቶ አለማየሁ አለሜ እንደገለጹት፣ በኢፕድ የስልጠና ማዕከል የወሰድነው የማነቃቂያ ስልጠና ከተቋሙ አላማና ግብ ጋር የተሳሰረ ውጤታማ የሆነ ሠራተኛ መፍጠር የሚያስችል ነው። በተለይ የ2015 በጀት አመትን በመጨረስ አዲስ የበጀት አመት የምንጀምርበት ወቅት ላይ ይህን አይነት ስልጠና መሰጠቱ እውቀትን ከተግባር ጋር በማስተሳሰር እንዴት በሥራ ላይ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ትልቅ መንገድ የሚያሳይ ነው። በአጭር ጊዜ በቂና ገንቢ ስልጠና አግኝተናል ነው ያሉት።

በኮርፖሬሽኑ የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያ ከፍተኛ የማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያው አቶ ንጉስ ተፈራ ስልጠናው በቀጥታ ከኮርፖሬሽኑ ግብና አላማ ጋር የሚዛመድ መሆኑን በመጠቆም፣ ኢፕድ የስልጠና ጊዜው አጭር ከመሆኑ በስተቀር ከስልጠና መርሀ ግብሩና ከአሰልጣኞች አመራረጥ ጀምሮ ትክክለኛና ተገቢ ስልጠና እንድናገኝ አድርጎናል። ይህ አይነት ስልጠና በሌሎች ተቋማትም ሊለመድና ሊሰራበት ይገባል ብለዋል።

ሌላኛዋ በከርፖሬሽኑ ከፍተኛ አርክቴክት ወይዘሮ መድኃኒት በቀለ፤ ስልጠናው ውብና ሳቢ በትክክልም አነቃቂና የሥራ ላይ ውጤታማነት እንዴት ማስመዝገብ እንደሚቻል ያሳየ ነው ብላለች።

ለኮርፖሬሽኑ የማነቃቂያ ስልጠና የሰጡት ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ እንደገለጹት፤ «አስተሳሰብ» «mindset» አሉታዊ አስተሳሰብን በአዎንታዊ አስተሳሰብ በመለወጥ ራስንና የሚሰሩበትን ተቋም መለወጥ ያስፈልጋል። ራስን የመምራት፣ ተቋምን የመምራትና የአገልጋይት ስነልቦናን መላበስ አስፈላጊ ነው።

ከአሉታዊ አስተሳሰብ በመውጣት የእለት ተእለት ውሎ ጀምሮ ለራስ ብሩህ አስተሳሰብ መፍጠር አስፈላጊ ነው ያሉት ዶክተር ወዳጄነህ፤ በአመራር እና በመሪ መካከል ያለውን ልዩነት በማውሳት ራስን የማወቅ፤ በቤትም መስሪያ ቤትም ውስጥ በመመሪያ፣ በግልጽነት፣ በተጠያቂነትና የመግባባት ችሎታን በማዳበር መስራት ለአንድ ሥራ አስፈላጊ ናቸው ብለዋል።

ጥሩ መሪ በአደባባይ ያመሰግናል፤ ሲገስጽም ለብቻ ወስዶ ይመክራል፤ ይሄን አይነት ክህሎት መላበስ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው አማካኝነት "በኢንዱስትሪው ዘርፍ የጥራት ሚና ለሀገር ግንባታ" በሚል ርዕስ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ ትኩረቱም የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከዓለም አቀፍ የገበያ ሥርዓት ጋር ተወዳዳሪ መሆን በሚቻልበት ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነው።

በዓለም አቀፍ የገበያ መድረክ ተፈላጊ ምርት ለማምረት አስተሳብን ከውጤትና ከምርት ጋር በማስተሳሰር መስራት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን አገዋ ቆመ ብሎ መቆዘም ይቀራል። ጥራቱ የተጠበቀ ምርት ሲመረት ፈላጊ ይኖራል፡ ለዚህ እንዴት መስራት እንደሚቻል ቴክኖሎጂን እንዴት መጠቀምና ምርት ማምረት እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የትራንስፎርሜሽንና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍጹም ከተማ በስልጠናው መጀመሪያ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ በ2025 ኢትዮጵያን የማኑፋክቸሪንግ ማዕከል ለማድረግ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት የነቃ፣ የበቃ አመራርና ሠራተኛ ያስፈልጋል ብለዋል። በኢፕድ የሚሰጠው ስልጠናም የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ ከዓለም አቀፍ ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻልና የተሻለ ተቋም ለመገንባት ወሳኝ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አንጋፋ እንደመሆኑ መጠን ኢንዱስትሪውን በአግባቡ ለመደገፍ የሚያስችል ስልጠና በእውቁ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣውና ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ አማካኝነት እንድናገኝ ስላደረገ እናመሰግናለን፤ በቀጣይም ኢፕድ ተመሳሳይ ስልጠናዎችን እንድሚያዘጋጅ ተስፋ እናደርጋለን ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ሄለን እስክንድር በበኩላቸው፤ ኢፕድ በህትመት ሚዲያው ዘርፍ ከ82 አመታት በላይ መረጃን ለህዝብ ተደራሽ እያደረገ የመጣ ተቋም መሆኑን በመጥቀስ፤ ባለፉት ሦስትና አራት አመት በተሰራው የለውጥ ሥራ በስድስት የሀገር ውስጥ ቋንቋዎችና በሁለት የውጭ ሀገር ቋንቋዎች መረጃን ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ በጥናትና ምርምር ውስንነቶችን በመለየት ለተለያዩ ተቋማት ለሠራተኞችና አመራሮች ስልጠና እየሰጠ ይገኛል ብለዋል።

በማዕከሉ ስልጠና ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር እንደ ሀገር ውጤታማ የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ሥራ እንዲፈጠር ለማስቻል ለፌዴራል፣ የክልልና የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎችና አመራሮች፣ ለተለያዩ ተቋማት ሠራተኞችና አመራሮች በሥራ ላይ ሥነ ልቦና፣ የሥራ ላይ ተግባቦትና ምላሽ አሰጣጥ፣ የሥራ ላይ ሥነምግባር፣ አገልጋይነትና በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ስልጠና ተሰጥቷል ብለዋል።

የኢፕድ የስልጠና ማእከል እስካሁን ከ84 በላይ ለሚሆኑ የተለያዩ ተቋማት ስልጠና ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነትም ተፈራርመዋል።



አቶ ጂማ ዲልቦ



አቶ ፋሲካው ሞላ

## በጦርነትና በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች 850 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተደረገ

- **ለትግራይ ክልል ሰብዓዊ ድጋፍ የማሰባሰብ ሥራ ተጀምሯል**

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በጦርነት እና ድርቅ ለተጎዱ ዜጎች 850 ሚሊዮን ብር የሚገመት የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ መደረጉን የኢፌዴሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አስታወቀ።

ባለስልጣኑ በትግራይ ክልል ሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍ ለማድረግ 4ኛ ዙር ሀብት የማሰባሰብ መርሃግብር በትናንትናው ዕለት አስጀምሯል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጂማ ዲልቦ በመርሃግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በጦርነት፣ በድርቅና በሌሎች ችግሮች ጉዳት ለደረሰባቸው አካላት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሀብት በማሰባሰብ የዓይነት እና የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል።

በቀጣይም በሚካሄደው አራተኛ ዙር ሀብት የማሰባሰብ ሥራ ለትግራይ ክልል ተከታታይነት ያለው ሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍ ለማድረግ፣ የተገኘውን ሰላም ለማስቀጠል፣ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን ለማጠናከር እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ጉዳት ለደረሰባቸው ማህበረሰቦች ሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍ ለማድረግ ከፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት በኋላ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምቹ ምህዳር ተፈጥሯል ሲሉም አቶ ጂማ ተናግረዋል።

የኢፌዴሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር አቶ ፋሲካው ሞላ በበኩላቸው፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሀገሪቱ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲከሰቱ ለማህበረሰቡ ሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ ብለዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ባስተባበረው ሶስት ዙር የሀብት ማሰባሰብ ሥራ 850 ሚሊዮን ብር የሚገመት የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ በጦርነት እና በድርቅ ለተጎዱ ክልሎች ተደርጓል ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ የተሰባሰበው ሀብት ለትግራይ፣ አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ እና ለሌሎች ክልሎች ተጎጂዎች መተላለፉን አስታውቀዋል።

በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በትግራይ ክልል ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳቶች በመድረሳቸው መልሶ የማቋቋምና ግንባታ ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የሀብት አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ክትትል አስተባባሪ እና አማካሪ ዶክተር መብራቱ መለሰ በበኩላቸው፤ በትግራይ ክልል የደረሰው ሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት ከፍተኛ በመሆኑ መልሶ ለማቋቋምና ለመገንባት ረጅም ጊዜ እና የሁሉንም ማህበረሰብ እገዛ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ብለዋል።

በክልሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ተፈናቅለው በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች እንደሚገኙ የጠቆሙት ዶክተር መብራቱ፤ የዕለት ምግብ እና ህክምና ለማግኘት በከፍተኛ ሁኔታ ስለተቸገሩ አስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ አሳስበዋል።

በተጨማሪም የጤና፣ የትምህርት፣ የውሃ እና ለመኖ መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን መልሶ መገንባት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው ብለዋል።

በክልሉ የደረሰውን ውድመት ወደነበረበት ለመመለስ ሁሉም ማህበረሰብ እገዛ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

## "የእንስሳት ሀብት ጥቅም በትክክል እየተመዘነ አይደለም"

*ፕሮፌሰር ብርሃኑ በላይ*
*ዓለም አቀፍ የእንስሳት እርባታ ተመራማሪ*

**ምሕረት ሞገስ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ትልቅ ቁጥር ያለው የእንስሳት ሀብት ያላት ቢሆንም ሀብቱ በትክክል እየተመዘነ አለመሆኑንና ለሀብቱ ተገቢው ትኩረት አለመሰጠቱን ዓለም አቀፍ የእንስሳት እርባታ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ብርሃኑ በላይ ገለጹ።

ዓለም አቀፍ የእንስሳት እርባታ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ብርሃኑ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሁሉም የእንስሳት አይነቶች ከፍተኛ ቁጥር ያለ ቢሆንም፤ ምርት እና ምርታማነታቸውን ከወተት፣ ከስጋ እና ከእንቁላል አንፃር ብቻ መመዘን ተገቢ አይደለም።

በእርሻ ዘርፍ ላይ ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚሆን በሬ አርሶ የሚያበላ መሆኑን የጠቆሙት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ይህ መታወቅ እና መደነቅ እያለበት ብዙ ጊዜ የእንስሳት ምርት እና ምርታማነት ላይ የእንስሳት አገልግሎት ስሌት ውስጥ አይገባም ብለዋል።

እንደፕሮፌሰር ብርሃኑ ገለፃ፤ ሀገሩ በበሬ እየታረሰ ዕቅድ ላይ ወተት እና ስጋ ብቻ ይጠቀሳል። ገበሬው ሲቸግረው ጊዜያዊ የገንዘብ ፍላጎቱን ለማሟላት ግልገል ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብም ታሳቢ አይደረግም። ነገር ግን እንስሳት የስጋ፣ የወተት፣ የእርሻ አገልግሎት እና ለአርሶ አደሩ ፈጣን የገንዘብ ማግኛ መንገዶች መሆናቸው መታወቅ አለበት።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ግብርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የተሸከመ ቢሆንም፤ ከትራንስፖርት ፣ ከኢንደስትሪ እና ከሌሎችም ዘርፎች ጋር ሲወዳደር መንግሥት በግብርና ላይ ኢንቨስት የሚያደርገው እና የሚሰጠው ትኩረት በጣም አነስተኛ ነው። ይህም ዘርፉ የበለጠ ውጤታማ እንዳይሆን ያደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

ለሆቴል፣ ለህንፃ ግንባታዎች እና ለሌሎችም ሥራዎች ከሚገኘው ብድር አንጻር ለግብርና ዘርፍ የሚሰጠው ብድር ብዙ ውጣውረድ ያለበት መሆኑን በመጠቆም፤ የባንኮች አሠራር እና አንዳንድ የመሬት ሥሪት ሁኔታዎችም መስተካከል እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ዜና

# የሳይበር ጥቃትን የመከላከል አቅም 96 በመቶ ደርሷል

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሳይበር ጥቃትን የመከላከል አቅም 96 በመቶ መድረሱን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አስታወቀ። ተቋማት የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል መረጃዎቻቸውን በጥንቃቄ እንዲይዙም ተጠይቋል።

በአስተዳደሩ የሳይበር ደህንነት ባለሙያ አቶ የቻለው ይግዛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ተቋማት የሀገር የጀርባ አጥንትነታቸውን በመረዳት የየራሳቸውን መረጃዎች በጥንቃቄ በመያዝ ከሳይበር ጥቃት ራሳቸውን ሊከላከሉ ይገባል።

መረጃዎቻቸው ላይ ጥቃት ቢደርስ በሀገር ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በመረዳት ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባቸው መሆኑን ያመላከቱት አቶ የቻለው፤ ተቋማት የሳይበር ሴኩሪቲን የሚመለከቱ መመሪያዎች እንዲኖራቸውና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወጡ መመሪያዎችንም እንዲተገብሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የሳይበር ደህንነት ጉዳይ ኃያላን ሀገራት በየዓመቱ በርካታ ትሪሊዮን ዶላሮችን ፈሰስ በማድረግ የሚያስጠብቁት ጉዳይ መሆኑን የገለጹት አቶ የቻለው፤ የሳይበር ጥቃት ሲፈፀም ሀገር ላይ የሚያደርሰው ተፅእኖ ከፍተኛ በመሆኑ ሁሉም ተቋማት በንቃት ሊከላከሉት የሚገባው ጉዳይ መሆኑንም ተናግረዋል።

ተቋማት ሠራተኞቻቸውን የማንቃት ሥራ መስራትና ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን ማሳወቅ እንደሚገባ አመልክተው፤ እያንዳንዱ ተቋም የሰው ኃይሉን የሚያስተዳድርበት የራሱ ህግ የመኖሩን ያህል በሳይበር ደህንነት ጉዳይ ላይም የራሱ ህግ ሊኖረው ይገባል ብለዋል።

አቶ የቻለው በገለፃቸው፤ ተቋማት በሳይበር ደህንነት ዘርፍ የተቃኘና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማብቃትና ማሰልጠን ይኖርባቸዋል፤ የሚመሩበት ፖሊሲና ስታንዳርድ ማውጣት እንዲሁም ተቋማት የሚጠቀሙበትን ማንኛውም ሶፍትዌር ዘመናዊ መገልገያዎችን መጠቀም ያስፈልጋልም ነው ያሉት።

ተቋማት የበቃ ዓለም አቀፍ የሳይበር ደህንነትን የሚረዳ ሠራተኛን ለማፍራት የሚያስችላቸውን ስልጠና በመስጠትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመታጠቅ የሳይበር ፖሊሲ ስታንዳርድን በማሟላት ማንኛውንም የሳይበር ጥቃት ሊከላከሉ ይገባል ሲሉም አቶ የቻለው ተናግረዋል።

በተለይም የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪና መሰል ተቋማት ለመረጃዎቻቸው ትኩረት በመስጠት ያልተገባ ስፍራ እንዳይቀመጥና ለጥቃት እንዳይጋለጥ መጠንቀቅ አለባቸው። መስሪያ ቤታቸው ተቋማት ለሚኖራቸው ማንኛውም ጥያቄና ዕገዛ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ 96 በመቶ የሳይበር ጥቃትን የመከላከል አቅም ላይ መድረሷን ያወሱት አቶ የቻለው፤ በዚህ ረገድም የተቋማት የመከላከል አቅምን ማዳበርና ባህል ማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክትም ነው የተናገሩት።

የሳይበር ደህንነት ማለት ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ መረጃን ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ መልኩ ከመረጃ ላኪው ወደ ተቀባዩ መድረስ ሲሆን፤ የሳይበር ጥቃት ማለት ደግሞ መረጃ መድረስ ለሚገባው አካል በተለያዩ ምክንያቶች ወይ በከፊል አሊያም ሙሉ በሙሉ ሳይደርስ ሲቀርና በመንታፊዎች እጅ ሲወድቅ መሆኑን አቶ የቻለው አብራርተዋል።

## የጤናው አውደ ርዕይ ከ70 ሺ በላይ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚኒስቴሩ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ተገኔ ረጋሣ በሰጡት መግለጫ እንዳብራሩት፤ ሰኔ 13 ቀን የተከፈተው "የመጪው ትውልድ ጤና" አውደ ርዕይ በ30 ቀናት ውስጥ ከ100 ሺ በላይ ሰዎች ይጎበኙታል ተብሎ በእቅድ ተይዞ ነበር።

በዚህም መሠረት እስካሁን ከ70 ሺ በላይ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የምርምር ተቋማት፣ የዩኒቨርሲቲዎች፣ የክልል የጤና ቢሮ ኃላፊዎች ሠራተኞችና በዘርፉ የተሠማሩ የግል ባለሀብቶች ጎብኝተውታል ብለዋል።

አውደ ርእዩ ለሀገር በቀል ህክምና ልዩ ትኩረት የተሰጠበት በመሆኑ በዚህ ረገድ እንደ ሀገር እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን በማበረታታት ወደዘመናዊ የህክምና ሥርዓት ለማስገባት በር የሚከፍት ነው ያሉት ዶክተር ተገኔ፤ በዚህም በሀገሪቱ ያለው የጤና እድገት ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰና የቀጣይ ጉዞን በተመለከተ መረጃ ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

በተጨማሪም በአውደ ርዕዩ ነጻ የጤና ምርመራ፣ የበጎ ፈቃድ ደም ልገሳና ሙያዊ የምክር አገልግሎት እንዲሁም በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች የፓናል ውይይት እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአውደ ርዕዩ ዋና አላማ ህብረተሰቡ የጤና ሥራዎችን የራሱ በማድረግ ተሳትፎውን እንዲያጎለብት ለማስቻል ነው ያሉት ዶክተር ተገኔ፤ በተጨማሪ ህብረተሰቡ ህመም ከመከሰቱ በፊት ለወጪና ለእንግልት ሳይዳረግ ጤናውን እንዴት መጠበቅ እንደሚኖርበት ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው ብለዋል።

አውደ ርዕዩ እስከ ሐምሌ 12 ይቀጥላል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው በቀሩት ጊዜያት ሁሉም ዜጎች እንዲታደሙ ጥሪ አቅርበዋል።



# ችግኞችን መትከል ትውልድን ደህንነቱ በተረጋገጠ ሀገር ላይ ማኖር ነው

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ችግኞችን መትከል የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልዶችን ደህንነቱ በተረጋገጠ ሀገር ላይ ማኖር ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳኛው ገብሩ ተናገሩ፡፡ ትናንት ከ350 የሚበልጡ የባለስልጣኑ ሠራተኞች አቃቂ ቃሊቲ ወረዳ አስራ ሁለት ጨሪ መድኃኒዓለም አካባቢ 10 ሺህ ችግኞችን ተክለዋል፡ ፡

በችግኝ ተከላ መርሐ ግብሩ የተገኙት የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳኛው ገብሩ እንደገለጹት፤ ችግኞችን መትከል ሀገርን ማጽናት እና ለነገ ተረካቢ ትውልድ ሀገራቸውን በሰላም ደህንነቷን ጠብቆ ማኖር ነው፡፡

እንደ ዋና ሥራ አስኪያጁ ንግግር፤ ችግኝን ተንከባክቦ ማሳደግ ከራስ በተጨማሪ ለቀጣይ ትውልድ ማሰብና የአየር ንብረትን ማረጋጊያ መልካም አማራጭ ነው፡፡

ዋና ሥራ አስኪያጁ በንግግራቸው እንዳመላከቱት፤ መስሪያ ቤታቸው በአረንጓዴ አሻራ መርሀግብር አገልግሎት ከተጀመረ ጀምሮ የተለያዩ ተክሎችን ሲተክልና ሲንከባከብ ቆይቷል። አሁንም መትከል ብቻ ሳይሆን የመንከባከብ ስራንም ይሰራል።

በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በርካታ ችግኞች እየተተከሉ መሆኑን የገለጹት ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ ችግኞችን መትከል ብቻ ሳይሆን ተንከባክቦ እንዲጸድቁ ማድረግ እንደሚገባም ነው የገለጹት፡፡

የችግኝ መተከል ፕሮግራሙ ከተጀመረ ጀምሮ የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣንም በተለያዩ ቦታዎች በየአመቱ በርካታ ችግኞች እየተከለ ሲሆን፤ በዘንድሮ አመትም 10 ሺህ ችግኝ እንደሚተክል ነው የገለጹት፡፡

ችግኞችን እንደ ልጆች መንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን የተናገሩት አቶ ዳኛው፤ በሚደረገው የመንከባከብ ሥራ ላይ በመሳተፍ ችግኞቹ እንዲጸድቁ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንደሚወጡ ቃል ገብተዋል፡፡ በአሁኑ የተከላ መርሀ ግብር ላይም ቶሎ እንዲፀድቁ በማሰብ ያደጉ ችግኞችን እንደተጠቀሙም ዋና ሥራ አስኪያጁ ገልጸዋል፡፡

አቶ ዳኛው በንግግራቸው እንዳመላከቱት፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በተጨማሪ በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይም በንቃት ተሳትፎ ያደርጋል። በማዕድ ማጋራት እና በቤት እድሳት መርሀ-ግብሮች ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ መደረጉንም አክለው ተናግረዋል፡፡

በችግኝ ተከላ መርሀ ግብሩ ላይ ከባለስልጣኑ ሠራተኞች በተጨማሪ አቃቂ ቃሊቲ ወረዳ አስራ ሁለት ነዋሪዎች ተሳትፈዋል፡፡

## በአፍሪካ ምቹ የንግድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ስለዚህ በአፍሪካ ምቹ የንግድ ሥራ እንዲኖር ሀገራት የፖሊሲ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይገባል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ የሥራ ፈላጊ ወጣቶችንና የሥራ ዕድሎችን ማጣጣም ይገባል። እንደ አህጉር የኢኮኖሚ ግብ ለማሳካትና ለውጥ ለማምጣት በርካታ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በተለይ መንግሥትና የግሉ ዘርፍ እንዲሁም አጋር አካላት በአዲስ እሳቤ ለውጥ ለማምጣት በጋራ መስራት አለባቸው ያሉት ሊቀመንበሩ፤ በመንግሥትና በግል ሽርክና መተማመንን በመገንባት ክህሎትንና ኢንቨስትመንቶችን በማጣመር የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

እንደ ሊቀመንበሩ ገለፃ፤ በአፍሪካ አህጉራዊ የንግድ ከባቢ አነስተኛ ንግዶች በዲጂታል መድረኮች የመማር ዕድሎችን እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል። በአፍሪካ ውስጥ የንግድ ሥራን ምቹ ለማድረግና ለማሳለጥ ፖሊሲዎችን እና አካሄዶችን ማጣጣም ተገቢ ነው። በተጨማሪም ተመጣጣኝ ፋይናንስና አዳዲስ ገበያዎችን ማግኘት እንዲቻል በጎ ተጽዕኖ ማሳደር የሚያስችሉ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል።

በአህጉሪቱ ዕድገት ተግዳሮት የሆነውን ሥራ አጥነት ለመቀነስ እርስ በእርስ በመማማርና ተሞክሮዎችን በመለዋወጥ ችግሩን ለመፍታት በጋራ መስራት ይገባል ብለዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል በበኩላቸው፤ አፍሪካ ያልተነካ እምቅ ሀብቷን በመጠቀም የኢኮኖሚ ነጻነቷን እንድታረጋግጥ መስራት ይገባል።

የአፍሪካ ትልቁ አጀንዳ የሥራ ዕድል ፈጠራ ነው ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ላይ የተደረሰው ስምምነት በአህጉሪቱ ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በር ይከፍታል ብለዋል።

ፎረሙ ለሦስት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ሲሆን፤ በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና የዲጂታል እና የፋይናንስ አካታችነት ትግበራ፤ ለአፍሪካ ወጣቶች ሥራ ዕድል ፈጠራ እና የአፍሪካ ስትራቴጂክ ኢንቨስትመንት ጥምረት ፍኖተ ካርታ ላይ ውይይት ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

በመድረኩ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚልን ጨምሮ የአፍሪካ ሕብረት የንግድ፣ ቱሪዝም፣ ኢንዱስትሪና ማዕድን ኮሚሽነር አልበርት ሙቻንጋ፣ የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን ምክትል ሊቀመንበር ሞኒክ ንሳንዛባንጋዋ እና የአፍሪካ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ተቋማት አመራሮች ተገኝተዋል። ከፎረሙ ጋር ተያይዞም የአፍሪካ ትስስር ቀን ተከብሯል።

## በክልሉ ከ600 ሺህ በላይ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ገልጸዋል።

ለዚህ መርሀ ግብርም በ13 ተግባራት ላይ የሚሳተፉ ሲሆን፤ ከእነዚህም የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርን ጨምሮ የደም ልገሳ ፣የቤት እድሳት ፣አቅመ ደካሞችን ማገዝ፣ የማዕድ ማጋራት፣ የአልባሳት ድጋፍ፣የደብተርና እስክሪብቶ ልገሳ የመሳሰሉት የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም በግብርና ዘርፍ ገበሬዎችን የማገዝ እንዲሁም የከተማ ጽዳት አገልግሎት እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ እና ኮሌጅ የሚመለሱ ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ላሉ ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡበት መርሀ ግብር የሚካሄድ መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ደስታ እንዳስታወቁት ባለፈው አመት በ12 ተግበራ ላይ የተሳተፉ ሲሆን፤ ዘንድሮ በተለየ መልኩ በተሰማሩበት ሙያ የማገልገል ተግባርን በ13ኛነት እንደተጨመረ ተናግረዋል።

ወጣቶች በበጎ ተግባራት ላይ መሳተፋቸው ጊዜያቸውን አለአግባብ ከማሳለፍና ለተለያዩ ሱስ ተጋላጭ እንዳይሆኑ ከመርዳቱም በላይ እራሳቸውን በእንደዚህ አይነት በመልካም ተግባራት በመሳተፍ በጎነትን ልማድ ማድረግ እንዲችሉ ያደርጋል ሲሉ አስታውቀዋል።

አቶ ደስታ እንደነዚህ ያሉ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች የእቅድ ማስፈጸሚያ ብቻ ሳይሆን አመርቂ ውጤት እየታየ ብዙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ሁሉም በዚህ ተግባር በመተባበር በየጊዜው ለውጦችን ለመፍጠር መስራት አለበት ብለዋል።

ባለፈው አመት 657 ሺህ ወጣቶች በክረምት በጎ ፍቃድ ለማሳተፍ ታቅዶ የእቅዱን 94 በመቶ በማሳካት አመርቂ ውጤት መገኘቱን አስታውሰው፤ ዘንድሮም ከአምናው የተሻለ ወጣቶችንና ሁሉንም የማህበረሰብ አካላት የበጎነት ተግባር ላይ እንዲሳተፉ መልእክት አስተላልፈዋል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት



**‹‹ግብርና ላይ ውጤታማ**
መሆን ከተፈለገ ዘርፉን ወደ
ፕራይቬታይዜሽን ማዞር ያስፈልጋል››

ፕሮፌሰር ብርሃኑ በላይ
የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ መስራችና ፕሬዚዳንት

ገጽ 6

መነሻውን
በሽቦ መኪና
ያደረገው
የማሽኖች
አምራች

ገጽ 13





ገጽ 16

**እጆች ሲዝሉ ...**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «ግብርና ላይ ውጤታማ መሆን ከተፈለገ ዘርፉን ወደ ፕራይቬታይዜሽን ማዞር ያስፈልጋል»

*- የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ መስራችና ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ብርሃኑ በላይ*

ምህረት ሞገስ



**በሞያቸው የእንስሳት እርባታ ዓለም አቀፍ ተመራማሪ ናቸው። በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለ28 ዓመታት ሲያስተምሩ ቆይተዋል። የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የዩኒቨርሲቲው መሥራች ፕሬዚዳንት ሆነው ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል። በዩኒቨርሲቲዎች ለበርካታ አመታት ከሠሩ በኋላ ዓለምአቀፍ የምርምር ፈቃድ ተሰጥቷቸው ከሞያው ጋር ተያያዥ ከሆነ ከዓለምአቀፍ የቆላማ አካባቢዎች የግብርና ምርምር ሥራ ማዕከል (ኢንተርናሽናል ሴንተር ፎር አግሪካልቸራል ሪሰርች ኢን ድራይ ኤሪያ) ጋር ምርምር በማካሔድ ላይ ናቸው።**

**የዓለምአቀፍ ተመራማሪው የተወለዱት በድሮ ጎጃም ክፍለ አገር በአሁኑ አዊ ዞን ጓትሳ ሺጉዳድ ወረዳ ዛላ ቀበሌ ነው። ነጋዴ አባታቸው ቲሊሊ አካባቢ ወሰደዋቸው በቲሊሊ አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። የመካከለኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አዊ ዞን ግምጃቤት ተምረዋል። የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር በነበረው በቀድሞ አጠራሩ የዓለምማያ እርሻ ኮሌጅ ገብተው በእንስሳት ሳይንስ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።**

**ለሁለት ዓመታት በአምቦ አካባቢ ግብርና ላይ ሲሠሩ ቆይተው፤ የኖርዌ መንግሥት ወጪያቸውን ሸፍኖላቸው በታንዛኒያ ሶኪኔ ዩኒቨርሲቲ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዳጠናቀቁ ጅማ እርሻ ኮሌጅ በመምህርነት የተቀጠሩ ሲሆን፤ ከመምህርነት በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የትምህርት ኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ሲሠሩ ቆይተዋል።**

**በጅማ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ክፍል ኃላፊ፣ የኮሌጅ ምክትል ዲን፣ የግብርና ኮሌጅ ዲን ሆነው ካገለገሉ በኋላ ወደ ሕንድ በማቅናት በሕንዱ ናሽናል ዲዬሪይ ሪሰርች የሦስተኛ ዲግሪያቸውን በዚሁ በእንስሳት እርባታ ላይ ሠርተዋል።ከሕንድ ተመልሰው ወደ ጅማ በማቅናት የማኅበረሰብ አቀፍ እና የድህረ ምረቃ ከፍተኛ ዳይሬክተር ሆነው አገልግለዋል። የጅማ ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ማኅበረሰብ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው በማገልገል ላይ እያሉ፤ የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ መስራች ፕሬዚዳንት ሆነው ተሹመዋል።**

**ዩኒቨርሲቲውን ከማስገንባት ጀምረው ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር እንዲጀምር በማስቻል ከፍተኛውን ሚና መጫወታቸው ይነገራል። ከእኚሁ ጉምቱ ተመራማሪ እና መምህር ፕሮፌሰር ብርሃኑ በላይ ጋር ዩኒቨርሲቲው የተገነባበትን ሁኔታ፣ በሙያቸው የእንስሳት እርባታ ላይ እና አጠቃላይ ምርምርን በተመለከተ ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ፡-**

**አዲስ ዘመን፡-የነጋዴ ልጅ እንዴት የእንስሳት እርባታ ተማሪ እና ተመራማሪ ሆነ? ከሚለው እንጀምር፡፡**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** የአባቴ አባት በጣሊያን ወረራ ጊዜ ነው የሞቱት።በዚህ ጊዜ አባቴ 10 አመቱ ነበር። አባቴ በእንጀራ አባት ሲያድግ የተማረው ድቁናን እንጂ ዘመናዊ ትምህርት አልነበረም።አባት ያላቸው የእርሱ ጓደኞች ዘመናዊ ትምህርት ሲማሩ፤ እርሱ ግን መማር እየፈለገ ለመማር አልታደለም። ስለዚህ ከግብርናው በመቀጠል ወደ ንግድ ገባ። መማር እየፈለገ ሲነግድ ኖረ። ስለዚህ እርሱ ያጣውን ትምህርት ልጆቹ እንዲያገኙ ይፈልግ ነበር።

ወደ አስመራ እና ወደ አዲስ አበባ በመኪና 110 ኩንታል ዕህል ሲጭን በመመዘን እና ገንዘብ በመቁጠር ለማገዝ እሞክር ነበር። ጓደኞቼ ወደ ንግድ ሲገቡ፤ እኔም ወደ ንግድ ለመግባት ስሞክር ነበር፤ ነገር ግን አባቴ ፊት አይሰጠኝም ነበር። ክረምት ላይ ንግዱን ሳግዘው እርሱ ግን አይፈልግም ነበር።በመጨረሻ ፍላጎቴን እያየ እስከ መራገም ደረሰ። «ለሰው ልጅ መልካሙ ነገር ንግድ ሳይሆን ትምህርት ነው።ንግድም ቢሆን የሚያምረው ሲማሩ ነው» እያለ በትጋት እንድማር ይገፋኝ ነበር።በዚያ ምክንያት እኔም ወደ ትምህርቱ አዘነበልኩ፤ በኋላ አባቴም በጣም ደስተኛ ሆነ።

በጊዜው አጠቃላይ ብሔራዊ ፈተናን 300 እና 400 ልጅ ተፈትኖ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡት 7 እና 8 ልጆች ብቻ ነበሩ። እኔም ከ7ቱ መካከል አንዱ በመሆኔ በጣም ተደሰተ። እኔም በትምህርቴ መደሰት ጀመርኩኝ። አባቴ ሦስተኛ ዲግሪዬን እስከምጨርስ በሕይወት ኖሮ አይቷል፤ ከዓለም ድካም አርፏል። በዚህ ምክንያት የነጋዴ ልጅ ብሆንም ወደ ትምህርቱ አዘንብያለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- እሺ አሁን ወደ ዩኒቨርሲቲ እንግባ፤ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች በተለይ የአንደኛው ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች ነባሮቹ ከኮሌጅ ተነስተው ያደጉ ናቸው።እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ግን በአንድ ጊዜ ዩኒቨርሲቲ ከሆኑ የአራተኛው ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንደኛው ነው።እስኪ አመሠራረቱ እንዴት ነበር?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** አዎ! የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የምሥረታ ሂደት በተለያየ ፈርጅ ይታያል። የመጀመሪያ ትውልድ የሚባሉት እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ባህርዳር እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ የተመሠረቱት ከእርሾ ነው። ለምሳሌ ጅማ እርሻ ኮሌጅ ነበር። የጅማ ጤና ሳይንስ ኮሌጅም ነበር። በዲፕሎማ እና በዲግሪ የሚያስመርቁ ሁለት ኮሌጆችን አንድላይ በማድረግ የመጀመሪያ ትውልድ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተቋቋመ።

የሁለተኛ ትውልድ፣ የሦስተኛ ትውልድ እና የአራተኛ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች ግን በአብዛኛው የተመሠረቱት ከምንም ነው። ምንም እርሾ በሌለበት ማኅበረሰቡ ወይም የአካባቢው አስተዳደር ብቻ መሬት ያዘጋጃል። በጊዜው ለዩኒቨርሲቲዎች እስከ 200 እና ከዚያ በላይ ሄክታር መሬት ይሠጥ እና ዩኒቨርሲቲ ይገነባ ነበር።በወቅቱ በየአካባቢው ተደጋጋሚ የዩኒቨርሲቲ ይገንባልን የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩ።መንግሥት ደግሞ ጥያቄውን ተቀብሎ ዞኖችን አወዳድሮ በአዋጅ ዩኒቨርሲቲ እንዲቋቋም ውሳኔ ያስተላልፋል።

የዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ቦርድ ከተመደበ በኋላ ቦርዱ ፕሬዚዳንት መልምሎ ይመድባል። በዚህ ሂደት የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያ ተቀጣሪ እና መስራች ፕሬዚዳንት ሆኜ ሥራ ጀመርኩ። በቅድሚያ 200 ሄክታር መሬት ከተረከብኩ በኋላ፤ ምክትል ፕሬዚዳንት እና የአስተዳደር ፕሬዚዳንቶችን እንዲሁም የሰው ሀብት፣ የግዢ፣ የፋይናንስ እና የተማሪዎች አገልግሎትን የመሳሰሉትን የመቅጠር ኃላፊነት ተሰጠኝ።

የመጀመሪያው ሥራ ከሲቪል ሰርቪስ ጋር በመገናኘት መዋቅር እንዲፀድቅ ማድረግ ነበር። በጊዜው ብቻዬን ብሆንም የሌሎች ዩኒቨርሲቲ ሰዎችን እና ቦርዱን በመጠቀም መዋቅሩን አስፀደቅኩኝ። በመቀጠል ምክትል ፕሬዚዳንቶችን እና ሌሎችም የኃላፊነት ቦታ የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች ላይ ሰዎች ከተቀጠሩ በኋላ፤ ቅጥሩን እያሰፋን ቀጠልን። ለምሳሌ በቅድሚያ 50 እና 100 ሰው በወር እና በሁለት ወር ቀጥረን ከሆነ፤ ትንሽ አረፍ ብለን በድጋሚ እየቀጠርን ቀጠልን።

ሁለተኛው ሥራ የተሰጠንን መሬት ሕጋዊ አድርጎ ማጠር ነው።ቦታው ሰፊ ሲሆን በሃሳብ ይህን ያህል ነው ከማለት ውጪ፤ የተከለለ አልነበረም። ስለዚህ ምልክቶችን በማድረግ የዩኒቨርሲቲው መሬት መሆኑን ማረጋገጥ ስለሚያስፈልግ መሬት ከተገኘ በኋላ ወደ መሠረተ ልማት ተገባ።መሠረተ ልማት ሲባል የተማሪ መማሪያ፣ ማደሪያ እና መመገቢያ እንዲሁም ቤተመጽሐፍትን የመሳሰሉ ሕንፃዎችን ከመገንባት ጀምሮ መሥራት ተጀመረ።

ሕንፃው ብቻ ሳይሆን ዋናው ትልቁ ነገር መንገድ፣ ውሃ እና መብራትን እንዲሁም ቴሌኮሙኒኬሽንን የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች እየተሳሰሉ ይቀጥላሉ። ይህ በእውነቱ በኢትዮጵያ የቢሮክራሲ ሂደት እነዚህን ነገሮች ማሳካት ቀላል አልነበረም። ሕንፃዎችን ማስገንባትም በተመለከተ በመጀመሪያው ዙር ወደ 12 ተቋራጮች ነበሩ። የሠራተኛ ቅጥርን በተመለከተም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር አብረን ስንሠራ ቆይተናል። ሠራተኛው ተቀጥሮ ግንባታ ተካሒዶ፤ መብራት፣ ውሃ እና ኢንተርኔትን ጨምሮ ለማስተማር ብቁ መሆናችን ሲረጋገጥ በ2010 ዓ.ም ተማሪ መቀበል ጀመርን።

**አዲስ ዘመን፡-እንዴት በሁለት ዓመት ውስጥ ማጠናቀቅ ቻላችሁ?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** ሁሉንም ነገር በሙሉ ጥርት አድርገን በሁለት ዓመት ውስጥ ማጠናቀቅ ችለናል። ምክንያቱም ተቋራጮቹ አስራ ሁለት ነበሩ። አንዱ አንድ ትንሽ እና ትልቅ ሕንፃ ሲይዝ፤ ሌላኛው ውሃ አስገብቶ ይዘረጋል። ሌላኛው ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል ላይ ይረባረባል።ሁሉም ተከፋፍሎ ወደ ሥራ ገብቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ተማሪን ለመቀበል በሁለት ዓመት ውስጥ ስንት ሕንፃ ገነባችሁ? የኅብረተሰቡ አቀባበል ምን ይመስል ነበር?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** መኝታው፣ መማሪያው እና ቤተመጽሐፉ በአጠቃላይ ወደ 18 ሕንፃዎች ተገንብተው ነበር። ከዚህ ሁሉ በኋላ በ2010 ዓ.ም ታኅሣሥ ላይ ወደ አንድ ሺህ 500 ተማሪዎች ተቀብለን ማስተማር ጀመርን። ለአንድ ወር ካስተማርን በኋላ ዩኒቨርሲቲው ሥራ መጀመሩን በተመለከተ እና የተማሪዎች አቀባበል በሚል ማኅበረሰቡ ጥር 12 ቀን ትልቅ ፕሮግራም አዘጋጀ።

ለበዓሉ የከተማዋ ባለሀብቶች በሬ ገዝተው ሰጡ። ወጣቶች ተደራጅተው ሕዝቡን አስተባብረው ገንዘብ በማምጣት፣ በግ እና በሬ በማቅረብ ተሳትፈዋል።እድሮችም ለዩኒቨርሲቲው ምርቃት ብለው በበኩላቸው በሬ አቅርበዋል። በጣም የሚገርመው በዚያ ጊዜ በመንግሥት አቅም አጥር ለማጠር በመቸገራችን «ዩኒቨርሲቲ እንዴት ያለአጥር ይታያል?» ብለው የመጀመሪያውን ወደ ስምንት ኪሎ ሜትር የሽቦ አጥር የሠሩት በመዋጮ የአካባቢው ማህበረሰብ ነው።

በበዓሉ የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣ የወቅቱ አፈጉባኤ አቶ አባዱላ ገመዳ እና ብዙ ሚኒስትሮች፣ የክልል አመራሮች እና በሙሉ ባለሥልጣናት እንጅባራ ነበሩ። ኅብረተሰቡ የፈረስ ጉግስ ባህሉ በመሆኑ የፈረስ ጉግስ በማቅረብ በዓሉ ያማረ እና የደመቀ ሆኖ ተጠናቋል። ኅብረተሰቡ በሙሉ ልቡ የዩኒቨርሲቲው መገንባት አስደስቶት ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ስትጀምሩ ኮሌጆቹ እና የትምህርት ክፍሉቹ ምን ያህል ነበሩ?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ ፡-** መነሻችን አራት ኮሌጆች ናቸው። ተፈጥሮ ሳይንስ፣ የማህበራዊ ሳይንስ፣ ቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ነበሩ። አንዳንዱ ሦስት አንዳንዱ አራት በአጠቃላይ ወደ 16 እና 17 አካባቢ የትምህርት ክፍሎችን በማዘጋጀት ተማሪዎችን ከፋፍለን ማስተማር ጀመርን።

**አዲስ ዘመን፡- ከሕንፃ ግንባታው ባሻገር በአዲስ ዩኒቨርሲቲ ከዜሮ ጀምሮ መምህራንን ጨምሮ አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲ ሠራተኞችን መቅጠር ፈተና እንደሚኖረው አያጠያይቅም። እዚህ ላይ እንዴት እንደነበር ያብራሩልን።**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** ትክክል ነው። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሁለት የሠራተኛ ዓይነት አለ። አንደኛው የአስተዳደር ሠራተኛ ሲሆን፤ ሌላኛው መምህር ነው።የአስተዳደር ሠራተኞችን በማስታወቂያ ቀጠርን። ዩኒቨርሲቲ ስሙም ጥሩ በመሆኑ በአካባቢው ከዞን እና ከሌሎች የመንግሥት ተቋማት ልምድ ያላቸው ተወዳድረው እና የቅጥር መስፈርቱን አሟልተው ወደ ዩኒቨርሲቲው ተቀላቀሉ።

የመምህራን ጉዳይ የመጀመሪያው መምህር ራሴ ነበርኩኝ። ምክትል ፕሬዚዳንቶቹም ያስተምሩ ነበር።በመቀጠል ግን መምህራኑን ያሟላነው በሁለት መንገድ ነው። የትምህርት ሚኒስቴር ቀድሞ ዕቅድ ስለነበረው ከሁለት ዓመት በፊት ቀድሞ በመጀመሪያ ዲግሪ ጥሩ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲማሩ በማድረግ ዩኒቨርሲቲው ሥራ ሲጀምር ከ100 በላይ የሚሆኑትን መምህራኖች የትምህርት ሚኒስቴር ለዩኒቨርሲቲው አቀረበ። ነገር ግን ተመራቂዎቹ ምንም ዓይነት ልምድ ሳይኖራቸው ከትምህርት ቤት በቀጥታ የመጡ ናቸው። የሥራ ዓለም ልምድ አልነበራቸውም። ይህ ቀላል ችግር አልነበረም።

ሁለተኛው እነርሱ በቂ ስላልነበሩ ማስታወቂያ በማውጣት መምህራን እንዲፈተኑ እና ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ የትምህርት ክፍል ፍላጎቶችን ለማሟላት ችለናል። ፈተናውን በተመለከተ ለየት ያደረግነው፤ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የካበተ ልምድ ያላቸውን መምህራን በፈታኝነት እንጋብዝ ነበር። ለምሳሌ አምስት የአካውንቲንግ መምህር ከተፈለገ ከጎንደር፣ ከባህርዳር፣ ከደብረማርቆስ፣ ከጅማ እና ከሌሎችም ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ መምህራን ይፈትኑ ነበር።

ፈተናው አንደኛ ቃለመጠይቅ ሲሆን፤ ሌላው የአስተማሪነት ብቃትን ለማወቅ አንድ የትምህርት ክፍል ወስደው በፋይናንስ ከሆነ ተፈታኞች ፈታኞችን እንደተማሪ በማሰብ ትምህርቱን እንዲያስተምሩ በማድረግ በመስፈርቱ ነጥብ ተሰጥቷቸው ይመዘናሉ፤ ይለያሉ።ሌላው የሁለተኛ ዲግሪያቸው ላይ ወይም የቆዩ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከነበሩ የሠሯቸው ምርምሮች ይኖራሉ፤ ስለዚህ ምርምራቸውን ያቀርባሉ።በመጨረሻም በማስተማር ስልታቸው፤ በቃለመጠይቅ እና በምርምር ምርጥ የሆኑት ይቀጠራሉ። ስለዚህ በአጠቃላይ ከትምህርት ሚኒስቴር በተገኙት መምህራን እና በቅጥር የመለመልናቸውን አጣምረን ወደ ማስተማር ገብተናል።

**አዲስ ዘመን፡- በወቅቱ የገጠማችሁ ፈተና ምን ነበር?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** ይህንን ስናደርግ አንዱ ፈተና ዩኒቨርሲቲው ሲመሠረት ከቦታው የተነሱ ገበሬዎች ነበሩ። መጀመሪያ ከነበረው መሬት በተጨማሪ እኔ ሞያዬም ከእርሻ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ቀድሞ ከነበረው 200 ሔክታር በተጨማሪ ተራራውን ጨምሮ 125 ሔክታር መሬት እንዲካተት አድርጌያለሁ። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው በ325 ሔክታር ላይ የተቋቋመ ሲሆን፤ በዚህም ብዙ የልማት ተነሺ ገበሬዎች ነበሩ።

ገበሬዎቹ መሬታቸውን አስረክበውናል። ነገር ግን የተሠጣቸው ካሳ በጣም ትንሽ በመሆኑ ማድረግ ያለብንን ተወያይተን ለተነሺዎቹ ልዩ ድጋፍ ተመቻቸ። አንደኛው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «ግብርና ላይ ውጤታማ መሆን ከተፈለገ ዘርፉን...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ራሳቸው ወይም ቤተሰቦቻቸው በዩኒቨርሲቲው ሥራ ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ወሰንን።በዚህ ምክንያትም ወደ 260 የልማት ተነሺ ሲሆን፤ ቢያንስ ከየቤተሰቡ አንዳንድ ሰው ወደ ሥራ እንዲገባ አድርገናል። ለምሳሌ በጥቃቅን እና አነስተኛ ተደራጅተው በዩኒቨርሲቲው የአረንጓዴ ልማት ላይ ይሰማራሉ። እነዚህ ሰላሳ እና አርባ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሌላው ዩኒቨርሲቲው የምግብ ግብዓት ያዘጋጃል፤ እነርሱ ደግሞ ሥራ ይሠራሉ። ማብሰል እና ፅዳት እንዲሁም ጥበቃ እና ሌሎችም የተለዩ ወደ ሰባት የሚደርሱ የሥራ ዘርፎች ላይ እነኚህ ወደ 260 የተጠጉ አርሶ አደሮች በልዩ ሁኔታ ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዲቀላቀሉ አድርገናል። ይህ ዩኒቨርሲቲው በማኅበረሰቡ ተቀባይነት እንዲኖረው እና እንዲወደድ አድርጓል። ይህ የሆነው ዩኒቨርሲቲው ከኋላ በመፈጠሩ እና የሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችን ተሞክሮ በማየታችን ነው።

እኔ ሥራውን ስጀምር ከእኔ በፊት የነበሩትን የሦስተኛ እና የአራተኛ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎችን በሙሉ ያጋጠማቸውን አጥንቼ ነበር። ቅጥር ላይ እና ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር እንዲሁም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር እንዴት እንደሚሠሩ አጠቃላይ የነበረባቸውን ግንኙነት በደንብ አጥንቼ ስለነበር ያንን ማወቄ በጣም ረድቶኛል።

ሁለተኛው በአካባቢው ገበሬው ከወጣ በኋላ ሳር ነበር። በጊዜው በዩኒቨርሲቲው ከብት እርባታ አልነበረንም። ስለዚህ ሳሩን ለሁለት እና ለሦስት ዓመት በነፃ እንዲጠቀሙ አድርገናል። ይህ በጣም ትልቅ ነገር ነው።ሌላው የገበሬዎች ልጆች ሆነው የመማሪያ መስፈርቱን የሚያሟሉ ከሆነ ያለምንም ክፍያ ወጪያቸው ተሸፍኖላቸው የማታ እንዲማሩ ይደረግ ነበር። የድሃ ድሃ የሚባሉት የእነዚያው የገበሬዎች ልጆችን በዶሮ እርባታ በማደራጀት ራሳቸውን እንዲችሉ ጥረት ተደርጓል።አሁንም የዶሮ እርባታው ቀጥሏል።በዚህ ምክንያት አንድም ቀን በዩኒቨርሲቲው እና በአካባቢው ማኅበረሰብ መካከል ግጭት እና ቁርሾ አልነበረም።

ይህንን አካሔድ በመከተላችን በጊዜው አጥር የሌለው ዩኒቨርሲቲ ምንም ዓይነት ሌብነት አላጋጠመውም። በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ያጋጠመው ችግር እንጅባራ ዩኒቨርሲቲን አላጋጠመውም። እንዲያውም የአካባቢው ማኅበረሰብ በየዓመቱ ድግስ እየደገሰ ይጠራናል። የእኛ ድርሻ ልብስ ለብሶ መቅረብ ነው። ይህ እጅግ የሚያኮራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዩኒቨርሲቲው ምስረታ ወጣ ብለን ወደ ምርምር እንግባ። በእርግጥ ዩኒቨርሲቲዎች ምርምሮችን ያካሒዳሉ።ነገር ግን የሚያካሂዷቸው ምርምሮች ወርደው የማኅበረሰብን ሕይወት ከመቀየር አንፃር ክፍተት አለባቸው በሚል በተደጋጋሚ ወቀሳ ይሰነዘራል።እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** በኢትዮጵያ ደረጃ እንደዩኒቨርሲቲዎቻችን ብዛት፣ እንደሕዝባችን ቁጥር፣ በአቅማችን ቢሆንም እንደሚመደበው በጀት ብዙ ህትመት የለም። ከአውሮፓ ቀርቶ ከኬንያን እና ከደቡብ አፍሪካ አንፃር ስናየው በቂ አይደለም። ያም ሆኖ ደግሞ በመምህራን እና በተመራማሪዎች በኩል በግብርና ሚኒስትርም ሆነ በዩኒቨርሲቲዎች ህትመት አለ።

ህትመቶች በመኖራቸው በጣም ደስተኛ ነኝ። ምክንያቱም አንደኛ ህትመቱ በሀገራችን ሁኔታ የሁለተኛ ዲግሪም ሆነ አንደኛ ዲግሪ የሚማሩ እንደአቅማቸው ምርምር ሲያካሂዱ የታተመውን ምንጭ ሊደርጉት ይችላሉ። ያ ባይኖር ኖሮ የሕንድን ወይም የአሜሪካን ወይም የጃፓንን ያጣቅሱ ነበር። ይህ ማለት በእኛ ሀገር ተቀባይነቱ እና ተፈላጊነቱ እስከዚህም ይሆናል። ስለዚህ ምርምሩ የወደቀ አይደለም። ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም። ከምርምሮቹ ውስጥ ወደ ማኅበረሰቡ መሔድ ያለባቸው አሉ። ሁሉም ግን ወደ ማኅበረሰቡ መሄድ አለበት ማለት አይደለም።

150 የምርምር ህተመቶች ቢኖሩ ሁሉም ቴክኖሎጂ ወይም ሁሉም አሠራርን የሚቀይሩ አይደሉም። ከእነዚህ ውስጥ አምስቱ አሠራርን ወይም ፖሊሲን የሚቀይሩ ከሆነ ለምሳሌ የግብርናን ምርት እና ምርታማነት ከፍ ለማድረግ የሚጠቅም ከሆነ መልካም ነው።ነገር ግን በዚህ ረገድም ሲታይ ውስንነት አለባቸው። ለምሳሌ ዘርን ብንወስደው የምርምር ውጤት ነው። የማዳበሪያ አጠቃቀም የምርምር ውጤት ነው።እንስሳትን መቀለብ የምርምር ውጤት ነው። በዚያ ረገድ ጥረቶች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም። ነገር ግን እያንዳንዱ የሚያሳትመው ሰው አንዷን እንኳን መሬት ላይ ሳያደርስ ከቀረ ይህ በጣም አደገኛ ነው። 150ውን መሬት ያድርስ አይደለም፤ ቢያንስ አንድ ሁለቱን ምርምር የኀብረተሰቡን ምርት እና ምርታማነት ከፍ እንዲያደርግ አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት።በዚህ ረገድ የተሳካላቸው ጥቂት ሰዎች አሉ። በአብዛኛው የተሳካላቸው አይደሉም። ስለዚህ ይህንን ለማድረግ በትክክልም ምርምሩ ሲሠራ ከመጀመሪያው አንስቶ ከማኅረሰብ አንፃር መታቀድ አለበት።

ተመራማሪዎች ምርምሩን ሲያካሂዱ ከማሳተም ባሻገር በተግባር ፖሊሲ የሚያስቀይር፤ የገበሬውን ምርታማነት የሚያሻሽል፣ የጤና ሁኔታን የሚያሳድግ ተብሎ መጀመሪያ መታቀድ አለበት። እንዳልኩት በዚህ ረገድ የተሳካላቸው አሉ። ያልተሳካላቸውም አሉ። ምርምርን ሼልፍ ማድረግ በየትኛውም ዓለም አለ። በጣም የሚያሳዝነው ግን ጭራሽ ለሼልፍም ያልበቃው ነው። መረጃ ተሰብስቦ ገንዘብ ወጥቶለት ወደ ህትመት የማይደርስ እና ለተማሪዎች እንኳን ማጣቀሻ የማይሆን አለ። መረጃው እያለ ሳይተነተን የጨነገፈ አለ።የሚያሳዝነው ይህኛው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዩኒቨርሲቲም ሆነ በምርምር ተቋማት የተመራማሪው ቁጥር ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ምን ያህሉ በምርምር የማኅበረሰብን ሕይወት ቀይሯል? የሚለው አጠያያቂ ነው። ይህ የሆነው በምን ምክንያት ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** የመጀመሪያው ምርምር ፈንድ በሚደረግበት ጊዜ የማኅበረሰብ ተጠቃሚነት በዕቅድ ውስጥ መግባት አለበት። ህትመት(ፐብሊኬሽን) አንዱ መለኪያ ይህንን ገንዘብ ሰጥቼሃለሁ አምስት ህትመት ማምጣት አለብህ ይባላል። ለምሳሌ ሦስተኛ ዲግሪ ስናሰለጥን ህትመት ማሳተም አለበት እንላለን።አምስት የሚታተም ከሆነ አንዱ ማኅበረሰቡን የሚጠቅም መሆን አለበት ተብሎ መጀመሪያውኑ መታቀድ አለበት።

ሁለተኛው ችግር የሚሆነው አንድ ቴክሎጂ ወይም አሠራር ቢወጣም፤ ያንን ተጠቃሚ የሚሆን ለምሳሌ ከግብርና አንፃር ብንወስደው ምርምሩ እና የልማት ባለሞያው መናበብ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ ምርምር አለ። የምርምር ውጤት እና ቴክኖሎጂ አለ። የአሠራር ስልት አለ። ይህንን የአሠራር ስልት ደግሞ ተቀብሎ መሬት ላይ የሚያወርድ የልማት ባለሞያው ወይም የግል ዘርፉ በቁርኝት ደረጃ መተግበር አለበት።

ሁለተኛው ሰው መበረታታት ይፈልጋል። አሳትሞ የቆመው ሰው እና አሳትሞ ወደ መሬት ያወረደው ሰው መካከል ልዩነት መኖር አለበት። መሬት ያወረደው ሰው ዕውቅና ሊሰጠው ይገባል። ዕውቅና በማመስገን ሊሆን ይችላል፤ በገንዘብ ሊሆን ይችላል። ወይም ሌላ አካባቢ ሄዶ እንዲያይ የመሳሰሉ ማበረታቻዎች መኖር አለባቸው።

የኢንዱስትሪ እና የዩኒቨርሲቲዎች ትስስር አናሳ መሆንም ምርምር የማኅበረሰቡን ሕይወት እንዳይቀይር ያደርጋል። በሌሎች ሀገሮች ኢንዱስትሪው ችግር ይዞ ይመጣል። ይህንን ፍታልኝ ብሎ ለዩኒቨርሲቲው ገንዘብ ይከፍላል። ኢንዱስትሪው እንዲታከም ዩኒቨርሲቲው መድኃኒቱን በምርምር ያገኛል። ስለዚህ ቅንጅት ያስፈልጋል የሚል ሃሳብ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ምርምር ብዙ ጊዜ እና ከፍተኛ ጉልበት የተለየ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል።ከዚህ አንፃር ሰልጥነዋል ተብለው የሚጠቀሱ ሀገራት ለምርምር በጀት ከመመደብ አንስቶ የሚሰጡት ትኩረት ከፍተኛ ነው።ምንም እንኳ የሀገሪቱ የዓቅም ሁኔታ ቢታወቅም በትክክል ለምርምር የሚሰጠው በጀት በቂ ነው ብለው ያምናሉ?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** እዚህ ላይ እኔ በተገላቢጦሽ የምርምር ገንዘብ የሚገኘው ከመንግሥት ብቻ ነው? የሚል ጥያቄን ማንሳት እችላለሁ። የምርምር ገንዘብ የሚገኘው ከመንግሥት ብቻ አይደለም። የሌሎች ሀገሮችም ተሞክሮ ይህንን አያሳይም። የምርምር ገንዘብን ከሦስት አቅጣጫ ማግኘት ይቻላል። አንደኛው እና ትልቁ ከመንግሥት ነው።ሁለተኛው ከልማት አጋሮች ነው። ይህ በውድድር የሚገኝ ሲሆን፤ ፕሮፌሰሮች እና ተመራማሪዎች ከሌሎች ሀገሮች ጋር ተወዳድረው የሚያገኙት ገንዘብ አለ።ሦስተኛው የገንዘብ ምንጭ ኢንዱስትሪው ነው።ከላይ እንደገለፅኩት የኢንዱስትሪውም በትስስር የሚገኝ ነው።

እነዚህን ሦስት ነገሮች አጣጥመን መሔድ አለብን። በእርግጥ ኢትዮጵያ ውስጥ በሦስቱም መልክ ውስንነት አለብን። መንግሥት በቂ ገንዘብ መመደብ ብቻ ሳይሆን፤ ይህንን ገንዘብ የምመድበው ይህንን ውጤት እንድታመጣ ነው የሚል ተጨባጭ ነገር የመጠየቅ ውስንነት አለበት። ሁለተኛው የባለሙያው ልምድ እና ተወዳዳሪነት ነው። ከእነኚህ ከልማት አጋሮች ጋር ተነጋግሮ ለማምጣት ውስንነት አለ። በሦስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ትስስሩ አናሳ ነው። ስለዚህ ሁሉም ድርሻ አለው፤ ችግሩ ሁሉን አቀፍ ነው፤ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ደግሞ በተለየ መልኩ በእርሶ ዘርፍ ያለውን ጉዳይ በተመለከተ እንነጋገር።ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ግንባር ቀደም ከሆኑ ከአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ጭምር ተጠቃሽ ሀገር ናት።በተቃራኒው በዚህ ሀብቷ ተገቢውን ጥቅም እያገኘች ስላለመሆኑ እና ብዙዎች በዚህ እንደሚቆጩ ይነሳሉ።ለዚህ ምላሾት ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** እርግጥ ከቁጥር አንፃር ከሆነ ኢትዮጵያ ትልቅ ቁጥር ያለው የእንስሳት ክምችት አላት።ይህ በትንበያ ነው። ትንበያውን እንውሰድና በሁሉም የእንስሳት ዓይነቶች ከፍተኛ ቁጥር ያለው እንስሳት አለን፤ እንበል።ነገር ግን ምርት እና ምርታማነታቸው ከዚህ በላይ መሆን አለባቸው ብለን ስናይ ብዙ ጊዜ የምንሳሳተው በወተት፣ በስጋ እና በእንቁላል ብቻ ስለምንመዝን ነው። የእኛን ሀገር ከውጭው ለየት የሚያደርገው እርሱ ነው።

እርሻው ዘርፍ ላይ ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚሆን አርሶ የሚያበላው በሬ ነው። ይህ መታወቅ እና መደነቅ አለበት።ብዙ ጊዜ የእንስሳት ምርት እና ምርታማነት ላይ ይህ ስሌት ውስጥ አይገባም። በዕቅድም ላይም ወተት እና ስጋ ብቻ ይጠቀሳል። ሁለተኛው ገበሬው በጣም የሚጠቀምበት ከስጋ፣ ከወተት በተጨማሪ እንስሳት ገንዘብ ናቸው። ለምሳሌ በግ እና ፍየልን ማንሳት ይቻላል። እነዚህ ለትንንሽ አርሶ አደሮች ልክ እንደ ኤቲ ኤም ናቸው። ሲቸግራቸው በአስቸኳይ ይሸጧቸዋል።

የስጋ፣ የወተት፣ የእርሻ፣ የፈጣን ገንዘብ ማግኛ ሆነው ግን የእንስሳትን ሀብት ጥቅም በትክክል እየተመዘነ አይደለም።ይህ በመንግሥት ደረጃም የታየ ነው።በዚህ ምክንያት ለዚያ የምንሰጠው ትኩረት ከሰብል ያነሰ ነው። እንደእኔ መላምት እነዚህ ሁሉ ነገሮች አንድላይ መጥተው ጥናት ቢካሔድ በቂ ትኩረት ባያገኝም ለእዚህች ሀገር የእንስሳት አስተዋፅኦ በጣም ከፍተኛ ነው። ነገር ግን በዚህ ደረጃ አልታየም።ትኩረት ባለመስጠታችን እየተንጠላጠልን ያለነው የውጭ ዝርያ በማምጣት ያለመዱትን አካባቢ በግድ እንዲለምዱ እያደረግን ነው።

የውጭ ላሞች ሀገራቸው ላይ 30 እና 40 ሊትር ወተት ያመርታሉ ይባላል። ከቻይና የመጣ ወፍጮ ቻይናም ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ 50 ኩንታል ሊፈጭ ይችላል። ከእንስሳት አንፃር ግን የሀገሩን በሬ በሀገሩ ሰርዶ እንደሚባለው ነው። እንስሳቱ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ማሽን ባለመሆናቸው ውጤቱ ተመሳሳይ አይሆንም።ስለዚህ እዚሁ ያሉ እንስሳትን በመምረጥ እና በማሻሻል፣ የእንስሳት መኖን በማዘጋጀት እና የገበያ ትስስር በመፍጠር የእንስሳትን ምርት እና ምርታማነት ከፍ ማድረግ ይቻላል።

አሁን እየሠራሁበት ያለው መስሪያ ቤት ከዓለምአቀፍ የቆላማ አካባቢዎች የግብርና ምርምር ሥራ ማዕከል (ኢንተርናሽናል ሴንተር ፎር አግሪካልቸራል ሪሰርች ኢን ድራይ ኤሪያ) ትልቁ አላማው የሀገር በግ እና ፍየልን እዚያው ቤታቸው ላይ እያሉ ማሻሻል ነው። ላለፉት አስር ዓመታት ይህ ፕሮግራም እየተካሔደ ነው።ወደ ሁለት መቶ መንደሮች እና ቀበሌ ገበሬ ማህበራት አሉ። አንድ መንደር 100 ገበሬዎችን ይይዛል። ይህንን ሥራ ስናከናውን ሦስት መሻሻሎች ታይተዋል። አንደኛ በዚህ የዝርያ ማሻሻል የታቀፉ ገበሬዎች ካልታቀፉት 20 በመቶ ገቢያቸው አድጓል። አንድ በግ ብቻ ያርድ የነበረ ገበሬ ሦስት በግ ማረድ ችሏል። አንደኛ ገቢ ነው። ሁለተኛ የምግብ ዋስትና ነው።ፋሲካ ወይም መውሊድ ላይ አንድ በግ ሲያርድ የነበረው ገበሬ አሁን ላይ ሦስት በግ ማረድ ችሏል። ይህ የዛሬ አምስት ዓመት የተጠና ጥናት ነው። እዚህ ላይ ከሥራ ፈጠራ ጋር በማቀናጀት መኖን ብናዘጋጅ የእኛን እንስሳት ማሻሻል እንችላለን።

ገበሬው የምትፈልገው የስንዴ ማሳህን ነው ወይስ በሬህን የሚል አማራጭ ቢቀርብለት፤ መልሱ ሁለቱንም እፈልገዋሁ የሚል ነው። ባለሞያው ግን የሚሻልህ ስንዴ ነው ይለዋል። ነገር ግን እውነቱን ለመናገር በሰብልም ያን ያህል አልተሻሻልንም። ከውጭ የምናስመጣው ወተት ብቻ አይደለም። ስንዴንም ሆነ ሩዝን ከውጭ እናስመጣለን። ጤፍን የምናስመጣበት አጥተን እንጂ እናስመጣ ነበር። ስለዚህ ግብርናው በእንስሳት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሁሉን አቀፍ ችግር አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ችግር መኖሩን ካመንን መፍትሔው ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** የመጀመሪያው መፍትሔ የመሬት ስሪታችን መታየት አለበት። መሬት የመንግሥት እና የሕዝብ ነው ይላል።ይህንን በደንብ ማየት ይፈልጋል።ሁለተኛው ከላይ እንደጠቀስነው ምርምሩ ቴክኖሎጂን አፍልቆ ጥሩ ዝርያ እንዲያመርት መሥራት ያስፈልጋል። ከዚያም ምርታማነቱ ሲጨምር በተለያየ መንገድ አግሮ ፕሮሰሲንግን በመደገፍ ኢንዱስትሪ ማስፋትን ይጠይቃል። ትልቁ ነገር ግብርና ዕውቀት ይፈልጋል። አያቶቻችን እና አባቶቻችን ሀገር በቀል ልምድ አላቸው።ያ የሚናቅ አይደለም፤ ነገር ግን በተጨማሪ ግብርና እውቀት ይፈልጋል።ግብርና ዕውቀት የሌለው ሰው ሥራ መሆን የለበትም፡፡

ገበሬው በደረጃው ዕውቀት ያስፈልገዋል፤ የግብርና ልማት ባለሙያውም ሆነ ተመራማሪው እንዲሁም አግሮ ፕሮሰሰሩ ዕውቀት ያስፈልገዋል። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ዛሬ የልማት ሠራተኛው ገበሬውን የማማከር ብቃቱ አነስተኛ ነው።ይህንን አትረስ፤ በዚህ ሰዓት ጥመድ፤ በዚህ ሰዓት ፍታ ማለት ዕውቀት አይደለም።የገበያ ትስስርም አስፈላጊ ነው ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ከዕውቀት ችግር ባሻገር ግን የልማት ባለሞያው ደሞዙን ብቻ አስቦ ሳይሆን በተጨባጭ የአርሶ አደሩን ሕይወት ለመለወጥ እንዲሠራ ምን መደረግ አለበት?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** ገበሬው ዕውቀቱን እና ጉልበቱን አጣምሮ በመሬቱ ላይ ውጤታማ እንዲሆን ዕውቀት ያስፈልገዋል። ገበሬውን ደግሞ የሚያሰለጥነው የግብርና ባለሞያ ዕውቀት ያስፈልገዋል። ባለሞያውን የሚያሰለጥነው መምህር ዘመኑን በዋጀ መንገድ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ዕውቀት ያስፈልገዋል። የሕንድ ዕውቀት አይደለም። የአገራችን ዕውቀት ያስፈልገዋል። ይህንን ደግሞ የሚመራ ተቋም ግብርና ሚኒስቴር፣ ግብርና ምርምርም ሆነ ዩኒቨርሲቲ ይህንን ሥራ በአግባቡ መምራት አለበት። በአግባቡ መምራት ማለት የበጀት ፣ የገበያ ፣ የሚሰለጥኑ ሰዎችን ማበረታታት ከሁሉም በላይ ደግሞ የብድር ሁኔታ ተገቢውን ትኩረት ማግኘት አለባቸው።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ግብርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የተሸከመ ቢሆንም ኢንቨስት የሚደረግበት ግን በጣም አነስተኛ ነው። ከትራንስፖርት፣ ከኢንዱስትሪ ጋር ሲወዳደር በጣም ትንሽ ነው። አንድን ሥራ ውጤታማ ለማድረግ ኢንቨስት የሚደረግበት መጠን ወሳኝነት አለው። የግብርና አነስተኛ ነው። ለሆቴል ግንባታ ብድር ይገኛል።ለግብርና ብድር ለማግኘት ጣጣው ብዙ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይሔንን ቀደም ብለው ከጠቀሱት ከመሬት ሥሪት ጋር ማያያዝ ይቻላል?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** ትንሽ ለየት ይላል።

**አዲስ ዘመን፡- ነገር ግን አንድ አርሶ አደር የመሬት ባለቤት ከሆነ መሬቱን አስይዞ መበደር ይችላል፡፡**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** አዎ! ዋናው ጉዳይ ግን በየትኛውም ሁኔታ ብድር መገኘት አለበት። ግብርና የተረሳ ሥራ ነው። ለምሳሌ በደጋም ሆነ ቆላም ወደ አፋር፣ ወደ ጋምቤላ፣ ወደ አማራ ክልል ሲኬድ ብዙ መሬቶች አሉ። እነዚህን በግል ዘርፍ መልማት አለባቸው። ደጋው ላይ ብቻ አንድና ሁለት እርሻ ስላለ ግብርናው አያድግም።የግል ዘርፉ ብድር በደንብ ተሰጥቶት ቁጥጥር እና ግምገማ እየተካሄደ አጭበርባሪውን በደንብ ለመግታት መሥራት ይገባል።

ለምሳሌ በ1960ዎቹ በግብርና ሞያ ላይ ያለው ዩኒቨርሲቲ ዓለምማያ ነበር።በግብርና ዲግሪ የጨረሰ ኢንተርፕርነር መሆን የፈለገ ብሔራዊ ባንክ ዲግሪውን አስይዞ መበደር ይችል ነበር።በዚህ ምክንያት እነሁመራ፤ መካከለኛው አዋሽ ፣ ተንዳሆን የመሳሰሉት የለሙት በዚያ ጊዜ ነው።ወደ ሻሸመኔ ቦለቄ እና አኩሪ አተር የተመረተው በዚያ መልኩ ነው።ነገር ግን በ1966 ዓ.ም አብዮቱ ሲፈነዳ እነዛ በጣም ሃብታም እየሆኑ የነበሩት ብላቴናዎች መሬቱ ተወሰደባቸው ብድሩንም አልከፈሉም።

በኋላም ወደ አሜሪካን እና ወደ ሌሎችም ሀገሮች ተሰደዱ።ስለዚህ ግብርና ላይ ውጤታማ መሆን ከተፈለገ ዘርፉን ወደ ፕራይቬታይዜሽን ማዞር ነው።በሆነ መንገድ የግል ዘርፉ ወደ ግብርና ካልገባ በስተቀር የሀገሪቱ ምርት እና ምርታማነት ከፍ አይልም።እንስሳት ብናረባ መዓት ውጤት ማግኘት ይቻላል፤ ስንዴን ብናመርት በጣም ብዙ ዕድል አለ።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ በዋናነት በእንስሳት ዘርፉ ላይ መሠራት አለበት የሚሉት ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** የውጭ ዝርያዎችን ማስመጣት የጀመርነው በ1950ዎቹ ነው። በጥቁር እና ነጭ ላሞች ማለት ነው።ነገር ግን የውጭ ዝርያ ያላቸው ከብቶች ዝርያ አሁንም ከአንድ እና ከሁለት በመቶ አላለፉም።ስለዚህ መሆን ያለበት የእኛን የሀገራችንን ዝርያ ማሻሻል ያስፈልጋል። አቅም ያለው እና የአውሮፓን የአሠራር ሥርዓት መተግበር የሚችል ፕራይቬት እንዲሠማራ ማድረግ ነው።እነሳውዲ አረቢያ እና እነእስራኤል በጣም ሞቃት ሀገሮች ቢሆኑም፤ አሁን በወተት ምርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ናቸው። የሚያደርጉት በቤት ውስጥ የአየር ሁኔታውን ከብቶቹን ካመጡባቸው አካባቢዎች የአየር ሁኔታ ጋር አመሳስለው የሚፈለገውን መኖ በማቅረብ ከአሜሪካ እና ከአውስትራሊያ ወተት ማምጣት አቁመው የራሳቸው ምርት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ስለዚህ የእኛን ምርታማነት ማሻሻል ይቻላል።

ሁለተኛ የተመረተው ምርት ላይም ብዙ ነገር አለ። ለምሳሌ ከበግ አንፃር እንመልከት ከተባለ ሐረርም ሆነ ሌሎች አካባቢዎች ገበሬው አምርቶ መሸጥ አይችልም።ዋጋ የሚቆርጠው ደላላው ነው። ገበሬው በለፋው ልክ አያገኝም፤ ደላላው ሸጦ ብዙ ያተርፋል።ይሔ ደግሞ አያበረታታም።ስለዚህ የገበያም ችግር አለ። መፍትሔው ግን ምርትን ማብዛት ብቻ ሳይሆን የገበያ ትስስር ላይም መሥራት ይፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም በጣም አመሰግናለሁ፡፡**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## የሕፃናት ዓይን ሕክምናን የማስፋት ጅምር

**አስናቀ ፀጋዬ**

ከኢትዮጵያ አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር 70 ከመቶ ያህሉ ወጣት ነው። ከዚህ ውስጥ ደግሞ አብዛኛዎቹ ዕድሜያቸው ከአስራ አምስት አመት በታች መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ።ይህ አሃዝ ኢትዮጵያን በቀጣይ በሁለንተናዊ መልኩ ሊለውጡ የሚችሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች እንዳሏት ያሳያል።ሆኖም የወጣቶች ቁጥር መብዛት ብቻውን ሀገርን ሊለውጥ አይችልም።ምክንያቱም ቅድሚያ የሚሰጠው የጤና ጉዳይ ነውና ወጣቱ ኃይል ጤናው ተጠብቆ በሚፈለግበት የሥራ ዘርፍ መሰማራት ስላለበት ነው።

በሌላ በኩል ከኢትዮጵያ ወጣት የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ ከ60 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ከአስራ ሁለት አመት በታች የሆኑ ሕፃናትና ታዳጊዎች እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚህ አንፃር በተለይ ሕፃናትና ታዳጊዎች የነገ ሀገር ተስፋ ናቸውና የእነርሱ ጤና መጠበቅ ወሳኝ መሆኑ ሁሉንም ያስማማል።ሕፃናትና ታዳጊዎች ጤናቸው ሲታወክ ሁሉንም ዓይነት የሕክምና አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይጠበቃል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የዓይን ሕክምና አገልግሎት ነው።ሆኖም በሀገሪቱ ከፍተኛ የሕፃናት ዓይን ሕክምና አገልግሎት እጥረት መኖሩ ይነገራል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በሀገሪቱ የሚገኙት የዓይን ስፔሺያሊስት ሀኪሞች ቁጥር ዘጠኝ ብቻ ነው። ከነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ሀኪሞች በግልና መንግሥታዊ ባልሆኑ የሕክምና ተቋማት ውስጥ የሚያገለግሉ ናቸው። ይህም የሕክምና አገልግሎቱን ከሚፈልጉ ሕፃናት ቁጥር ጋር ሲነፃፀር የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት ያለው መሆኑን ያሳያል። በመንግሥት ደረጃ አገልግሎቱን የሚሰጡ ጤና ተቋማት ቁጥርም ከሦስት የማይበልጥ በመሆኑ የሕፃናት ዓይን ሕክምና አገልግሎት ችግር እጅግ የገዘፈ መሆኑን ይጠቁማል።

ዶክተር ሰለሞን ቡሳ በአለርት ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የዓይን ስፔሺያሊስት ሀኪምና በሆስፒታሉ የዓይን ሕክምና ክፍል ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት የሕፃናት ዓይን ሕክምና አገልግሎት አሁን ላይ ካለው ሕክምና ፈላጊ ሕፃናት ቁጥር ጋር አይመጣጠንም። በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሞያዎች ቁጥር ዝቅተኛ መሆንና የዓይን ሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስንነትም አገልግሎቱን በሚፈለገው ልክ ለመስጠት አላስቻለም።

በአሁኑ ጊዜ የሕፃናት የዓይን ሕመም እየጨመረ በመምጣቱ ችግሩን ለመቅረፍ ባለሞያዎችን ማሰልጠንና የዓይን ሕክምና መስጫ ተቋማትን ማስፋት ያስፈልጋል።ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሕክምና አገልግሎቱን ለማስፋት በመንግሥትም ሆነ በግለሰቦች የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ።ከነዚህ ውስጥ አንዱ አለርት ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በግቢው ውስጥ ለማስገንባት የመሠረት ድንጋይ ያስቀመጠበት የሕፃናት ዓይን ሕክምና ማዕከል ነው።

አለርት ሆስፒታል ሪፈራል ሆስፒታል እንደመሆኑ ከአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ አካባቢዎችና ከከተማዋ ዙሪያ ከሚገኙ ቦታዎች የሕክምና አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ በርካታ ታካሚዎችን ያስተናግዳል። እየሰጣቸው ካሉ የሕክምና አገልግሎቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ የዓይን ሕክምና ቢሆንም በአብዛኛው ትኩረት አድርጎ ሲሠራ የቆየው በአዋቂ የዓይን ሕክምና አገልግሎት ላይ ነው። ይሁንና አሁን ለመገንባት ያሰበው የሕፃናት ዓይን ሕክምና ማዕከል ሥራ ሲጀምር ቀደም ሲል ይታይ የነበረውን የሕፃናት ዓይን ሕክምና ችግር በመጠኑን ቢሆን ይቀርፈዋል ተብሎ ይታሰባል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ ለዓይን ሕክምና ማዕከል ግንባታው 60 ሚሊዮን ብር የተመደበ ሲሆን ሙሉ ወጪው ሲቢ ኤም (ክርስቲያን ብላይንድ ሚሽን) በተሰኘው የጀርመን ተራድኦ ድርጅት ይሸፈናል። የማዕከሉ ግንባታ ተጠናቆ ወደ ሥራ ለማስገባትም ሁለት አመታትን ይፈጃል።

ማዕከሉ ተጠናቆ ሥራውን ሲጀምር በውስጡ አስተኝቶ ማከሚያ አልጋዎች፣ መመርመሪያ ክፍሎች፣ የቀዶ ሕክምና፣ የማስተማሪያ ክፍሎች፣ የሕፃናት ማቆያ ክፍሎች፣ ልዩ ልዩ ቢሮዎችና የመጫዎቻ ስፍራዎች ይኖሩታል። ይህም አለርት ሆስፒታል ወደ ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለማደግና የዓይን ስፔሽያሊስት ሀኪሞችን በቀጣይ እዚያው ለማሰልጠን የያዘውን ግብ የሚደግፍ ነው።

ማዕከሉ በቀን 30 ያህል ሕፃናትን የማከም አቅም ያለው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ፐርሰናል አይ ኤግዛሚኔሽን ኪት /PEEK/ በተሰኘውና በስማርት ስልክ መተግበሪያ አማካኝነት በትምህርት ቤቶች የዓይን ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የመለየትና የመነፅር አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ዘዴ

**ከዚህ በተጓዳኝ የማይተላለፉ የዓይን ህመሞች በተለይ ደግሞ ከዕድሜ መግፋት ጋር በተያያዘ ከሚመጡት ውስጥ አንዱ የሆነው ካታራክት ወይም የዓይን ሞራ ግርዶሽ በሕክምና የሚስተካከል ቢሆንም 49 ከመቶ ያህሉን የኅብረተሰብ ክፍል የዓይን ብርሃናቸውን እንዲያጡ ምክንያት እየሆነ መጥቷል**



በቀጣይ በሆስፒታሉ የሚገነባው የማዕከሉ ሕንፃ ዲዛይን፤

የሕክምና አቅሙን ከፍ እንዲያደርግ ያስችለዋል።

ምንም እንኳን የዓይን ሕክምና ማዕከሉ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ አገልግሎቱን ለሕፃናት በነፃ የሚሰጥ ቢሆንም ሀገሪቱ በቂ በጀት ሊኖራት ስለማይችልና በረጂ ድርጅቶች ላይ ብቻ መንጠልጠል ስለማይቻል በነፃ ሕክምና ብቻ የሚቀጥል አይደለም። ከዚህ አኳያ ለወደፊቱ ያለውን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ለሁሉም ሕፃናት ተደራሽ በሆነና በተመጣጣኝ ዋጋ የሕፃናት የዓይን ሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ስልት ከወዲሁ መቀየስ ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ ለዚህ የሕዝብ ቁጥር ሊመጥኑ የሚችሉ የዓይን ሕክምና ማዕከላትን ከስር ከስር መገንባት ያስፈልጋል። በዓይን ሕክምና ዘርፍ የሚሰለጥኑ ባለሞያዎችን ቁጥርም ማሳደግ ይገባል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ችግሩ እየሰፋ ይሄዳል። ስለዚህ አለርት ሆስፒታል ለመገንባት ያሰበው የሕፃናት ዓይን ሕክምና ማዕከል በሕፃናት የዓይን ሕክምና በኩል የሚታየውን ችግር በመጠኑ እንጂ ሙሉ በሙሉ ሊቀርፍ አይችልም።

በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ሕይወት ሰለሞን እንደሚናገሩት፤ የዓይን ሕክምና አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ከመጀመሪያ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ያላቸው ተቋማት አሉ። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ቁጥር አንፃር ያለው የዓይን ሕክምና አገልግሎት በቂ ነው ማለት አይቻልም። ሆኖም የዓይን ሕክምና አገልግሎቱን ለማስፋት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አሉ።

በዋናነትም በዝቅተኛ ደረጃ አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው የመጀመሪያ የጤና አገልግሎት መስጫ አሃድ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተለይ ደግሞ በቀላሉ ሊመረመሩና እዚያው በጤና ጣቢያ እና በሆስፒታል ደረጃ ሊታከሙ በሚችሉ የዓይን ሕክምና አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው።በተጨማሪም ወደ ኅብረተሰቡ በመቅረብ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና ከሌሎች ሴክተር መስሪያቤቶች በተለይም ከትምህርት ሴክተር ጋር በመሆን የሚሠሩ ሥራዎችም አሉ። ይህንንም በቀጣይ ለማስፋት ታስቧል።

በተለይ ደግሞ ሕፃናትን በትምህርት ቤት ደረጃ ለመምህራን ግንዛቤ በመፍጠር የዓይን ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካጋጠሟቸው በሚሰጣቸው ሥልጠና መሠረት ወደ ጤና ተቋማት እንዲሄዱ ምክር እንዲለግሷቸው ወላጆቻቸውንም እንዲያማክሯቸው ይደረጋል። ይህንን በማድረግ በርካታ የዓይን ጤና ችግር ያለባቸውን ታዳጊ ሕፃናትን ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ የዓይን ምርመራ ተደርጎላቸው አስፈላጊው ሕክምና እንዲያገኙ ተደርጓል። መነፅር ለሚያስፈልጋቸውም እገዛ ተደርጎላቸዋል። ነገር ግን ካለው ችግር አኳያ ይህ ገና ጅማሬ በመሆኑ በቀጣይ ገና ሰፊ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጎን ለጎን በሁለተኛ ደረጃ አገልግሎት የሚሰጡ የዓይን ጤና ተቋማትን የማስፋት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። እንዲሁም በስፔሻላይዝድ ደረጃ የሕክምና አገልግሎትን ለማስፋት በከፍተኛ ደረጃ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ይህ በብዛት በመንግሥት ጤና ተቋማት ላይ እየተሠራ ቢሆንም ከቁጥር አንፃር አሁንም ውስንነቶች ይታያሉ። ስለዚህ የግሉ ጤና ተቋማት በዚህ ላይ በስፋት እንዲገቡና የሕፃናት ዓይን ሕክምና አገልግሎትን ተደራሽ እንዲደርጉ በቅንጅት ሥራዎች የሚሠሩ ይሆናል።

በሌላ በኩል ጤና ሚኒስቴር በዓይን ሕክምና ላይ የሚሠሩ የተለያዩ አጋር ድርጅቶች የዓይን ጤና ሀገር አቀፍ ስትራቴጂን መሠረት አድርገው እንዲሠሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ሥራዎችንም በየጊዜው ይፈትሻል። አገልግሎቱን ተደራሽ የማድረግና የመሳሰሉትን ሥራዎችንም ከነዚህ አጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሠራል።

እንደ መሪ አስፈፃሚዋ ገለፃ አብዛኛዎቹ የዓይን ሕክምና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በአብዛኛው በትላልቅ የሀገሪቱ ከተሞች ላይ የሚገኙ እንደመሆናቸው በመጀመሪያ ደረጃ ዓይን ሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የማስፋት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተመሳሳይ በሁለተኛ ደረጃ አሃድ የሚሰጡ የዓይን ሕክምና አገልግሎት መስጫዎችን ተዳራሽ የማድረግ ሥራዎችም አብረው እየተሠሩ ነው።

ይሁን እንጂ ኅብረተሰቡ ሌሎች ትልልቅ ሆስፒታሎች ከመሄድ ይልቅ የዓይን ሕክምና አገልግሎቱ በመጀመሪያ ሕክምና መስጫ ተቋማት ውስጥ እንዳለ ተረድቶ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ግንዛቤውን የማስፋት ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል። ኅብረተሰቡን ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱ በሚሰጥባቸው ጤና ተቋማት ላይ ያሉ ባለሞያዎችም በተመሳሳይ ግንዛቤውን እንዲያሰፉ የማድረግ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቃል።

ከዚህ ባለፈ የዓይን ህመም በርካታ እንደመሆኑ በተለይ ተላላፊ ከሆኑት የዓይን ህመሞች ውስጥ አንዱ የሆነውን የዓይን ማዝ ወይም ትራኮማ ህመምን እንደሀገር ለማጥፋት እቅድ ተይዞ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ህመሙን ለማጥፋት ደግሞ በጤና ተቋማት የሚሰጡ የሕክምና አገልግሎቶች ብቻ በቂ አይደሉም።ከዚህ አኳያ ንፁህ የውሃ አቅርቦት፣ የግልና የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ፣ የባህሪይ ለውጥ ማምጣትና በዚህ ላይ በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል። ከዚሁ ጎን ለጎን ግንዛቤ መፍጠርና የሕክምና አገልግሎቱን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ይገባል። በተጨማሪም በየዓመቱ በተለይ ደግሞ የዓይን ህመም ለገጠማቸው ታዳጊ ሕፃናት የሚደረገውን የመድኃኒት እደላ መጨመር የግድ ይላል። የዓይን ቆብ መቀልበስ ችግር ያለባቸውን ደግሞ በመደበኛና በዘመቻ የቀዶ ሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል። በየአመቱም እስከ 80 ሺ የሚጠጉ ታዳጊዎች የዚሁ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

ከዚህ በተጓዳኝ የማይተላለፉ የዓይን ህመሞች በተለይ ደግሞ ከዕድሜ መግፋት ጋር በተያያዘ ከሚመጡት ውስጥ አንዱ የሆነው ካታራክት ወይም የዓይን ሞራ ግርዶሽ በሕክምና የሚስተካከል ቢሆንም 49 ከመቶ ያህሉን የኅብረተሰብ ክፍል የዓይን ብርሃናቸውን እንዲያጡ ምክንያት እየሆነ መጥቷል። ይህንም በመደበኛና ከመደበኛ ውጪ በሆኑ የሕክምና ሥራዎች ችግሩን የመቅረፍ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ይሁንና አሁንም ከችግሩ ስፋትና ከኅብረተሰቡ ቁጥር አንፃር እየተከናወነ ያለው ሥራና እየተሰጠ ያለው የሕክምና አገልግሎት በቂ አይደለም።

በአለርት ማዕከል ለመገንባት የታሰበው የሕፃናት ዓይን ሕክምና ማዕከልም በተለይ አገልግሎቱን ለሕፃናት ተደራሽ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት አንዱ አካል ነው። እንደ አዋቂዎቹ ሁሉ ሕፃናትም የዓይን ጤና ችግር ሲያጋጥማቸው አስፈላጊውን ምርመራና ሕክምና ሊደረግላቸው ይገባል። ለሕፃናት የሚደረገው የዓይን ሕክምና አገልግሎትም የባለሞያዎችን ልምድና ክህሎትን ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር ምንም እንኳን በሕፃናት ዓይን ሕክምና ላይ አተኩረው የሚሠሩ የግል ጤና ተቋማት ቢኖሩም የተወሰኑ የመንግሥት ተቋማትም አገልግሎቱን ይሰጣሉ።

በከፍተኛ ደረጃ የዓይን ሕክምናን ከሚሠሩ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል። በተመሳሳይ በክልል የጅማ ዩኒቨርሲቲም ሊጠቀስ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪም አለርት ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የዓይን ሕክምና አገልግሎት ከሚሰጥባቸው የጤና ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው። በዚሁ ሆስፒታል ለመገንባት የታሰበው የሕፃናት ዓይን ሕክምና ማዕከል ለሕፃናት የዓይን ሕክምና አገልግሎት ተዳራሽነት ለማስፋት እየተደረገ ያለውን ጥረት ያግዛል። ማዕከሉ የመማሪያ ክፍሎችም የሚኖሩት በመሆኑ የባለሞያዎችን አቅም ከመገንባት አኳያም ያራሱ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

# ነፃ ሃሳብ

# ስለመውጫ ፈተናው ውጤትም ደህንነትም

**ታምራት ተስፋዬ**

አንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትን በማምጣት የሕዝቦቿን ኑሮ ማሳደግ የምትችለው በሚኖራት የሰው ኃይል አቅም ነው፡፡ ስኬትና ኪሳራን የምታወራርደው ባለመቻቸው፣ እልምታም ባበቃቸው ትውልድ ነው። ትምህርት ደግሞ ይሕን ትውልድ እውን ለማድረግና ለአንድ አገር እድገት መሰረት፣ ዋልታና ማገር ነው።

ስለ ትምህርት ሲነሳ ብዙዎች እንደ ማሳያ የሚጠቀሙበት የደቡብ አፍሪካ የነፃነት ምልክት ኔልሰን ማንዴላ ‹‹ትምህርት ዓለምን ለመለወጥ ልትጠቀምበት የምትችለው በጣም ኃይለኛ መሣሪያ ነው ” የሚለው ንግግራቸው ሁሌም ተጠቃሽ ነው፡፡

አገር በትምህርት ውስጥ የሚያልፉ ዜጎቿ በጨመሩ ቁጥር፣ ምክንያታዊ ትውልድን እያፈራች እድገትና ልማቷን የማፋጠን እድሏ እየጨመረ ይሄዳል። እነዚህ ዜጎቿ ችግሯን የሚሸሹ፣ ሲከፋም ችግር የሚፈጥሩባት ሳይሆን በቅርብ ሆነው መፍትሄ የሚሰጡና የችግርን መፍቻ ቁልፍ የታጠቁ ናቸው። ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን ዜጎች ለአገር ሸክም ይሆናሉ። የተሠራን የሚያጠፉና የሚያወድም ትውልድም ይፈጠራል። ለዚህ ታዲያ ቁልፍ መሠረቱ የትምህርት ሥርዓት ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃም በርካታ አገራት ለትምህርት ዘርፍ በሠጡት ትኩረት የድካማቸውን ፍሬ መልቀም ችለዋል፡፡ ለትምህርት ዘርፍ ትኩረት በመስጠት ረገድ በተለይ ጥራትን ማስጠበቅና የተደራሽነቱን ማስፋትም የአገርን እድገት አንድ እርምጃ ወደፊት ለማስቀጠል እጅግ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም።

ኢትዮጵያም ከትላንት እስዛሬ የትምህርት ፋይዳ የገባት ‹‹መማር ያስከብራል፤ አገርን ያኮራል›› የሚለው ብሂል፤ ትምህርት ለግል አእምሮአዊ እድገት ብቻ ሳይሆን ለአገርም ምን ያህል ፋይዳ እንዳለው የሚገለፅባት ከፍ ሲል የሚዘመርባት አገር ናት፡፡

በኢትዮጵያ በቀደሙት ዓመታትም በመንግሥት ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው ዘርፎች መካከል ትምህርት በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል፡፡ በሁሉም ደረጃ የትምህርት ተደራሽነቱን ላይ በጎና ሰፊ ስራ ተሰርቷል። ይሑንናን ብዛት ሳይሆን ጥራት ሲጠየቅ መልሱ ቀላል አልነበረም፡፡

የትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት በሚል በሚከናወኑ ተግባራት የትምህርት አቅርቦቱ ሊያድግ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ጎን ለጎን የጥራቱን ጉዳይ ታሳቢ ያደረገ መንገድ ካልተከተሉ ዞሮ ዞሮ አተርፍ ባይ አጉዳይ ሆኖ መቅረት የማይቀር ነው፡፡

ኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓቱ ብዛትን ተከትሎ የጥራትን መንገድ በመሳቱ፤ በብርቱ ሲታመም እና ሲሰቃይ ቆይቷል፡፡ በየትምህርት ስርዓት ላይ ለሚታየው ስብራት በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በቀደሙት ዓመታት ለትምህርት ስርአቱ ሞት በተለይም ለጥራቱ ዝቅጠት ግንባር ቀደም መንስኤዎች ተብለው ከተለዩት ምክንያቶች አንዱም የፈተና ሂደት ከዝግጅት እስከ ስርጭት ደካማ መሆን በቀዳሚነት ይነሳል፡፡

እንደሚታወቀው ትምህርት የነገ የአገር ተስፋ የሆኑ ተማሪዎችን በእውቀት፣ አመለካከትና ሥነምግባር ቀርጾ የማውጣት ቁልፍ ሲሆን ፈተና ደግሞ የዕውቀት መለኪያ ነው። ፈተና ተማሪዎች በትምህርት ወቅት በገበዩአቸው እውቀቶች ልክ የሚፈተሹበትና የሚለኩበት ሚዛን ነው።

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በፈተና አሰጣጥ ሂደት በሚስተዋሉ ድክመቶች ተማሪዎች በተደራጀ ሁኔታ ኩረጃ ላይ ሲተጉ ይስተዋላል። ኩረጃ በዕለት ተዕለት የትምህርት ስርዓት ወቅት የሚያጋጥም ቢሆንም በተለይ በብሔራዊ ፈተናዎች ላይ የሚከወንበት መንገድ ዘመን ባመጣው ቴክኖሎጂ የተደፈገ መሆኑ ኪሳራውን ከፍ አድርጎታል።

ኩረጃው በተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በፈተና ጣቢያ አስተባባሪዎች፣ በፈታኝ መምህራን፣ በመስተዳድር ኃላፊዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በተለይም ስማቸውን በመሸጥ ጥሩ ገቢ ለማግኘት በሚጥሩ ትምህርት ቤቶችም ጭምር መቀነባበሩም

**እውቀት፣ ክህሎት፣ የስራ አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ ቆብ መጫንና ምስክር ወረቀትን መያዝ ቀዳሚ ምርጫ ያደረገ ትውልድ እንዲሁም ከጥራት ይልቅ ብቃትን በማስቀደም በርካቶችም« ማስመረቅ» ቻልኩኝ በሚል የሚኮፈሱ የትምህርት ተቋማት እንዲበራከት አድርጓል**



የኢትዮጵያን የትምህርት ስርአት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎት ቆይቷል። በመንግስት በኩል ችግሩን ለመከላከል ለተከታታይ ዓመታት የተለያዩ ተግባራት ቢከናወኑም ውጤታማ መሆን ግን አልተቻለም።

ይህም ድክመትም እንደ አገር የትምህርት ስርአቱን አከራካሪ ሲሰባብረው ቆይቷል፡፡ ችግሩም በተማሪዎች ከራስ ጥረትና ልፋት ይልቅ በሌሎች ትከሻ ወረቀትን ለማግኘት እንዲተጉ፣ እውቀትን ከመሸመት ይልቅ ኩረጃን እንደ አቋራጭ መንገድ መጠቀምን ቀዳሚ ምርጫ እንዲያደርጉም ምክንያት ሆኖ ታይቷል፡፡

ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባሉት የትምህርት እርከኖች ተማሪዎች ‹‹ባናጠናም እናልፋለን›› የሚል አስተሳሰብ እንዲዳብርና ሳይዘጋጁ ለፈተና መቅረብ የተለመደ እንዲሆን አድርጎትም ቆይቷል፡፡ የፈተናው አሰጣጥና ውጤት ጥራት ደካማ በመሆኑም በተለይ የመሰናዶ ተማሪዎች በሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበት አሳፋሪ ሁኔታን ፈጥሯል።

እውቀት፣ ክህሎት፣ የስራ አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ ቆብ መጫንና ምስክር ወረቀትን መያዝ ቀዳሚ ምርጫ ያደረገ ትውልድ እንዲሁም ከጥራት ይልቅ ብቃትን በማስቀደም በርካቶችም‹‹ ማስመረቅ››ቻልኩኝ በሚል የሚኮፈሱ የትምህርት ተቋማት እንዲበራከት አድርጓል፡፡ የአገሪቱ የትምህርት ዘርፍ የገባበትን ገደል ጥልቀት ለመረዳት ደግሞ ብዙ ርቀትን መመለስ ሳይፈልግ የቅርቡን የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና አስደንጋጭ ውጤት ማስታወስ በቂ ነው፡፡

የወቅቱ መንግስትም ይህን የትምህርት ዘርፍ ስብራት በመረዳት የዘርፉን ችግር ያስቀራል የተባሉት ማሻሻያዎችን ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ሲከውን ቆይቷል፡፡ የትምህርትና የሥልጠና ፍኖተ ካርታ ከማዘጋጀት ጀምሮ አዳዲስ አሠራሮችን አስተዋውቋል፡፡ አዳዲስ አሰራሮች ከተተገበሩባቸው መካከል ደግሞ የፈተና አሰጣጥ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። ባለፉት ጊዜያትም የፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱን ከማሻሻል ጀምሮ ሌሎች አቋራጭ መንገዶችን ለመዝጋት የሚያስችሉ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ተግባራት አንዱም የመውጫ ፈተና ነው፡፡

በአዲስ ፍኖተ ካርታም ወደ ተቋማቱ የሚገቡትን ብቻ ሳይሆን አጠናቀው የሚወጡትም የሥራ ገበያውን ከመቀላቀላቸው በፊት ብቃታቸው መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ትምህርት ሚኒስቴርም ከአንድ ዓመት በፊት የዩኒቨርሲቲ የመውጫ ፈተና በሁሉም የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚሰጥ ውሳኔን አሳልፋል፡፡ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናውንም ከቀናት በኋላ መሰጠቱ እርግጥ ሆኗል።

በአሁን ወቅትም ሁሉም በየፊናው ለፈተናው ስኬትና ያማረ ውጤት እየተጋ ይገኛል፡፡ የተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ተማሪዎቻቸው ለመውጫ ፈተናው ብቁ እንዲሆኑ እየተጉ ናቸው፡፡ የመንግስትን ውሳኔ በመቀበል የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት በልዩ ትኩረት ተማሪዎችን ከማብቃትና ከማዘጋጀት አንፃር ሰፊ ስራዎች እየሰሩም ናቸው፡፡

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ከሰሞኑ ለስራ በተንቀሳቀሰባቸው ዩኒቨርሲቲዎች፣ ፈተናው በትምህርት ጥራት እንዲሁም ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ከማፍራት አንፃር ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ ታሳቢ ባደረገ መልኩም ከተማሪዎች፣ ከመምህራን፣ ከአመራሮችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት ጋር በቅርበት እየሰሩ መሆኑን መታዘብ ችላል፡፡ ስለ ፈተናዉ መረጃና ግንዛቤ የመስጠት፣ ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን የመለየት፣ ቲቶሪያል ትምህርት የመስጠትና ለዘርፉ አጋዥ የሆኑ ሞጁሎችን እና መጽሐፍቶችን እንዲሁም ሞዴል ፈተናዎችን የማዘጋጀት ተግባራት በስፋት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በእርግጥ የትምህርት ጥራትን የሚያረጋግጠው የመውጫ ፈተና ብቻ አይደለም፡፡ ይሑንና የመውጫ ፈተና ወደ ትምህርት ጥራት የሚደረገውን ጉዞ ምቹ ከሚያደርጉ መደላድሎች በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ የመንግስት የለውጥ ጉዞ እርምጃውም ኢትዮጵያ በቂ የተማረ እና ለውጥ የሚያመጣ ትውልድን እንድታገኝ ትልቅ አቅም የሚሰጥ ነው፡፡ መሰል አሰራር በስርቆት መተማመንም ሙሉ በሙሉ ያስቀራል፡፡ ከስርቆት ይልቅ በራሱ አቅም የሚተማመንና በእውቀት የላቀ ትውልድን ለመፍጠር አቅም ይፈጥራል፡፡

የመውጫ ፈተናው ቀጥታ ውጤት የተማሪው ሊሆን ይችላል፡፡ በተዘዋዋሪ ግን የመምህሩ፣ የትምህርት ክፍሉ፣ የኮሌጁና የዩኒቨርሲቲው አጠቃላይ ውጤት ነው፡፡ የመውጫ ፈተናው በተለይ በአገሪቱ ትምህርት ጥራት ላይ የሚኖረው አስተዋፅኦ ነጋሪ አያሻውም፡፡ ይሕ ማለት ግን ውጤቱ ወዲያው ይታያል ማለት አይደለም፡፡ ፈተናው መኖሩ በመታወቁ ብቻ ከዚህ በኋላ ሁሉም ዩኒቨርሲቲም፣ አስተማሪም ሆነ ተማሪ መማር ማስተማርን በልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ እንዲመለከቱ ያስገድዳል፡፡

መውጫ ፈተና በተለይም ለዩኒቨርሲቲዎች የህልውና ጉዳይ ነው፡፡ ለዩኒቨርሲቲዎች ሁለት እድልን ሰጥቶ ያልፋል፡፡ በርካታ ተማሪዎች ማሳለፍ ያልቻለ ዩኒቨርሲቲ ራሱን እንዲፈትሽ እንዲሁም በሚመለከታቸው አካላት ፍተሻ እንዲደረግበት ያስችላል፡፡

ተማሪዎቹም ለሀገር አቀፋዊ ፈተናው የሚሆን ዝግጅት እያደረጉ ናቸው፡፡ መምህራኖቻቸውም የተመረጡ የትኩረት መስኮች ዙሪያ የተለያዩ ግንዛቤን በማስጨበጥና ትቶሪያል ትምህርቶችን በመስጠት እገዛ ማድረጋቸው አላቋረጡም፡፡ ይሑንና በአንዳንድ ተማሪዎች ዘንድ የመውጫ ፈተና አቅሎም፣ አክብዶም የመመልከት እሳቤ ማስተዋል ተችሏል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎቹም የመውጫ ፈተናውን በስኬት ለመወጣት ተማሪዎች ከመሰል የተሳሳተ እሳቤ እንዲታረሙ በተለይ ስነ ልቦና ዝግጁነት ላይ ሰፊ የምክርና ድጋፍ ስራዎች ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡ መውጫ ፈተና እንደሚሰጥ ከተነገራቸው ግዜ ጀምሮ አስፈላጊውን ሁሉ ዝግጅት ሲያደርጉ የቆዩ ተማሪዎች ቢሆን ከየዩኒቨርሲቲዎቻቸው ባገኙት ድጋፍ እጅጉን ደስተኛ ስለመሆናቸው በተግባራቸው ብቻ ሳይሆን በአንደበታቸው ሲመሰክሩም መታዘብ ችለናል፡፡

የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ.... እንደሚባለው የተከናወኑ ተግባራት ፈተናው ውጤታማ ለማድረግ አቅም የሚፈጥሩ መሆናቸውም የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ ተፈታኝ ተማሪዎችም ስለ መውጫ ፈተናው አዎንታዊ እንጂ አሉታዊ አመለካከት እንደማይኖራቸው፣ ፈናውን በብቃት እንደሚወጡ በልበ ሙሉነት የሚናገሩ እንጂ ፍርሃት ያሸመደመዳቸው ማግኘት ከባድ መሆኑም እርግጥ ነው፡፡

ምንም እንኳን ባለፉት ወራት በተከናወኑ ተግባራት የመውጫ ፈተናውን ውጤታማ በሆነ መልኩ መወጣት እንደሚቻል ቢታመንም የፈተናው ሂደት ሙሉ በሙሉ ከስጋት ነፃ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ በተለይ የኔትወርክና የመብራት መቆራረጥ ችግር የፈተናው አሰጣጡ ሂደት ላይ እክል እንዳይፈጥር ያሰጋል፡፡ መሰል ችግሮች ለአንድና ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ሳይሆን ለበርካቶች ስጋት ሊሆኑ ስለሚችሉ ከወዲሁ የሚመለከታቸው አካላት መፍትሄው ላይ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ከሰሞኑ ለስራ በተንቀሳቀሰባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ምንም እንኳን ተማሪዎች በዝግጅትም ሆነ በስነልቦና ጠንካራ ሆነው መውጣት ቢችሉም አንዳንዶች በአንጻሩ ፈተናውን የተመለከቱበት የፍርሃት መነፅር አሁንም ድረስ አለመጠረጉ በግልፅ ማስተዋል ችሏል፡፡ የመውጫው ፈተናው ውጤት የተማሪዎቹን ቀጣይ ሕይወት የሚወስን እንደመሆኑ ስነልቦናዊ ጫና እንደፈጠረባቸው በገፅታቸው ላይ የሚነበብ ብቻ አይደለም፡፡ በአንደበታቸው ጭምር የሚገለፅ ነው፡፡ ማናቸውም ተማሪዎች ዘንድ የሚስተዋል ጭንቀት እና ስጋት ደግሞ ምናልባትም ከፍ ሲል ነገሮች ባልተፈለገ አቅጣጫ ሊወስዳቸው የሚችልበት እድል የለም ለማለት አያስደፍርም፡፡

በተለይ በቂ ዝግጅት ያላደረጉ ተማሪዎች ውዥንብር በመፍጠር ፈተናውን ለማደናቀፍ ያልተገባ ሙከራ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ዝግጅትም አስፈላጊ ስለመሆኑ ይሰማኛል። የመውጫ ፈተናውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ብቻም ሳይሆን ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንዲጠናቀቅ ማድረግ እጅጉን ወሳኝ ነው፡፡

ለትምህርት ጥራት የሚገቡትን ብቻም ሳይሆን የሚወጡትንም ለማጥራት የሚከናወኑ ተግባራት በሚፈለገው ልክ ውጤታማ ለመሆን ተማሪዎችም የመውጫ ፈተናውን ሁለንተናዊ ጥቅም ጠንቅቀው መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ በተዛባ አስተሳሰብ ራሳቸውን ሳያስጨንቁና ሳይረብሹ በተረጋጋ መንፈስ ፈተናው ላይ ብቻ ትኩረት ሊያደርጉም ይገባል፡፡

ዩኒቨርሲቲውንም ሆነ ራሳቸውን በውጤታማነትን ብሎም በሰላማዊነት ማስጠራትን ቀዳሚ ምርጫ ማድረግም ይኖርባቸዋል፡፡ መሰል ለትምህርት ጥራት ወወደ ዩንቨርሲቲ የሚገቡትን ብቻ ሳይሆን የሚወጡትንም የማጥራት ተግባር፤ ሀገር ለማዳን ከሚከፈል መስዋዕትነት እኩል ሊታዩ የሚገባው፤ የትምህርት ስርአቱ ከወደቀበት ለማንሳት ትልቅ አቅም የሚሆን ነው። ከዚህ የተነሳ ለመውጫ ፈተናው ውጤታማነት ሁሉም ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

## የጥንዶቹ የጭካኔ በትር!

**ሶሎሞን በየነ**

አቶ ልጅዓለም ጌታቸው እና ወይዘሮ ቆንጅት ሙሉታ በ2011 ዓ.ም ሶስት ጉልቻ ቀለሱ። ትዳራቸው በአንድ ጣሪያ ሥር መድመቁ ቀጠለ። ሁለት ልጆችን አፈሩ። አቶ ልጅዓለም የአክስቱ ልጅ የሆነችውን አስቴር ነገሳን ገና እድሜዋ 10 ዓመት ሳይሞላ፤ ከወለጋ ክፍለ ሀገር "እኔ ላሳድጋት" ብሎ አክስቱን ወይዘሮ አድስ ታዬን አስፈቅዶ ወደ አዲስ አበባ ይዟት መጣ። ከእነርሱ ጋር መኖር ጀመረች፤ እንደዋዛ ዓመታት ነጎዱ።

አስቴር አንድ ፍሬ ልጅ ለራሷ ገና ሳታድግና ጉልበቷ ሳይጠና እጣፈንታዋ ልጆች አሳዳጊነት ሆነ። ወደ አዲስ አበባ መጥታ መኖር ከጀመረች ዓመታት ቢያልፉም የተሻለ ኑሮ እና የትምህርት እድል አልገጠማትም። ልጅ አሳዳጊ ሆና የነገ ተስፋዋም ጨልሞ በሰላም እንድትኖር አልተፈቀደላትም። የቤት እመቤቷ ወይዘሮ ቆንጂት ውሃ ቀጠነ በሚል ሰበብ በማገዶ ፍልጥ እንጨት እያገላበጠች ትቀጠቅጣታለች፤ ትወግራታለች።

"ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ ይቀዳሉ" እንዲሉ፤ አባወራው አቶ ልጅዓለም ባለቤቱን "ተይ! ልጅ በምክር እንጂ በዱላ አይታረቅም" ብሎ መምከር ሲገባው በተመሳሳይ መልኩ ባለቤቱ ስትቀጠቅጣት የዋለቻትን አንድ ፍሬ ልጅ እርሱ ደግሞ ማታ ሥራ ውሎ ሲገባ ተራውን ተቀብሎ ይቀጠቅጣታል። ይህቺን ለጋ ህፃን እንዲህ ባልና ሚስቱ እየተቀባበሉ ሲቀጠቅጧት ያዩ ጎረቤቶች "ኸረ ተው! ይቺ ልጅ እጃቹህ ላይ ሕይወቷ ያልፍባችኋል" በሚል ይገለግላሉ፤ ይመክራሉ።

"ልጄን ስገርፍ ተው ብሎ የገላገለኝ የልብ ወዳጄ ነው" ከሚለው የሀገሬው ብሂል በተቃራኒው በተለይ ወይዘሮ ቆንጅት ልጅቷን ስትገርፍ "ተይ አትምቻት" ብሎ የገላገላትና የመከራትን ሰው እንደ ጠላት ማየት ጀመረች። ለእርሷ ብለው የመከሯትን ጎረቤቶቿን እላፊ ቃላት ከመናገር አልፎ ተርፎም ወደ ጥል ለማምራት ይቃጣት ጀመር። ይህኔ ጎረቤቱ ልጅቷ ጠዋት እና ማታ እንደ እባብ እየተቀጠቀጠች እያዩ ልባቸው ቢያዝንም "ተው አትምቷት" ብሎ መናገር ሌላ መዘዝ የሚያስከትል በመሆኑ ሁኔታውን በዝምታ መከታተል ጀመሩ።

ባልና ሚስቱ ልጅቷን ሲገርፉ "ተዉ አትምቷት" ብሎ የሚገላግልና የሚመክር ሰው ሲጠፋ ጭራሽ ነጋ ጠባ አንዴ በማገዶ ፍልጥ እንጨት፣ በሶኬት (በኤሌክትሪክ ሽቦ)፣ በጎማና በውሃ ማስተላለፊያ የፕላስቲክ ቱቦ መቀጥቀጡን ተያያዙት። በዚህም የልጅቷ ገላ ላይ ዱላ ያላረፈበት የሰውነት ክፍል አካል ፈልጎ ማግኘት ከባድ ሆነ።

ልጅቷ በደረሰባት ድብደባ በተለይ እጇ ዝሎ እንደፈለገች እጇቿን ለማዘዝ ቢሳናትም በደመነፍስም ቢሆን የሚያዟትን ለመሥራት ተገደደች። ያቅሟን ለመሥራት ደፋ ቀና ትላላች። ባልና ሚስት ግን አስቴር በደረሰባት ድብደባ አካሏ ዝሎ ተዳክማ እያዩዋት ልባቸው አይራራም። ወደ ሀኪም ቤት ወስደው ሊያሳክሟትም አልፈቀዱም።

በተለይ ወይዘሮ ቆንጅት በጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም "ወተት ሰረቅሽኝ" በሚል ሰበብ እንደለመደችው ህጻኗ አስቴርን ኩሽና አስገብታ ትደበድባት ጀመር። ይህኔ በጣም ዱላው የበረታባትን ህጻን ሲቃ ሰምቶ እንዳልሰሙ መሆን ያቃታቸው ጎረቤት ወይዘሮ በቀሉ ሸዋዬ፤ በአጥር ብቅ ብለው ለምን ትመቻታለሽ ይሏታል። "ወተት ሥርቃኝ ነው" ብላ መልስ ትሰጣለች። ወተት ሰረቀችኝ ብለሽ ከምትደበድቢያት ለምን መጀመሪያ አጥግበሽ አታበያትም ይሏታል።

ይህኔ ወይዘሮ ቆንጅት ልጅቷ ውጭ እንደወደቀች ልጅቷን ስትገርፍበት የነበረውን የፍልጥ እንጨት አሽቀንጥራ ጥላ ወደ ቤት ገባች። ህጻኗ አስቴር ግን ከወደቀችበት ለመነሳት አቃታት። ጉልበቷ ቄጠማ ሆነባት። በዚያው አፈር ላይ እንደወደቀች ሰዓታትን ቆየች። ከምሽቱ 1:00 ሰዓት ገደማ ሲሆን፤ አንድ



ግቢ ውስጥ የሚኖሩ ጎረቤት ወይዘሮ ፀሐይ አገዘ ከሥራ ውለው ወደ ቤታቸው ሲገቡ፤ ከወደቀችበት መነሳት ያቃታት አስቴርን አንስተው ወደ ቤት እንዲያስገቧት ተማጸኑ። ምላሽ ሲያጡ፤ ነገሩ ሌላ እንዳይተረጎምባቸው "ወደ ቤት ላስገባት ወይ" ብለው ወይዘሮ ቆንጅትን ጠየቁ። ወይዘሮ ቆንጅት ግን ህጻኗን "መነሳት ትችያለሽ ለምን አትነሺም" ብላ በፍልጥ እንጨት መሃል ወገቧን ከወደቀችበት ሁለት ጊዜ መታቻት። ይህኔ ወይዘሮ ፀሐይ የልጅቷን ስቃይ ከማይ ብለው ትተው ወደ ቤታቸው ገቡ።

ታዲያ አንድ ቀን እንደልጅ ሳትቦርቅ፣ ከእኩዮቿ ጋር ስቃ ሳትጫዎት እንዲህ ጠዋት ማታ ዱላ የበዛባት አስቴር በዚሁ ዕለት ምሽት 2:00 ሰዓት ሲል በደረሰባት ድብደባ ሕይወቷ አለፈ። ባልና ሚስቱ ግን አስቴር ሕይወቷ ማለፏን ለማንም ትንፍሽ አላሉም። እንደልጅ ሊያሳድጓት ያመጧት አንድ ፍሬ ልጅ ሕይወቷ ሲያልፍ አላለቀሱም፤ ጎረቤትም አልጠሩም። ይልቁንም የሬሳ ሳጥን ገዝተው አስከሬኑን በሳጥን ውስጥ አድርገው በድብቅ ሊቀብሩ ሲሰናዱ በሁኔታው የተጠራጠሩ ጎረቤቶች ለፖሊስ ጥቆማ ያደርሳሉ።

ፖሊስም ጥቆማው እንደደረሰው በእግር በፈረስ ገስግሶ ባልና ሚስቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 11 ክልል ልዩ ቦታው ማንጎ ሰፈር አካባቢ ቤት ተከራይተው ከሚኖሩበት ቤት ሰተት ብሎ ሲገባ የሟች አስክሬን በሬሳ ሳጥን ውስጥ ገብቶ ተቀምጦ አገኘ። ፖሊስም በጥር 18 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ባልና ሚስቱን በቁጥጥር ሥር አውሎ፤ የተጠርጣሪዎቹን የእምነት ክህደት ቃል፣ የምስክሮችን ቃል፣ የሟች አስከሬን የህክምና ውጤትና የአማሟት ሁኔታዋን የሚያሳዩ ምስሎችና መረጃዎች አደራጅቶ ዐቃቢ ሕግ በተጠርጣሪዎች ላይ ክስ እንዲመሰርትባቸው መረጃውን አቀረበ።

### ጎረቤቶች ምን አሉ?

ከላይ በተጠቀሰው ቦታ በጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 12:00 ሰዓት ገደማ ወይዘሮ በቀሉ ሸዋዬ የተባሉት ግለሰብ፤ ከጎረቤቷ ወይዘሮ ጠጄ አስፋው ቤት እቃ ለመዋስ ያመራሉ። በወሬ ተነስቶ ወይዘሮ ጠጄ "እዚህ ግቢ ውስጥ ሁሌ የምትደበደብ ልጅ አለች" ብላ ለወይዘሮ በቀሉ ትነግራታለች። ጎረቤታማኞቹ ስለ ልጅቷ እያወሩ እያለ "ድው! ድው"! የሚል ድምጽ ሰምተው ወደ ውጭ ወጥተው በአጥር በኩል ሲያዩ፤ ወይዘሮ ቆንጂት የተባለችው ግለሰብ አስቴር ነገሳ የተባለችውን ሟች ህጻን ልጅ ኩሽና አስገብታ በፍልጥ ደጋግማ ስትደበድባት ያያሉ።

ይሔኔ ሲያዩ በአጥሩ ብቅ ብለው ልጅቷን የምትደበድበውን ግለሰብ ‹‹ለምን ትመቻታለሽ?›› ይሏታል። እሷም "ወተት ሰርቃኝ ነው" ብላ ትመልስላቸዋለች። "ምንሽ ናት?" ይሏታል ጎረቤታማኞቹ፤ "ልጄ ናት" ትላቸዋለች። ጎረቤታማኞቹም "ልጅሽማ አይደለችም፣ ልጅሽ ብትሆን እንደዚህ አትመቻትም" ይሏታል። እሷም መለስ ብላ "አይ የአክስቴ ልጅ ናት" ትላቸዋለች። ወይዘሮ በቀሉ "የአደራ ልጅ እንዲህ አይመታም። ወተት ለምን ሰረቅሽ ብለሽ ከምትመቻት አጥግበሽ ለምን አታበያትም? እንዲህ ካስቸገረችሽስ ለምን ወደ ቤተሰቦቿ አትሰጃትም?›› ይሏታል። እንዳልሰዳት "ጅማ መስመር መንገዱ ዝግ ነው" ብላ መልስ ስትሠጥ "ጅማ መንገዱ ሰላም ነው፤ ብር ከሌለሽ ከሰፈር አሰባስቤ አምጥቼ ልስጥሽ። ለፖሊስ አሳውቀሽ ለቤተሰቦቿ ደውለሽ አሳፍረሽ ላኪያት። ትሞትብሻለች በልጆችሽ ይዥሻለሁ አትምቻት" ብለው ወይዘሮ በቀሉ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ።

ወይዘሮ በቀሉ በቤታቸው አገር አማን ብለው በተኙበት በጥር 18 ቀን 2014 ዓ.ም ጠዋት 1:00 ሰዓት ላይ ጎረቤታቸው ወይዘሮ ጠጄ ከተፍ አሉ። "በጠዋት ምን እግር ጣለሽ ወይዘሮ ጠጄ" ሲሉ፤ የትናንትናይቱን ልጅ ገደሏት ብለው" ይነግሯቸዋል። ወይዘሮ በቀሉ ይህንን አስደንጋጭ ዜና ሲሰሙ እጃቸው ላይ የገባውን ነጠላ ቢጤ አፈፍ አድርገው ወደ ተጠርጣሪዎቹ ቤት ከወይዘሮ ጠጄ ጋር ተያይዘው እየተጣደፉ አመሩ። ወደ ተጠርጣሪዎቹ ቤት ሲገቡ የአስከሬን ሳጥን ቤቱ መሀል ላይ ተጎልቷል።

አቶ ልጅዓለምን "ምን ሆና ሞተች? ትናንት 12:00 ሰዓት ላይ አይተናታል" ሲሉት "ምሽት 2:00 ሰዓት ላይ ወድቃ ሞተች" ብሎ መልስ ይሰጣቸዋል። ከዚያ እነ ወይዘሮ በቀሉና ጠጄም "ምን ጭካኔ ነው! እሬሳ ታቅፋችሁ እንዴት አታለቅሱም? ጎረቤትስ ለምን አልጠራችሁም?" የሚል ጥያቄ ሲያነሱ አቶ ልጅዓለም የአክስቴ ልጅ ናት አያገባችሁም ከግቢው ለቃችሁ ውጡልኝ ብሎ ያስወጣቸዋል።

"ትናንት ባለቤቱ የአክስቴ ልጅናት አለች። ዛሬ ደግሞ አባወራው የአክስቴ ልጅ ናት አለን" ይሄ ነገር ሁኔታው አላማረንም" ይሉና እነ ወይዘሮ በቀሉና ጠጄ ደውለው ለፖሊስ ጥቆማ በማድረስ ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ያደርጋሉ። ከነዚህ በተጨማሪ ሌሎች ጎረቤቶችም ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ከዛ በፊትም በተለያየ ጊዜ ባልና ሚስት እየተፈራረቁ ሟችን እንደሚደበድቧት ለፖሊስ የምስክርነት ቃላቸውን እንደሰጡ ልብ አድርጉ።

### የተጠርጣሪዎች የእምነት ክህደት ቃል

ሟች አስቴር ነገሳ የተባለችውን ህጻን ከክፍለ ሀገር በቤት ሠራተኝነት አምጥታችሁ በተለያየ ቀን በማገዶ ፍልጥ እንጨት ዱላ፣ በሶኬት (በኤሌክትሪክ ሽቦ)፣ በጎማና በውሃ ማስተላለፊያ የፕላስቲክ ቱቦ የተለያየ የሰውነቷን ክፍል ስትደበድቧት ከላይ በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ሕይወቷ አልፏል። ሕይወቷ ካለፈ በኋላም በድብቅ ለመቅበር የአስከሬን ሳጥን በማምጣት ከትታችሁ ለመቅበር ሞክራችኋል፤ ተባሉ።

የአካባቢው ማህበረሰብ ለፖሊስ ባቀረበው ጥቆማ መሰረት ፖሊስ 1ኛ ተጠርጣሪ አቶ ልጅዓለም እና 2ኛ ተጠርጣሪ ወይዘሮ ቆንጅት ከላይ በተጠቀሰው ዕለት በቁጥጥር ሥር አውሎ ለቀረበባቸው የሰው መግደል ወንጀል ክስ የሚከተለውን የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል።

አንደኛ ተጠርጣሪ ሟች የአክስቱ ልጅ እንደሆነች ጠቅሶ፤ በ2008 ዓ.ም ከአክስቱ ነጥሎ ከወለጋ ክፍለ ሀገር "ላሳድጋት" ብሎ ወደ አዲስ አበባ ያመጣት መሆኑን ገልፆዋል። እርሱም በ2012 እና 2013 ዓ.ም የመጀመሪያና ሁለተኛ ልጁን ሲወልድ ሟች ልጆቹን ይዛ ተንከባክባ እንዳሳደገችለት ይናገራል። ሟች እቤት ውስጥ ቁጭ ብላ ቴሌቪዥን እየተመለከተች እያለ እንድትጠብቅ አደራ የተሰጣት የተጠርጣሪዎቹ ልጅ ከቤት ወጥታ ጎዳና ላይ አባቷ ሲያገኛት "ለምን ልጄን አትጠብቂም?" ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጀሉ ከመፈጸሙ ከሁለት ወር በፊት በቻርጀር መቀመጫዋ ላይ ደጋግሞ እንደመታት ይናገራል። ከዚህ ውጭ ገርፏት እንደማያውቅ እና እንደ ልጁ እንደሚያያት ተናግሯል።

"በጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 2:00 ሰዓት ላይ ሥራ ውዬ ወደ ቤት ስገባ ባለቤቴ ተኝታ ልጅ እያጠባች ነበር። ሟች ቆሻሻ ውሃ እደፋለሁ ብላ ይዛ ከቤት ስትወጣ በር ላይ ስትደርስ ማስታጠቢያውን እንደያዘች በፊት ለፊት በኩል ወደቀች። እኔም የሚጥል በሽታ ስላለባት የሚጥለው ነው ብዬ ከወደቀችበት አንስቼ ወደ ቤት አስገባኋት። ፍራሽ ላይ አስተኝቻት ልብስ አለበስኳት። ከዛ እረጅም ሰዓት ሳትነቃ ስትቆይ ምን ሆና ነው? ብዬ ልብሱን ገልጬ ስመለከታት አትተነፍስም፤ ሞታለች። የተፈጠረው ይህ ነው፤ እኔ ደብድቤ አልገደልኳትም" ሲል የእምነት ክደት ቃሉን ይሰጣል። 2ኛ ተጠርጣሪም በተመሳሳይ የሚጥል በሽታ ስላለባት የሞተችው ወድቃ እንጂ እኔ ደብድቤ አልገደልኳትም፤ መትቻትም አላውቅም" ብላ የእምነት ክደት ቃሏን ሰጠች።

### ዐቃቢ ሕግ

አጠቃላይ ሟች በሰውነቷ ላይ በደረሰባት በርካታ ጉዳቶች ምክንያት ሕይወቷ እንዲያልፍ ካደረጉ በኋላ በቀን በጥር 18 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት 3:00 ሰዓት የሟችን አስከሬን ሳጥን ውስጥ በማስገባት በድብቅ ለመቅበር ሲሉ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ልጅዓለም እና 2ኛ ተከሳሽ ወይዘሮ ቆንጅት የተያዙ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶባቸዋል።

ዐቃቢ ሕግም አምስት የሰው ማስረጃ፤ በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ያካሄደውን የፎረንሲክ ሜዲስንና ቶክሲኮሎጂ ትምህርት ክፍል በደብዳቤ ቁጥር ጳሀ8/3028 በታህሳስ 3 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠ የሟች አስቴር ነገሳ የሞቷ ምክንያት በሰውነቷ ላይ በተለያየ ቦታዎች ላይ ጉዳቶች በመድረሳቸው ሕይወቷ ያለፈ መሆኑን የሚያስረዳ የአስከሬን ምርመራ ውጤት ከነ ትርጉሙ07 ገፅ የሰነድ ማስረጃ፤ የሟችን የአማሟት ሁኔታ፣ ጉዳት እና ወንጀሉ የተፈጸመበትን ስፍራ የሚያሳይ 24 ገላጭ ፎቶ ግራፎችን እንዲሁም ተከሳሾች በወ/መ/ስ/ህ/ቁ 27(2) መሰረት ለፖሊስ የሰጡትን የእምነት ክህደት ቃል በማስረጃነት አያይዞ ለፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በፍጥነት እንዲታይ አቅርቧል። ዐቃቢ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በተከሳሾች ላይ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል።

### ውሳኔ

ታህሳስ 10 ቀን 2015 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በተከሳሾች ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመስጠት በችሎቱ ተሰይሟል። ፍርድ ቤቱም በዚህ ቀን በዋለው ችሎት ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በ25 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡና ለአምስት ዓመት ህዝባዊ መብቶቻቸው ተሽረው እንዲቆዩ ሲል ውሳኔ አሳልፏል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የዘሩትን ማጨድ!

**ቦጌዘ**

ሰሞኑን በማኅበራዊ ሚዲያ ሲዘዋወር ያየሁት አንድ የባህር ማዶ ገጠመኝ ለዛሬው ትዝብቴ መነሻ ነው። ታሪኩ እንዲህ ነው፦ በአሜሪካ ኮሎራዶ ውስጥ በሚገኝ አንድ የስጦታ መሸጫ መደብር ውስጥ አንዲት ያልታሰበች እንግዳ ድንገት መጣች። ይህች እንግዳ በአካባቢው ከሚገኘው ጫካ እግር ጥሏት የመጣች አጋዘን ናት። እናም ይህች አጋዘን ልክ እንደቤቷ ሰተት ብላ ወደመደብሩ ስትገባ ያየቻት የመደብሩ ባለቤት አላባረረቻትም። ይልቁንም እንኳን ደህና መጣሽ በሚል ስሜት ተቀብላት ከወንበሯ ተነስታ ዳበሰቻት፣ ኩኪስ ትበላ እንደሁ ብላ አውጥታ ሰጠቻት፡፡ አጋዟ የተሰጣትን ኩኪስ በላች እና ከመደብሩ ወጥታ ሄደች።

ከግማሽ ሰዓት በኋላም ያቺው አጋዘን ተመልሳ ኩኪስ ወደተሰጣት መደብር መጣች። አሁን ግን ብቻዋን አልነበረችም። እኔ የቀመስኩትን ይቅመሱ ብላ ልጆቿንም አስከትላ ነበር የመጣችው ።

«አዳኝ ብሆን ትሸሸኝ ነበር፣ ባባርራት ተመልሳ አትመጣም ነበር. .. ነገር ግን ለአጋዟ ጣፋጭ ኩኪስ ሰጠኋት፣ ይህን እሷ የቀመሰችውን ነገር ለልጆቿም እንድሰጥላት ልጆቿን አስከትላ መጣች። በየትኛውም አጋጣሚ ለማንኛውም ፍጡር ፍቅርን ከመስጠት ወደኋላ አንበል» ስትል የመሸጫ መደብሩ ባለቤት ምስሉን በድረገፅ አጋርታለች ፡፡

የዚህች ሴትዮ ተግባር አስደናቂ ነው፣ ብዙዎችም ወደራሳቸው እንዲመለከቱ ያደረገ ትልቅ ትምህርት ነው። ለማዳ ያልሆኑ የዱር እንስሳት ፍቅር እንደሚፈልጉ ትልቅ ማሳያ ነው። የሰው ልጅ ለየትኛውም ፍጡር ቢሆን ሳይለይ ፍቅር መስጠት እንዳለበት ትልቅ ምሳሌ ነው።

የኮሎራዶዋ ሴትዮ ለአጋዟ የሰጠችውን ፍቅር በማሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ እንኳን ለዱር አራዊት ለቤት እንስሳም የምንሰጠውን ቦታ አንታዘብ። እኛ ውሻ ያውም የማናውቀውን ድንገት መንገድ ስናይ በድንጋይ እናባርራለን። እንደዚህ የምናደርግ ሰዎች ውሻው ይነክሰናል ወይም ያጠቃናል ብለን አይደለም። ብቻ ባለቤት የሌለው ቢኖረውም ድንገት መንገድ ላይ የገጠመን ውሻ አይመቸንም። ይህ ልምድ ከየት እንደመጣና እንደዳበረ ምክንያታዊ ሃሳብ ማቅረብ አይቻልም።

እርግጥ ነው በእኛም ሀገር በርካታ ሰዎች የዱር አራዊትን አላምደው ፍቅር ሰጥተው አብረው ሲኖሩ የተመለከትንበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። የሐረር ጅቦች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ጅብ ብዙ ሰው የሚፈራውና በሰብአዊ ፍጡራን የማይወደድ አራዊት ነው። በእርግጥ ጅብ የሚወደድ ዓይነት እንስሳ አይደለም። ግን ደግሞ ካቀረብንና ከተንከባከብነው የአውሬነት ባህሪውን መግራትና ከዚያም አልፎ የቱሪስት መስህብ መሆን እንደቻለ የሐረር ጅቦች ማሳያ ናቸው።

ከፈረንጆች ልንኮርጃቸው ከሚገቡ ልምዶች መካከል ለእንስሳት ያለን አመለካከትና የምንሰጠው ቦታ አንዱ ነው። እነሱ ለእንስሳት ትልቅ ዋጋ ይሰጣሉ። በተለይም ለውሻና ድመት የሚሰጡት ቦታ አስገራሚም የሚያስቀናም ነው። በኢትዮጵያም በተለይም ለውሻ የሚሰጠው ቦታ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ እየተሻሻለ መጥቷል። ለዚህ በመዲናችን አዲስ አበባ በአንዳንድ ጎዳናዎች ትንንሽ ውሾች ሲሸጡ ማየት እየተለመደ መምጣቱን መጥቀስ ይቻላል። ከጎዳና አልፎም የተለያዩ ዓይነት ውሾች በውድ ዋጋ የሚሸጡበት ቦታ እዚሁ አዲስ አበባ መኖሩን በአንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ መመልከቴን አስታውሳለሁ።

ሰዎች ውሻና ድመትን በዋናነት የሚንከባከቡትና የሚያቀርቡት ከእንስሳቱ የሚያገኙት አገልግሎት ኖሮ አይደለም። ትልቁ ምክንያታቸው ከእንስሳቱ የሚያገኙት ፍቅር ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ግን በብዛት ውሻ የምናሳድገው በራችን ላይ ቆሞ እንደዘበኛ እንዲያገለግለን ነው። ድመትንም ቢሆን አይጥን የመሳሰሉ ትንንሽ አጥፊ እንስሳትን እንዲያድኑልን እንጂ ለሚሰጡን ፍቅር ብለን አይደለም። ያሳደግነው ውሻ ለማዳ ሆኖ ግቢያችን የገባ የወጣው ሰው ላይ ካልጮኸ ፈሪ ነው ተበላሽቷል ብለን አውጥተን የምንጥል ብዙ ነን። ድመትንም ቢሆን አይጥ አድና ትብላ ምግብ አትስጧት የሚሉ ሰዎች ገጥመውኝ ያውቃሉ። ይህ ትክክለኛ አመለካከት አለመሆኑን ለማስረዳት መድከም አያስፈልግም። ውሻን ማሳደግ ያለብን የሚሰጠንን ፍቅርና ታማኝነት በማሰብ መሆን ይገባል። ፈሪ ነው ብለን አውጥተን የምንጥለው ውሻ ከእኛ አልፎ የማኅበረሰብ ችግር ሊሆን እንደሚችል ማስታወስ ተገቢ ነው። ምናልባት ስለማናስተውል ይሆናል እንጂ ውሻን ፈሪ ነው ብለን አውጥተን ባንጥለውና ብንንከባከበው እንዲጠብቅልን የምንፈልገውን ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም። ባእድ የሆነ ነገር ሲያይ ፈሪም ይሁን ደፋር ጮኾ ለባለቤቱ ማሳወቁን አይቀርምና። ድመትም ብትሆን ምንም ያህል ብንንከባከባትና ብትጠግብ እንድታድንልን የምንፈልገውን አይጥ እየተመለከተች ዝም ብላ አትቀመጥም፣ ምክንያቱም ተፈጥሯዊ ባህሪዋ ነውና።

እንዲያው ውሻና ድመትን ለምሳሌ አነሳን እንጂ ትልቅ አገልግሎት ለሚሰጡን የቤት እንስሳትም ቢሆን ያለን አመለካከትና የምንሰጠው ቦታ አስተዛዛቢ ነው። ለዚህ ከአህያ የበለጠ ማሳያ ሊኖር አይችልም። አህያ አመመኝ ደከመኝ ሳትል የሰዎችን ሸክም ያቀለለች እንስሳ ነች፣ ለአንዳንዶችም የእንጀራ ገመድ ነች፣ ግን በዚያ ልክ እንክብካቤ ሲሰጣት አይታይም። እንዲያውም ከአቅሟ በላይ ተሸክማ ቁና ቁና እየተነፈሰች ስታገለግል የሚወርድባት የዱላ መአት ምንያህል እንደሚያሳዝን ሩቅ ሳንሄድ እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ሳንመለከት አንቀርም። ተግታ ባገለገለች ስሟ የመጥፎ ስድብ መገለጫ ተደርጎ የምናይበት አጋጣሚም ብዙ ነው። ውሻም በሀገራችን እንደ መጥፎ ስድብ ይቆጠራል። ግን ደግሞ አሁን አሁን እየቀረ የመጣ ይምሰል እንጂ በአንዳንድ አካባቢዎች እናቶች የሚወዱትን ልጅ «ውሻዬ» ብለው ሲያቆላምጡት እንሰማለን።

ከዚህ የምንረዳው በእንስሳት ላይ ያለን አመለካከት የተዛባና መስተካከል ያለበት መሆኑን ነው። ለማንኛውም ፍጡር ፍቅር ከሰጠን ፍቅር እንደምንቀበል ግን መነሻችን ላይ ካነሳነው ከአጋዟ ገጠመኝ መማር ይቻላል፣ ሰው የዘራውን ያጭዳል እንደሚባለው።

# ዓለም አቀፍ

## ኔዘርላንድስ በቅኝ ግዛት ወቅት የዘረፈችውን ቅርሶች ልትመልስ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኔዘርላንድስ በቅኝ ግዛት ወቅት ስትገዛቸው ከነበሩ ሀገራት የዘረፈችውን ሀብቶች ልትመልስ ነው።

ኔዘርላንድስ ለኢንዶኔዢያ እና ስሪ ላንካ ከምትመልሰው ውድ ሀብቶች መካከል በውድ ማዕድናት ያጌጠ ከነሐስ የተሠራ መድፍ ይገኝበታል። የኔዘርላንድስ የባሕል ሚኒስትር ጉናይ ኡስሉ «በመጀመሪያ ደረጃ ወደ ኔዘርላንድስ መምጣት ያልነበረባቸውን ዕቃዎች ስንመልስ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው» ብለዋል።

ኔዘርላንድስ የተዘረፉ ንብረቶችን እንደምትመልስ ይፋ የሆነው ሀገሪቱ በቅኝ ግዛት ተሳትፎዋ ይቅርታዋን እየገለጸች ባለችበት ወቅት ነው። የሀገሪቱ መንግሥትም በቅኝ ግዛት ወቅት የተዘረፉ ንብረቶች እንዲመለሱ በባለቤት ሀገር ጥያቄ ከቀረበለት እንዲመለስ ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲቀርብለት ነበር።

ቅርሶቹ እንዲመለሱ ሲጠይቁ ከነበሩት አንዱ የተዘረፉ ቅርሶችን በተመለከተ ጥናት እንዲያደርግ በሀገሪቱ መንግሥት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው። ኮሚቴው የደች መንግሥት ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ቅርሶቹን እንዲመልስ ምክረ ሃሳብ አቅርቧል። በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ የኔዘርላንድስ ንጉሥ ሀገራቸው በባሪያ ንግድ ላይ ለነበራት ተሳትፎ ይፋዊ ይቅርታቸውን አቅርበው ነበር።

ንጉሥ ዊሌም-አሌክሳንደር በኔዘርላንድ የባሪያ ንግድ የቆመበት 160ኛ ዓመት ሲዘከር ባደረጉት ንግግር የባሪያ ንግድን «እጅግ አስከፊ» ብለው ከገለጹ በኋላ ኔዘርላንድስ በባሪያ ንግድ ውስጥ ለነበራት ተሳትፎ በራሳቸው እና በሀገሪቱ ስም ይቅርታ ጠይቀዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሌሎች ቅኝ ገዢ የነበሩ ሀገራት ከጥንት በፊት የተዘረፉ ንብረቶችን ለባለቤት ሀገራት እየመለሱ ይገኛሉ። የእንግሊዝ እና የጀርመን ሙዚየሞች እ.አ.አ 1897 ላይ በእንግሊዝ መንግሥት ከናይጄሪያ የተዘረፉ የቤኒን ነሐሶች ተብለው የሚጠሩ ውድ ሀብቶችን ለምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር መልሰዋል።

የኔዘርላንድስ የባሕል ሚኒስትሩ ሀገራቸው የተዘረፉ ቁሶችን ከመመለስ በተጨማሪ ከሀገራቱ ጋር በትብብር ትሠራለች ብለዋል። ለኢንዶኔዢያ ከሚመለሱት ቅርሶች መካከል እ.አ.አ 1894 ላይ ሀገሪቱ ቤተ-መንግሥቶች ከአንዱ የተዘፉ በውድ ማዕድናት የተዋቡ ቅርጻ ቅርጾች፣



ውድ ማዕድናት፣ ወርቅ እና ብር ይገኙበታል። ስሪ ላንካ ደግሞ አምስተርዳም በሚገኘው ሪጅክስ ሙዚየም ለዕይታ ተቀምጦ የሚገኘውን የ18ኛው ክፍለ ዘመን የነሐስ መድፍ ትቀበላለች።



## የኢራን አብዮታዊ ጥበቃ በባህረ ሰላጤው የንግድ መርከብን ተቆጣጠረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኢራን አብዮታዊ ጥበቃ ሐሙስ ዕለት በባህረ ሰላጤው ዓለም አቀፍ ውሃ ውስጥ የንግድ መርከብን «በግዳጅ ያዘ» ተብሏል።

መርከቧም በሕገ-ወጥ ዝውውር ላይ የተሳተፈች ሳትሆን አትቀርም ሲል የአሜሪካ የባህር ኃይል ቃል አቀባይ ተናግረዋል። የአሜሪካ የባህር ኃይል ሁኔታውን ተከታትሎ ምንም ዓይነት ምላሽ ላለመስጠት ወስኗልም ተብሏል።

ኢራን በበኩሏ በባህረ ሰላጤው ውሃ ላይ ሲጓዙ ከነበሩት ታንከሮች መካከል አንዱ ከኢራን መርከብ ጋር በመጋጨቱ ለመያዝ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዳላት ገልጻለች። የብሪታንያ የባህር ላይ ደህንነት ኩባንያም አንዲት ትንሽ የታንዛኒያ ጀልባ የኢራን ኃይሎች ለመያዝ ሙከራ ማድረጋቸውን ተናግሯል።


«ኢራን በሕገወጥ መንገድ ዘይት ያጓጉዛሉ ብላ የጠረጠራቸውን ትናንሽ ታንከሮች አዘውትሯ ትይዛለች» ሲል ኩባንያው አክሎ ተናግሯል። ከዓለማችን አንድ አምስተኛው ድፍድፍ ዘይትና የዘይት ምርቶች በኢራን እና ኦማን መካከል ባለው የሆርሙዝ ባህር በኩል ይተላለፋሉ። የአሜሪካ የባህር ኃይል ኢራን በኦማን ባህረ ሰላጤ ላይ ሁለት የንግድ ታንከሮችን እንዳትይዝ ጣልቃ መግባቱን ገልጿል።

ከፈረንጆቹ 2019 ጀምሮ በአካባቢው መርከቦች ላይ ተከታታይ ጥቃቶች ይደርሳሉ ሲል ሮይተርስ ዘግቧል።

## መጋቢ አዕምሮ

# በፍጥነት የማሰብ ጥበብ

**አስናቀ ፀጋዬ**



በፍጥነት ስናስብ በርካታ ነገሮችን በቀላሉ ማሳካት እንችላለን። በቶሎ ስራችንንና ትምህርታችንን እናጠናቅቃለን። የምንፈልገውን ነገርም በፍጥነት እንለምዳለን። ምን አልባት ቋንቋ ይሆናል መልመድ የፈለግነው። ወይ ደግሞ በትምህርታችን ይሆናል መጎበዝ የፈለግነው። አልያም ስራችንን በፍጥነትና በጥራት ማጠናቀቅ ፈልገን ይሆናል። ዞሮ ዞሮ ግን አይምሯችን ከፈጠነ ሁሉ ነገር ቀላል ይሆናል።

መቼም አስተውላችሁ ከሆነ የሰለጠኑት ሀገራት ከባድ ሩጫ ላይ ናቸው። የኢንተርኔት ፍጥነትን ለማሳደግ ‹‹ፎር ጂ›› እና ‹‹ፋይፍ ጂ›› ይላሉ። ለምን ይመስላችኋል? የኢንተርኔት ፍጥነት በጨመረ ቁጥር መረጃዎችን በፍጥነት ለመቀያየር ስለሚያስችላቸው ነው። መረጃዎችን በፍጥነት በተቀያየሩ ቁጥር ደግሞ ስራቸውን በፍጥነት በማከናወን ያለሙት የእድገት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።

እኛም ማደግ፣ መለወጥና ህይወታችንን እስከመጨረሻው መቀየር የምንፈልግ ከሆነ አይምሯችን የሚያስብበት ፍጥነት መቀየር አለበት። አይምሯችን እንደ ተንቀሳቃሽ ስልክ ነው። መተግበሪያው ደግሞ ሃሳብ ነው። ሃሳባችን በፍጥነት ከተንቀሳቀሰ ህይወታችንን መቀየር እንችላለን። የምንፈልገውን ነገር በአንዴ እንለምዳለን። ስራችንን በፍጥነት እናከናውናለን። የተሻለ ቦታ ላይ እንገኛለን። ውጤታማም እንሆናለን። ስለዚህ በፍጥነት የማሰብ ጥበብን እንዴት ማዳበር እንችላለን?

### 1ኛ. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ

ተክዘው፣ ድክም ያለ አቀማመጥ ተቀምጠው በፍፁም በፍጥነት ሊያስቡ አይችሉም። ቢያንስ መንቀሳቀስና መራመድ አለብዎ። ልክ ሲንቀሳቀሱ ስሜትዎ ይቀየራል። በደምብ ማሰብ ይጀምራሉ። ‹‹emotions are created from motions›› ይላሉ ፈረንጆች። ጥሩ ስሜት የሚሰማን ስንቀሳቀስ ነው እንደማለት ነው። በተንቀሳቀስን ቁጥር ጥሩ እናስባለን። ስለዚህ አይምሯችን በሙሉ አቅሙ እንዲያስብ የሚያደርገው አንዱና ዋነኛው ነገር የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ነውና የግድ ከባድ ሳይሆን ቀላል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ አለብን።

ለምሳሌ ትንፋሻችንን ለማስተካከል የሚረዱ ኤሮቢክ እንቅስቃሴዎች መስራት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ረዘም ያለ የእግር ጉዞ ማድረግ ይቻላል። በመጠኑ ፈጠን ብሎ መሮጥም ሊሆን ይችላል። ብቻ ዋናው ዓላማው ትንፋሽ እንዲወጣና እንዲገባና በሰውነታቸው ጥሩ የአየር እንቅስቃሴ እንዲኖር ነው የሚፈለገው። ይህም አይምሯችን ነፃ ሆኖ እንዲያስብ ያስችለዋል። ይህን በሳምንት ውስጥ ለሶስት ወይም ለአራት ቀን ካደረግነው በጣም ጥሩ ይሆናል።

ታዲያ መቼ ልስራ ካሉ በጧት ይሁን። ለምን መሰልዎ? በጥዋት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ሲሰሩ አብዛኛውን የአይምሮ ማሰብ ስራ የሚከውኑት ‹‹ኒውሮ ትራንስሚተር›› የተሰኙት ክፍሎች ስራቸውን በፍጥነት ስለሚሰሩ ነው። ከስፖርቱ በኋላ ቢያነቡ፣ ስራ ቢሰሩና አዲስ ነገር ቢሞክሩ አይምርዎ በፍጥነት ያስባል።‹‹እኔ ማታ ከስራ በኋላ ነው ስፖርት የምሰራው›› ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ነገር ግን ማታ ስፖርት ከሰሩ በኋላ ይደክምዎታል። አይምሮዎም በዚህ ሰዓት አዲስ ነገር ሊያስብ አይችልም። ስለዚህ ስፖርት በጥዋት ይስሩ።

### 2ኛ. ነገሮችን እንደመዝናኛ መቁጠር

ይህ ማለት የሚማሩትን ትምህርትና የሚሰሩትና ስራ እንደመዝናኛ መቁጠር እንደማለት ነው። ይህ ሲሆን አይምሮዎ በተቀላጠፈ ሁኔታ ያስባል። ልብ ብለው እንደሆነ ሲዝናኑ ቶሎ አይሰለቹም። ቶሎ አይደክሙም። መቆምም አይፈልጉም። ደስ የሚለው ነገር ደግሞ የተዝናኑበትን ወቅት አይረሱትም። ስለዚህ ስራውንም፤ ትምህርቱንም እንደመዝናኛ መቁጠር ነው። የግድ መስራት ያለብን ነገር ካለ ለራሳችን ጥሩ ጥሩውን ነገር መንገር ነው። ‹‹እኔ እኮ በጣም የምወደውን ስራ እየሰራሁ ነው፣ እኔ እኮ በጣም ነው ደስ የሚለኝ ስራዬን ስሰራ፣ በጥሩ ስሜት ውስጥ ነው ያለሁት፣ ስራዬን እንደመዝናኛ እኮ ነው የማየው›› ማለት አለብን።

እነዚህን ንግግሮች በደጋገምናቸው ቁጥር አይምሯችን እውነት ይመስለዋል። መቼም ታውቃላችሁ ‹‹ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል›› ሲባል። አያችሁ! ስለዚህ በስራችን እንደምንዝናና ለአእምሯችን ደጋግመን በነገርነው ቁጥር የሆነ ሰዓት ላይ ስራውን እያቀላጠፍነው ነው። በፍጥነት እየጨረስን ነው። ለምን? አይምሯችን የሚያውቀው ያ ነገር እንደሚያዝናናን ነው። ስለዚህ በፍጥነት ያስባል ማለት ነው።

### 3ኛ. መደጋገም

ዓለምን ጉድ ካስባሉ የአይምሯዊ ጥናቶች መካከል ዶናልድ ሄብ የተሰኘው የሳይንስ ሊቅ የሰራው ጥናት አስደማሚ ነው። የሄቢያን ቲዎሪ እንዲህ ይላል: - ‹‹አንድን ስራ በመጀመሪያው ቀን ልክ ስናደርገው በአይምሯችን ውስጥ ያለች አንዲት ትንሸዬ ህዋስ ነቃ ትላለች። ከዛ አጠገቧ ያለውን ሌላ ደቃቅ ህዋስ ትነካዋለች፤ ታግለዋለች። እሱ ደግሞ ሌላውን ያጋግላል። እንዲህ እያሉ አንዱ ሌላውን ህዋስ እያጋጋለ መላው ህዋስ ይጋጋላል። በዚህም ሁሉም ህዋሳት ስሜት ውስጥ ገብተው organice transformation ይፈጥራሉ። ወይም በሌላ አነጋገር የሁኔታ ለውጥ ይፈጠርና ከዚህ በኋላ ስራውን ደጋግመን ስንሰራ ህዋሳቱ ቶሎ ቶሎ መነቃቃት ይጀምራሉ። ስለዚህ በቀላሉ ስራውን እንሰራዋለን››

ለምሳሌ ስልክ የመጀመሪያችን ከሆነ የኪቦርድ ፊደላትን ፈልጎ ለመንካት ግዜ ይፈጅብናል። ነገር ግን አይምሯችን እነዚህ ሴሎች ካለማመደ በኋላ ኤን ነክቶ ቢን መንካት ቀላል ይሆንለታል። ከዛም ሁሉንም ፊደላት በፍጥነት መንካት እንችላለን። ለምን? አይምሯችን ይህን ተግባር ለምዶታል። ስለዚህ በምንም ነገር በፍጥነት ማሰብ ከፈለግን፣ ምንም አይነት ምድራዊ የሆነ ክህሎት መቻል ከፈለግን በቃ አይምሯችንን ማለማመድ ነው።ቶሎ ቶሎ መደጋገም ነው።

ዓለምን ጉድ ያስባሉ ሰዎች የተሳካላቸው በመደጋገማቸው ነው። የዓለማችን እግር ኳስ ኮከብ ሊዮኔል ሜሲ ወዶ መሰላችሁ እንደው በየቀኑ ኳስ ሳልነካ አልውልም የሚለው። እንደቢልጌት የኮምፒዩተር ፕሮግራም ሳልሰራ ውዬ አላድርም ነበር የሚሉት። ሌሎቹም እንደዛው ክህሎታቸውን ይደጋግሙታል። እርስዎም ህይወትዎን ሊቀይር የሚችልና በጣም የሚፈልጉት ነገር ካለ ይደጋግሙት።ስኬታማ ያደርግዎታል።

### 4ኛ. የአኗኗር ዘይቤን ማስተካከል

የምንበላው፣ የምንጠጣው፣ የምናየውና የምንሰማው ነገር ሊያፈጥነውም ሊያዘገየውም ይችላል። ለምሳሌ በጣም ጠግቦ የሚበላ ሰው ማሰብ አይችልም። ይደክመዋል። ማረፍ፤ መተኛት ነው የሚፈልገው። ውሃ በደምብ የማይጠጣ ሰው አይምሮው ቶሎ ማሰብ አይችልም። ይደክመዋል። መጠጥ የሚያበዛ ሰውማ የሚያውቀውንም ሁሉ ይረሳል። ስለዚህ ውሃ በደምብ መጠጣት፣ የተመጣጠን ምግብ መመገብ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የምናያቸው ነገሮች ተደጋጋሚና አሰልቺ መሆን የለባቸውም። ለምሳሌ አንዳንድ ሰው ከጦርነት ፊልም ውጪ ምንም አያይም። ስለዚህ አይምሮው በፍጥነት አያስብም። እንደውም ያሚያስበው በጉልበቱ ነው። አይምሮዬ እንዴት በፍጥነት ሰርቶ ገንዘብ ላግኝ አይልም። ለምን? የሚያየው የድብድብ ፊልም ነዋ! ስለዚህ አንዳንድ ግዜ ወጣ ያለና አዲስ ነገር መሞከር አለብን። ‹‹እኛም እኮ ይህን ስለምናውቅ ነው የፍቅር ፊልም የምናየው›› ልትሉ ትችላላችሁ። የፍቅር ፊልምም ደጋግሞ የሚያይ ሰው ከዛ ውጪ የማያይ ከሆነ ስሜቱ ስስ ነው የሚሆነው። በቃ ነገሮችን የሚተረጉመው ከስሜት አንፃር ብቻ ነው። ቶሎ ይጎዳል። ስለዚህ በህይወታችን ውስጥ አዲስ ነገር መሞከር አለብን። የምናየውና የምንሰማው መቀየር አለበት። አድማሳችንን ባሰፋነው ቁጥር አይምሯችን በፍጥነት ያስባል። ብዙ ነገር ማሰብ ይችላል።

### 5ኛ.መጠነኛ ቅዝቃዜ ላይ መሆን

በጣም ሙቀት ውስጥ ከሆንን ድካም ነው የሚሰማን። እንቅልፍ እንቅልፍ ነው የሚለን። መተኛት ነው የሚታየን። በተለይ ውጫዊ ድካም ውስጣዊውን ይገለዋል። እንዴት ነው እርስዎ ደክምዎት የሚገርም ሃሳብ ሊያስቡ የሚችሉት? ስለዚህ ቀዝቀዝ ያለ ሻወር መውሰድና መጠነኛ የሰውነት ሙቀት ላይ መሆን አለብዎ።በፍጥነት እንዲያስቡ መቀዝቀዝ አለብዎ።

### 6ኛ.ውጫዊና ውስጣዊ ማነቃቂያ ማስቀመጥ

የሰው ልጆች ሆነን አንድ ነገር ለመስራት፣ ለማሰብና በደምብ ለመማር የሆነ ሽልማት እንፈልጋለን። ውጫዊ ሽልማቶች አንዳንዴ ይኖራሉ። ሽልማቱ ገንዘብ፣ በትምህርት ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ አልያም የሰዎች አድናቆት ሊሆን ይችላል። ይህ ግን ከራሳችን ሳይሆን ከሰዎች የምናገኘው ሽልማት ነው። አያችሁ! አንዳንዴ ስንሰራ ሰዎች ዞር ብለው ላያዩንም ይችላሉ። እኛ እኮ ምርጥ ነገር እየሰራን ነው።

ለአይምሯችን ሽልማት ካስቀመጥንለት በፍጥነት ያስባል። ስለዚህ ከሰው ሳንጠብቅ ራሳችንን መሸለም አለብን። ‹‹ይህን ስራ ከሰራሁት በደምብ አድርጌ እዝናናለሁ። እደሰታለሁ። የምወደውን ምግብ እበላለሁ። ከምወደው ሰው ጋር አወራለሁ። ከምወደው ሰው ጋር እዝናናለሁ። የእግር ጉዞ አደርጋለሁ። አይምሮዬን የሚያስደስተኝን ነገር አደርጋለሁ›› ስንል ያንን ስራ ለመስራት ሲል አይምሯችን በፍጥነት ያስባል። ስራው ይሰራል። ትምህርቱም ቶሎ ይገባናል። ለምን? ሽልማት አስቀምጠናላ! እንጓጓለን።

ለአይምሯችን ውጫዊ ማነቃቂያ ብቻ በቂ አይደለም። ውስጣዊም ያስፈልጋል። ውስጣዊ ስንል አንድን ነገር ስንሰራ በውስጣችን የሚሰማን ስሜት መጋል አለበት ማለት ነው። ‹‹ይሄን ስራ እኮ በደምብ ከጨረስኩት፣ በደምብ አድርጌ አስቤ ትምህርቴን ካጠናሁት፣ ቋንቋውን በደምብ ከቻልኩት ምን አይነት በራስ መተማመን ነው የሚሰማኝ›› ስንል ውስጣችን ለራሱ ሲል፣ በራስ መተማመኑን ለማሳደግ ሲልና ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ለማድረግ ሲል ቶሎ ይገባናል። ቶሎ እናነባለን። በፍጥነት ማሰብ እንችላለን። ስራው ይቀላጠፋልናል።

### 7ኛ. መፃፍ

ችግር ገጥሞዎት መፍትሄ ፈልገው ይሆናል። ስልክዎን ያጥፉ። ጡሩ አቀማመጥ ወንበር ላይ ይቀመጡ። ከዛ ወረቀትና እስክሪቢቶ ያውጡ። የገጠምዎን ችግርና ምን መፍታት እንደሚፈልጉ ይፃፉ። ይህን ሲያደርጉ ሁለት ነገሮች ይፈጠራሉ። የመጀመሪያው ችግሩ ቀለል ይልዎታል። በመቀጠል ደግሞ ልክ መፃፍ ሲጀምሩ አይምርዎ መፍጠር ይጀምራል። ‹‹ችግሩን እንዲህ ቢፈቱትስ›› እያለ አይምሮዎ ያስባል።

ከምንፅፈው ፍጥነት በላይ አይምሯችን ያስባል።ከዛ መፃፍ ነው እንግዲህ የመጣልንን መፍትሄ። ብዙ ሰዎች ‹‹ወረቀት ላይ በፃፍኩ ቁጥር ችግሬን እየፈታሁት ነው፤ ደስተኛ እየሆንኩ ነው›› ይላሉ። ስለዚህ ችግሮቻችንን ወረቀት ላይ መፃፍ አስገራሚ መፍትሄ ነውና እርስዎም ይለማመዱት።

### 8ኛ. ትክክለኛውን ጥያቄ መጠየቅ

አንድን ነገር በግልፅና ቅልብጭ ባለ መልኩ ከጠየቅን አይምሯችን በአንድ አቅጣጫ ያስባል። መፍትሄ ለማግኘት የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ለምሳሌ አንድ ሰው ‹‹እንዴት ህይወቴን ልቀይር?›› ብሎ ጥያቄ ቢያስቀምጥ ግልፅ አይደለም። በጣም ውስብስብ ነው። ህወቱን የሚቀይረው በገንዘብ ነው፣ በስራ ነው፣ በትምህርት ነው ወይስ በፍቅር ግንኙነት ነው? ‹‹አይ እኔ በገንዘብ ነው ህይወቴን መቀየር የምፈልገው›› ካለ ሁለተኛ ማንሳት ያለበት ጥያቄ በገንዘብ እንዴት ህይወቴን ልቀይር? ሊሆን ይችላል።

ይህም ቢሆን ግልፅ ጥያቄ አይደለም። በገንዘብ እንዴት ህይወቴን ልቀየር ሲል ገንዘብ እኮ በተለያየ መንገድ ይገኛል። በቢዝነስ ነው ህይወቱን የሚቀይረው፣ በብድር ነው ገንዘቡን የሚያሳድገው ወይስ በደሞዝ ነው ገንዘቡን ከፍ የሚያደርገው? ማሳደግ የምፈልገው ደሞዜን ነው ብሎ ወርሃዊ ገቢዬን እንዴት ላሳድግ? ብሎ ሶስተኛ ጥያቄ ሊያነሳ ይችላል። ይሄ ይሻላል። ቢሆንም ግን አሁንም ጥያቄው ግልፅ አይደለም። ምክንያም ወርሃዊ ደሞዙ ሀምሳ ብር ከሆነ ሃምሳ አንድ ብር ወር ላይ ቢመጣ አድጓል። ግን አንድ ብር ህይወቱን አይቀይረውም።

ጥያቄው ግልፅና ነጠላ መሆን አለበት። ስለዚህ ግለሰቡ ማለት ያለበት ‹‹ወርሃዊ ገቢዬን እንዴት ሁለት እጥፍ ማሳደግ እችላለሁ›› ነው። ይህ ትክክለኛ ጥያቄ ነው። አሁን አይምሮው በሁለት እጥፍ የግለሰቡን ደሞዝ ለማሳደግ የማይፈነቅለው ድንጋይ፤ የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። ‹‹ለምን አንላይን አትሰራም?›› ይላል። ከፈለገ ደግሞ ‹‹ለምን ሁለት ሶስት ስራ አትሰራም?›› ሊልህ ይችላል። እርስዎም ትክክለኛውን ጥያቄ ከጠየቁ አይምሮዎ ለመመለስ በጣም ፈጣን ነውና ትክክለኛውን ጥያቄ ይጠይቁ።

# መነሻውን በሸቦ መኪና ያደረገው የማሽኖች አምራች

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ገና ልጅ እያለ ጀምሮ ከሽቦና ከብረት ጋር ቁርኝት ጥብቅ እንደነበረው ያስታውሳል፡፡ ትኩረት ሰጥቶና ሥራዬ ብሎ ባይከታተለውም ከዕድሜ አቻዎቹ ይልቅ ለፈጠራ ሥራ ነፍሱ ታደላ እንደነበር ቤተሰቡን ጨምሮ ጓደኞቹ ይነግሩት እንደነበርም ያስታውሳል፡፡ ህጻናት አፈር ፈጭተው በሚጫወቱበት እሱም እንደ ዕድሜ አኩዮቹ የሽቦ መኪና ይሠራ ነበር፡፡ በወቅቱ የዕድሜ አቻዎቹ ከሚሠሩት መኪና ይልቅ እርሱ የሚሠራው የሽቦ መኪና አስር እጥፍ የተሻለና አስገራሚ በወቅቱ ጓደኞቹ ይገልጹለት እንደነበርም ያስታውሳል፡፡ ይህ ችሎታው በሰፈሩም ሆነ ከሰፈሩ ውጭ ባሉ ጓደኞቹ ተመራጭ አድርጎት እንደነበር ያስታውሳል፡፡

በወቅቱ ታዲያ በውስጡ ያለውን እምቅ ተሰጥኦ በቅጡ መረዳት ባይችልም፣ ‹‹ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል›› እንዲሉ ውስጣዊ ፍላጎትና ተሰጥኦውን እየተረዳ በመምጣቱ ለትምህርት ትኩረት በመስጠት አሳድጎታል፡፡

በትምህርት የዳበረውን ውስጣዊ ፍላጎትና ተነሳሽነቱን አጣምሮ የአምራች ኢንዱስትሪውን የተቀላቀለው እንግዳችን አቶ አይሸሽም ጥላሁን ይባላል፡፡ አቶ አይሸሽም የ‹‹ኤቲደብሊው›› ማሽነሪ አምራች ድርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ ተወልዶ ያደገው ደብረማርቆስ ከተማ ሲሆን፤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ንጉስ ተክለኃይማኖት ትምህርት ቤት፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ ደብረማርቆስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተከታተለው፡፡

አቶ አይሸሽም፤ ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጥ ቤተሰብ የተገኘ መሆኑ ለትምህርት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እንዲማር እንዳደረገው ይናገራል፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በሜካኒካል ኢንጅነሪንግ ያገኘ ሲሆን፤ ባገኘው የውጭ አገር የትምህርት ዕድልም እንዲሁ ሁለተኛ ዲግሪውን ከባርሴሎና፣ ስፔን በ‹‹ፐርሰናል ፋብሪኬሽን (ዲጅታል ፋብሪኬሽን)‹‹ አግኝቷል፡፡ ይህን ትምህርቱን ከውስጥ በመነጨ ጥልቅ ፍላጎት ደስ እያለው እንደተማረም አጫውቶናል፡፡ ፐርሰናል ፋብሪኬሽን ወይም ዲጂታል ፋብሪኬሽን የሚባለው ትምህርት በዋናነት በብዛት ማምረት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሳይሆን፤ ሰዎች ደስ ያላቸውን ማንኛውንም ነገር ማምረት እንዲችሉ የሚፈቅድ እንደሆነ አቶ አይሸሽም ይገልጻል፡፡

ከአገር ውስጥ በተጨማሪ በውጭ አገር ከውስጥ በመነጨ ፍላጎት ደስ እያለው የተከታተለው ትምህርት ዛሬ የተለያዩ የግብርና፣ የጽዳት፣ የጨርቃጨርቅ፣ የኮንስትራክሽንና ሌሎች የተለያዩ የማምረቻ መሳሪያዎችን ማምረትና ማባዛት አስችሎታል፡፡ በውስጡ የሚንቀለቀለውን የፈጠራ ሥራ ፍላጎት በተለያየ መንገድ አውጥቶ ለመጠቀም ባደረገው ከፍተኛ ጥረት ከውጭ አገር የትምህርት ዕድል በተጨማሪ በአገር ውስጥም የተለያዩ ዕድሎች አጋጥመውታል፡፡ ዕድሎችን በአግባቡ መጠቀም በመቻሉም ለስኬት እንደበቃ የሚናገረው አቶ አይሸሽም፤ ከትምህርት ቤት እንደወጣ በዳን ቴክኖክራፍት ሊፍት አምራች ድርጅት ውስጥ ለሁለት ዓመት ተቀጥሮ ሠርቷል፡፡ ከሁለት ዓመት የቅጥር ሥራ በኋላ ግን ከጓደኞቹ ጋር የተለያዩ ጥናቶች በማድረጉ በርካታ ክፍተቶችን ማስተዋል ችሏል፡፡ ክፍተቶችን ለመድፈንም ችግር ፈቺ የሆኑ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን እያመረተ ይገኛል፡፡

በፈጠራ ሥራዎቹ በተደጋጋሚ ተወዳድሮ ማሸነፍ የቻለው አቶ አይሸሽም፤ በፈጠራ ሥራዎቹ ህንድ አገርም የመሄድ ዕድል ገጥሞታል፡፡ የሜካኒካል ኢንጅነሪንግ ትምህርቱን በተለይም በባርሴሎና በብዙ ልፋትና ጥረት በተግባር መማር የቻለ ሲሆን፤ ትምህርቱም በመላው ዓለም ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር በመሆኑ ብርቱ ፉክክር የነበረው እንደሆነ ያስታውሳል፡፡ ያም ቢሆን ትምህርቱን በጥሩ ውጤት ማጠናቀቅ ችሏል፡፡ ወደ አገር ቤት በተመለሰ ጊዜም ትልቅ ራዕይ ሰንቆ በከፍተኛ ተነሳሽነት ለውጥ ለማምጣት አቅዶ የነበረ ቢሆንም ብዙ ደንቃራዎች ታግለውታል፡፡

ሁለተኛ ዲግሪውን በስፔን መንግሥት ወጪ የተከታተለው አቶ አይሸሽም፣ ይህን እድል ላመቻቸላት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለት ዓመት የማስተማር ግዴታ ነበረበት፡፡ ይህን ግዴታውን ለመወጣት በዩኒቨርሲቲው እሱ ተምሮት የመጣው ሙያ የትምህርት ክፍል ፕሮግራም ባለመከፈቱና የተለያዩ ግብዓቶች ባለመሟላታቸው ሳቢያ



አቶ አይሸሽም ጥላሁን

በዩኒቨርሲቲው ማስተማር አልቻለም፡፡ እርሱ ግን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የፈጠራ ሥራዎቹን በመሥራት የራሱን ድርሻ ለመወጣት ያደረጋቸው ከፍተኛ ጥረቶች ሁሉ ፍሬያማ ሆነው ውጤታማ እንዳደረጉት አጫውቶናል፡፡

መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚያድግበትን የተለያየ መንገድ እያመቻቸ እንደሆነ የሚናገረው አቶ አይሸሽም፣ ለእዚህም የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ አንዱ ማሳያ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ከማምረቻ መሳሪያዎች ጋር በተያያዘ በግሉ ፈቃድ ሳያወጣ ጀምሮ ከጓደኞቹ ጋር የሽመና ማሽን እና የተለያዩ መሳሪያዎችን ሲያመርት ጥቂት የማይባሉ ድጋፎችን ከመንግሥት ማግኘቱን ይገልጻል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም ያልተሠሩ በርካታ ሥራዎች ስለመኖራቸው ይጠቁማል፡፡

አቶ አይሸሽም በ2005 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በቀጥታ ይተላለፍ በነበረው የፈጠራ ሥራ ውድድር ሁለተኛ ወጥቷል፡፡ በወቅቱ ለውድድር ይዞ የቀረበው ማሽን የሽመና ሥራን በቀላሉና በፈጠነ መንገድ መሥራት የሚያስችል፤ የሸማኔዎችን ጊዜና ጉልበት የሚቀንስ፤ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምር ነው፡፡ በወቅቱ ውድድሩን በማሸነፉ ከተበረከተለት 150 ሺ ብር ተሸራርፎ የቀረውን 80 ሺ ብር እንዲሁም ከመንግሥት ያገኘውን መጠነኛ የማምረቻ ቦታ ተጠቅሞ ኤቲ ደብሊው ማኑፋክቸሪንግን መመስረት ችሏል፡፡

በጥረቱ ያገኘውን ዕድል ተጠቅሞ ከሽመና ማሽን በተጨማሪ በተለያዩ ዘርፎች አስፈላጊ የሆኑ ማሽኖችን ማምረት የጀመረው አቶ አይሸሽም፤ ወደ ገበያው ለመግባትም ቢሆን ብዙ ጥረት ማድረግን አልጠየቀውም፡፡ ለእዚህ ምክንያቱ ደግሞ ለሥራው ጥራት አቅሙን በሙሉ አሟጦ መጠቀም በመቻሉ ነው፡፡ ‹‹ሰው ከሠራ ለሥራው ጥራት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት›› የሚል ጠንካራ እምነትም አለው፡፡ ይህ አመለካከቱ ትርጉም ያለው ሥራ መሥራት እንዲችልና ውጤታማ እንዲሆን እንዳደረገው ይናገራል፡፡

መነሻውን በሽመና ማሽን ያድርግ እንጂ ሌሎች የፈጠራ ሥራዎችን የሚሠራው አቶ አይሸሽም፤ የሰራው የሽመና ማሽን ለሸማኔው በስፋት ተደራሽ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ያም ቢሆን ታዲያ በሚፈለገው ልክ ሊሄድለት ስላልቻለ የሽመና ማሽን ማምረቱን ገታ በማድረግ በሌሎች የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች ማምረት ስራ በመሰማራት የደረቅ ሳሙናና ዲተርጀንት ፈሳሽ ሳሙና ማምረቻ፣ የቆዳ ውጤቶችን ማምረት የሚያስችሉ፣ ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ ክሬሸርና እንዲሁም ለግብርና ጠቃሚ የሆኑ ማሽኖችን በማምረት ብዙዎች ዘንድ ተደራሽ መሆን ችሏል፡፡

‹‹ኤቲ ደብሊው ማኑፋክቸሪንግ የተለያዩ ማሽኖችን በማምረቱ በአንድ አይነት የማሽን ምርት አይታወቅም›› የሚለው አቶ አይሸሽም፤ በሁሉም የማሽነሪ ምርቶች በየእለቱ እድገትና ለውጥ ማስመዝገብ መቻሉንም ይናገራል፡፡ ውጤት እያስመዘገበና እያደገ የመጣው ኤቲ ደብሊው ማኑፋክቸሪንግ ቀድሞ ካገኘው የማምረቻ ቦታ የተሻለ ስፋት ያለው ቦታ ተወዳድሮ ማግኘቱንም ይጠቅሳል፡፡

መንግሥት በማኑፋክቸሪን ዘርፍ ለተሰማሩና ቢታገዙ የተሻለ ውጤት ማምጣት ይችላሉ፤ ተኪ ምርቶችን ያመርታሉ በሚል ባዘጋጀው አገር አቀፍ ውድድር የተለያዩ መስፈርቶችን ማሟላት የቻለው ኤቲ ደብሊው ማኑፋክቸሪንግ፣ አገር አቀፍ የማኑፋክቸሪንግ ውድድሩ አሸናፊ በመሆን ሰሚት አካባቢ 500 ካሬ ሜትር የተገነባ እንዲሁም ማስፋፊያ መሥራት የሚያስችል ተጨማሪ ቦታ ተመጣጣኝ በሆነ ክፍያ ከመንግሥት ማግኘት ችሏል፡፡ ይህ ትልቅ ድጋፍና ማበረታቻ በማግኘቱ መንግሥትን የሚያመሰግነው አቶ አይሸሽም፤ ሌሎችም ብዙ ጥረት የሚያደርጉና ጥቂት እገዛ ቢያገኙ ብዙ መሥራት የሚችሉ ስለመኖራቸው ተናግሯል፡፡

ኤቲ ደብሊው ማኑፋክቸሪንግ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የሚያመርታቸውን ማሽኖች እያሳደገ ከመሄዱ በተጨማሪ ለሠራተኞቹ የተለያዩና በመደበኛው ትምህርት የማያገኙዋቸውን አይነት ስልጠናዎች እንደሚሰጥም ይገልጻል፡፡ በተለይም በውጭው ዓለም ያገኘውን ዕውቀት ስልጠና በመስጠት ለሠራተኞቹ እያጋራ መሆኑን ይናገራል፡፡ አብዛኞቹ ሠራተኞች ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ የወጡ እንደመሆናቸው ያላቸውን መሰረታዊ እውቀት ተጠቅመው ተጨማሪ የፈጠራ ሥራዎችን መሥራት እንዲችሉ ትልቅ አዝዣም ያደርጋል፡፡ ለአብነትም ብዙ እንጀራ በአንድ ጊዜ መጋገር በሚያስችለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንጀራ ፕሮጀክት ላይ በአንድ ጊዜ ከፍተኛ መጠን ያለው አብሲት ማውጣት የሚያስችል ማሽን ዲዛይን ሠርተው አስረክቧል፡፡

ከአገር ውስጥ በተጨማሪ በውጭ አገር ከውስጥ በመነጨ ፍላጎት ደስ እያለው የተከታተለው ትምህርት ዛሬ የተለያዩ የግብርና፣ የጽዳት፣ የጨርቃጨርቅ፣ የኮንስትራክሽንና ሌሎች የተለያዩ የማምረቻ መሳሪያዎችን ማምረትና ማባዛት አስችሎታል

‹‹ሁሉም ነገር ከቻይና መምጣት የለበትም›› የሚለው አቶ አይሸሽም፤ መሰል የፈጠራ ሥራዎችን መንግሥት እንዲያበረታታም ጠይቋል፡፡ ወሳኝ ከሆኑ ምርቶች ውጭ ያሉት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መፍቀድ እንደሌለበት ሲያስረዳም አብዛኛዎቹ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች እዚሁ በአገር ውስጥ መሠራት የሚችሉ መሆናቸውን አስታውቋል፡፡ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ምርቶች በአገር ውስጥ መመረት እንዲችሉ ሲደረግ ጠቀሜታው ድርብ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ የውጭ ምንዛሪን ከማስቀረት ባለፈ ምርቶቹን በሥራ ዕድል ፈጠራ የሚኖረው አበርክቶ እጅግ የላቀ ነው ብሏል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የሰው ሃብትን ጨምሮ በርካታ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ሃብቶች ስለመኖራቸው የጠቀሰው አቶ አይሸሽም፤ በአንድ ወቅት ተግባራዊ የሆነውን 70/30 የትምህርት ፖሊሲ ለዘርፉ የሰው ኃይል ልማት አስተዋፅኦ አድርጓል ብለው የሚያምኑት አቶ አይሸሽም፣ ፖሊሲው ምን ደረጃ ላይ ነው ብሎ መፈተሽ ተገቢ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡ በዚህ መንገድ የሰው ኃይሉን ወደ ሥራ ለማስገባትም አምራች ኢንዱስትሪዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ በተለይም አምራች ኢንዱስትሪዎች ከማምረት ባለፈ እንዴት ማምረት እንደሚቻል ዕውቀት በማሸጋገር አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲበራከቱ ማድረግ እንደሚጠበቅም ይጠቁማል፡፡ በዚህ እሳቤ መሥራት ሲቻል ኢንደስትሪው ያድጋል፤ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ይቻላል ይላል፡፡

ኤቲ ደብሊው ማኑፋክቸሪንግ ማሽኖችን ሲያመርት በዘርፉ የሰለጠኑ 20 የሚደርሱ ባለሙያዎችን በቋሚነት ቀጥሮ ሲሆን፣ እንደአስፈላጊነቱ በጊዜያዊነት የሚያሰራቸው ሠራተኞችም አሉት፡፡ ባለሙያዎቹ ከተፈጠረላቸው የሥራ ዕድል በተጨማሪ ሙያቸውን ማሻሻልና ማሳደግ እንዲችሉ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡ ድርጅቱ የማሽነሪ ምርቶቹን በሁለት መንገድ ለገበያ ተደራሽ ያደርጋል፤ አንደኛው 85 በመቶ ያህሉን ትዕዛዝ ተቀብሎ ያመርታል፤ 15 በመቶ ያህሉን ደግሞ ጥናትን መሰረት በማድረግ አዳዲስ ማሽነሪዎችን ለማሳያነት እያመረተ ያቀርባል፡፡

ድርጅቱ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የማሽነሪ ዲዛይኖችን በመመልከት አብዝቶ ማምረት እንደሚችልም አቶ አይሸሽም ጠቁሟል፡፡ ለአብነትም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በጋራ ያለሙትን የስንዴ መውቂያ ማሽን አምራች ኢንዱስትሪዎች አባዝተው ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲያደርጉ ካደረጋቸው መካከል የአቶ አይሸሽም ድርጅት ነው፤ ይህ የመንግስት እርምጃ ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና የሚበረታታ መሆኑንም ገልጧል፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ስንዴ በስፋት በማምረት ትልቅ ውጤት እያስመዘገበች መሆኗን ጠቅሶ፣ የስንዴ መውቂያ ማሽን ዲዛይኑን ለማባዛትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን አጫውቶናል፡፡

ሁለቱ ተቋማት አንድ ብለው የጀመሩትን ሥራ ማስቀጠል ይቻላል የሚለው አቶ አይሸሽም፤ በተለይም ግብርና ሚኒስቴር እንዲህ አይነት ሥራዎችን መቀበልና ማበረታታት ከቻለ ግብርናውን ማዘመን እንደሚቻል ነው ያመላከተው፡፡ ለዚህም እርሱ በግሉ በዘመናዊ መንገድ ማረስ የሚያስችሉ አነስተኛና ከበሬ ይልቅ ውጤታማ የሆኑ በግፊ የሚያርሱ ስድስት የሚደርሱ ግብርናውን የሚያግዙ የማሽን ዲዛይኖች እንዳሉትም ጠቁሟል፡፡ ቴክኖሎጂውን ከማልማት ባለፈ መጠቀምና ማለማመድ ላይ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ከቻለ በተለይም ግብርና ሚኒስቴር በዚህ ላይ ፍላጎቱ ካለው ዲዛይኖቹን ወደ ተግባር በማምጣት የተሻለ ሥራ መስራት እንደሚቻል አመላክቷል፡፡

ኤቲ ደብሊው ማኑፋክቸሪንግ ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፤ በመደበኛነት በዓላትን ጠብቆ ሰዎች ምግብ እንዲመገቡ ከማድረግ በተጨማሪ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው የሥራ ዕድል ያላገኙ የአካባቢው ልጆች እንዲሰለጥኑና እንዲቀጠሩ በማድረግ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን አቶ አይሸሽም ገልጿል፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የግንባታ ዘርፉን የግብአት ማነቆ ለመፍታት - የጥናቱና የባለሙያው ዕይታ

ስምስም መንግሥቱ



በሀገሪቱ ግንባታ በስፋት ይስተዋላል፤ ከፍተኛ የግንባታ ፍላጎት እንዳለም ይገለጻል። በመንግስት የሚካሄዱ የመሰረተ ልማትና ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶች፣ በግሉ ዘርፍ የሚካሄዱ የመኖሪያ ቤቶችና የሪልስቴት ህንፃዎች፣ ሆቴሎች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ወዘተ. ግንባታዎች ለእዚህ በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በእዚህ ላይ ህዝቡ የሚያካሂዳቸው የመኖሪያ ቤትና የንግድ ተቋማት ግንባታዎች በርካታ አሉ።

ግንባታው በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል። የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ በአስር ዓመቱ የመንግስት እቅድም በመንገድ፣ በባቡር መስመር፣ በመኖሪያ ቤት፣ ወዘተ ሰፋፊ የግንባታ ስራዎች ይካሄዳሉ። በየቦታው የሚካሄዱ ግንባታዎች፣ የሲሚንቶ፣ የብረትና የመሳሰሉት የግንባታ ግብአቶች ፍላጎትና እጥረት የግንባታውን መስፋፋት ከሚጠቁሙት መካከል ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የግንባታው ሥራ እያደገና እየጨመረ ሲሄድ ለግንባታው የሚያስፈልጉ ግብአቶችም መጨመር ይኖርባቸዋል፤ ግብአቶቹ ከወቅቱ ጋር በጥራትና በመጠን በጊዜ መቅረብ ይኖርባቸዋል። ይሁንና የግንባታ ግብአት በማቅረብ በኩል ሰፊ ክፍተት እንዳለ ይታወቃል። ይህን ጉዳይ የዘርፉ ተዋንያን ሁሌም ያነሳሉ።

በዚህ ወቅት በኮንስትራክሽን ዘርፉ ቅሬታ እያስነሱ ከሚገኙት መካከል ለግንባታ የሚውሉ ግብአቶች አለመገኘታቸውና በወቅቱ እየቀረቡ አለመሆናቸው ነው። ለግንባታው ዋና አስፈላጊ የሆነው የሲሚንቶ አቅርቦትም እንዲሁ በከፍተኛ ሁኔታ ቅሬታ ሲነሳበት ቆይቷል። በሲሚንቶ አቅርቦት ላይ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በተለያዩ ጊዜያት መመሪያዎችን ቢያወጣም ችግሩ አሁንም እንደቀጠለ ነው። በግዥ ከውጭ በማስገባት አገልግሎት ላይ የሚውሉ በተለይም እንደ ህንጻ ማጠናቀቂያ ያሉ ግብአቶች በውጭ ምንዛሪ እጥረት እንደ ልብ አለመገኘታቸው፣ ቢገኙም በዋጋም የሚቀመሱ አለመሆናቸው ከግንባታው ጋር የሚጣጣም አቅርቦት እንደሌለ እንደ አንድ ምክንያት ይጠቀሳል።

ከግንባታ ግብአት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አንድ የዳሰሳ ጥናት በቅርቡ ተደርጓል። ጥናቱ የለያቸውን ችግሮች፣በአጭር ጊዜና በረጅም ጊዜ ያመላከታቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች ጥናቱን ያካሄዱት በሚኒስቴሩ የግንባታ ግብአት ልማት አቅርቦትና ጥራት ኤክስፐርት ኢንጂነር ዘሪሁን ዘገየን ጠይቀናቸው እንደሚከተለው ማብራሪያ ሰጥተውናል።

ኢንጂነር ዘሪሁን እንደገለጹልን፤ የዳሰሳ ጥናቱ የሲሚንቶ፣ የብረታብረትና የግንባታ የማጠናቀቂያ ግብአቶች አቅርቦትን የሚደግፍ የፖሊሲ ግብአት የሚሆን ምክረሀሳብ ለማቅረብ የተዘጋጀ ነው፤ በ2006 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለውን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ደግሞ የግንባታው ዘርፍ የግንባታ ግብአት አቅርቦት ማነቆ የሚታይበት ሆኗል። ለችግሩ መከሰት መንስኤዎቹ ምን እንደሆኑ፣ የጥናቱ አስፈላጊነትና መሠረታዊ ዓላማ፣ እንዲሁም ጥናቱ ሊያስገኛቸው የሚችሉ ውጤቶች ምንድናቸው የሚለውን ያካተተ የዳሰሳ ጥናት ነው የተካሄደው።

ለግንባታው የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ከሚባሉት መካከል ሲሚንቶ፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮን ጨምሮ ብረታብረት እንዲሁም እንደ ሴራሚክ፣ ታይልስ፣ የመፀዳጃ ቤት የግንባታ ማጠናቀቂያና ቀለም ግብአቶች አቅርቦት በግንባታ ኢንዱስትሪው ላይ ሰፊ ክፍተት እየፈጠረ እንደሆነ የጠቆሙት ኢንጂነር ዘሪሁን፤ እነዚህን መሠረት በማድረግም የግንባታ ግብአት ስትራቴጂክ በሚል በሶስት ደረጃ በመክፈል ጥናቱ መሰራቱን ጠቁመዋል። ግብአቶቹ ስትራቴጂክ ተብለው የተያዙበት ዋናው መነሻም የግብአቶቹ ወጭ ከፍተኛ በመሆኑ እንደሆነ አመልክተዋል።

በነዚህ ግብአቶች ላይ የሚስተዋለውን ክፍተት እንዲሁም መንግሥት በነዚህ ላይ ጣልቃ ገብቶ ኢኮኖሚውን እንዴት ሊያስተካክለው ይችላል በሚል ለሚዘጋጀው ፖሊሲ ምክረሀሳብ ለመስጠት የግንባታ ግብአት ጉዳይ በዳሰሳ ጥናቱ በደንብ መታየቱን ገልጸዋል።

እንደ ኢንጂነር ዘሪሁን ማብራሪያ፤ በግንባታ ግብአቶቹ አቅርቦት ላይ እየተስተዋለ ያለው ክፍተት የግንባታ ሥራዎች በወቅቱ እንዳይጠናቀቁ፣ በጥራትም እንዳይሰሩ እያደረገ ይገኛል፤ ይህም በዋናነት ከሚታዩ ችግሮች መካከል ይጠቀሳል። ይህ የአቅርቦት ክፍተት በሥራው ላይ በስፋት ተሰማርቶ የነበረውን የሰው ኃይል ከሥራ ውጭ በማድረግም አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። በአሁኑ ጊዜም በሺዎች የሚቆጠር የሰው ኃይል ያለሥራ ተቀምጧል፤ ቤተሰቡም ተጎጂ ሆኗል። በዘርፉ ላይ እየተስተዋለ ያለውን ተደራራቢ ችግር እንዲህ በጥናት በመለየት መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

እጥረቱ እንዲከሰት ምክንያት የሆኑትንም ጥናቱ አመላክቷል፤ ለአብነት ካመላከታቸው አንዱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በአቅማቸው ልክ ማምረት ካለመቻል ጋር የተያያዘው ነው። ለፋብሪካዎቹ የማምረት አቅም መቀነስ አንዱ ለሥራ የሚጠቀሙባቸው ማሽኖች በግዥ ከውጭ የሚገቡ መሆናቸው ናቸው። አሁን ባለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት አዲስ ማሽንም ሆነ የመለዋወጫ እቃ ግዥ ለመፈፀም አያስችላቸውም። ሌላው በፋብሪካዎቹ በኩል የሚነሳው ሥራ ላይ ያሉትን ማሽኖች መጠገን የሚችል ባለሙያ አለመኖርም ነው።

እነዚህ ተግዳሮቶች በፋብሪካዎቹ የማምረት አቅም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። በ2010 ዓ.ም በዓመት ይመረት የነበረው ሲሚንቶ ስምንት ነጥብ አራት ሚሊዮን ቶን ነበር። ይህ አሀዝ አሁን ላይ ወደ አምስት ነጥብ አምስት ዝቅ ብሏል። ከፍላጎቱ 20 በመቶውን እንኳ ያልሞላ ማለት ነው። ፋብሪካዎቹ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ እያመረቱ የነበሩት ከማምረት አቅማቸው 49 ነጥብ 6 በመቶውን ነበር። በአጠቃላይ ከ50 በመቶ በታች በማምረት ላይ ይገኛሉ። በተመሳሳይ በብረት ምርት ላይም ችግሩ እየታየ ነው።

በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ለግንባታው ዘርፍ ከሚያስፈልገው ግብአት 85 በመቶ የሚሆነው ከውጭ በግዥ የሚገባ ነው። መንግሥት ይህን ችግር የተለየ ሁኔታ እንዲያመቻች ይጠበቅበታል። ነገር ግን ያጋጠመው የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና የገንዘብ የመግዛት አቅም ማነስ የግንባታ ግብአት በአግባቡ ተደራሽ እንዳይሆን አድርጎታል።

ከጥራት አንጻርም እንዲሁ ጥናቱ ክፍተቶችን አመላክቷል። ኢንጂነር ዘሪሁን በዚህ ላይ በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ በተለይ የግንባታ ሥራ ማጠናቀቂያ የሆኑት እንደ ሴራሚክ፣ ታይልስና የመፀዳጃቤት እቃዎች እንዲሁም ቀለምና ለመስኮትና ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ የመስታወት ግብአቶች በሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ ተመርተው ይቀርባሉ። ለእነዚህ አገልግሎቶች የሚውሉ ግብአቶችን 99 በመቶውን በሀገር ውስጥ ምርት መሸፈን ይቻላል። ይሁን እንጂ በጥራት አምርቶ ማቅረብ ላይ ክፍተት እንዳለባቸው በስፋት ይነሳል። በጥራት መጓደል ምክንያትም ወደ ውጭ የማማተር ሁኔታ ተፈጥሯል። ይሄ ደግሞ የሀገር ውስጥ አምራቾች እንዳይበረታቱም ምክንያት እየሆነ ነው።

የኃይል አቅርቦት መቆራረጥም በሀገር ውስጥ አምራቾች ላይ እያሳደረ ያለው ተጽዕኖ ሌላው ተግዳሮት እንደሆነም ኢንጂነር ዘሪሁን ጠቁመዋል። የኃይል መቆራረጡ ፋብሪካዎች በአቅማቸው ልክ እንዳያመርቱ እንዳደረጋቸው ፋብሪካዎቹ በሚገኙባቸው አካባቢዎች ሄዶ በማየት ማረጋገጥ መቻሉንም አመልክተዋል።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ያለው ያለመረጋጋትና የፀጥታ ችግርም በተመሳሳይ ለዘርፉ ተግዳሮት መሆኑን ነው ኢንጂነሩ የጠቀሱት። የፀጥታው ችግር በፋብሪካዎች ላስከተለው ችግር አንዱ ማሳያ አርገው የጠቀሱት በሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት ሳቢያ በትግራይ ክልል የሚገኘው መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሥራ እንዲያቆም መገደዱን ነው። ፋብሪካው በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት በዓመት ወደ ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊየን ቶን የማምረት አቅም ነበረው።

የዋጋ ንረት ሲከሰት ለመከላከል የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖር ሌላው የዘርፉ ችግር መሆኑን ኢንጂነሩ ጠቅሰዋል። በአመራር ኃላፊነት ላይ ያሉት አካላት አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ መፍትሄ አለመስጠታቸው ለችግሩ መባባስ አንዱ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል።

ግብአቱን በግዥ ከውጭ ለማስገባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ በሀገር ውስጥም የሚመረተው በጥራት አለመቅረብና የፀጥታ ችግሮች፣ በመካከል ላይ ያለ ደላላ ለጥናቱ መነሻ ሆነው ይቅረቡ እንጂ፣ ችግሩ እየተንከባለለ መጥቶ አሁን ላይ የከፋ ደረጃ ላይ የደረሰ እንደሆነ ይታወቃል።

በተለይ ደግሞ በሀገር ውስጥ አቅም በመፍጠር ላይም የትኩረት ማነስ መኖሩ እንደ አንድ ምክንያት ይነሳል። እንዲህ ያሉ ክፍተቶች በጊዜ በጥናት ተለይተው ለምን መፍትሄ ሳይሰጣቸው ቆየ የሚል ጥያቄ ኢንጂነር ዘሪሁን አንስተንላቸው፤ በ2005 ዓ.ም እና 2007 ዓ.ም ሲሚንቶ በሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ እየተመረተ እንደነበር ጠቅሰው፣ ከውጭ በግዥ እንዳይገባ እግድ ተጥሎ እንደነበር ገልጸዋል። ከ2005 ዓ.ም በኋላ የግንባታው ዘርፍ በከፍተኛ ሁኔታ መስፋፋትና በተለይም የጋራ መኖሪያ ቤቶች እና የቀላል ባቡር የመሠረተ ልማት ግንባታ የግብአቱን ፍላጎት ከፍ እንዳደረገው ይጠቅሳሉ። ይህም ሆኖ በሀገር ውስጥ ምርት የግንባታ ፍላጎት ይሟላ እንደነበር ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ የግንባታ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሆኑንና በየዓመቱም ወደ 400ሺ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ለማከናወን እቅድ በመያዙ፣የመስኖ ግድቦች እና ሌሎችም ግንባታዎች በስፋት መኖራቸውን በመጠቆም የሲሚንቶ ግብአት አስፈላጊነት ወሳኝ እንደሆነም ኢንጂነሩ ያመለከቱት። ይህን ፍላጎት ለማሟላትም በሀገር ውስጥ ያለውን ሀብት አሟጦ መጠቀምና በቴክኖሎጂ መታገዝ እንደሚገባም አመልክተዋል።

የዳሰሳ ጥናቱ ያመላከተውን የመፍትሄ ሀሳብ በተመለከተም ኢንጂነር ዘሪሁን እንደጠቆሙት፤ በጥናቱ የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶች ምን መሆን እንዳለባቸው እንዲሁም ከማን ምን ይጠበቃል፣ ክልሎችና ፌዴራል መንግስት አብረው መስራት ያለባቸው መሆኑ ተመላክቷል። በተለይ ተናብቦ መሥራት ላይ ለአብነትም ማዕድን ሚኒስቴር ለግብአት የሚውሉ ጥሬ እቃዎች የሚገኙባቸውን አካባቢዎች በማመላከትና ለባለሀብቶች መረጃ ምቹ በማድረግ፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ስርጭቱ ላይ ዲጂታል የሆነ የአሰራር ሥርአት ዘርግቶ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አስታውቀዋል።

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ጥሬ እቃ በማቅረብና በክህሎት እንዲበቁ በማድረግ የበኩሉን ድርሻ የሚወጣበት አግባብ መኖሩም በጥናቱ ተመላክቷል። ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ደግሞ የአሰራር ሥርአቶችንና ደረጃዎችን፣ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ምቹ ማድረግ፣ ጥናቶችን ማካሄድ አዋጆች ላይ ትኩረቱን እንዲያጠናክር ተጠቁሟል።

ዘርፉ ያስከተለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት በአጭርና በረጅም ጊዜ በጥናቱ የተመላከተውንም እንዳስረዱት፤ በአጭር ጊዜ ዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ለተወሰነ ጊዜ በልዩ ትኩረት የሚያገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት ሲሚንቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ከውጭ ገበያ ማግኘት የሚቻልበትን አማራጭ እንዲፈለግ ተጠቁሟል። የብረት ግብአትንም እንዲሁ የብረት ፍላጎትን በ70 በመቶ ሊቀንሱ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመሥራት እየተደረገ ያለውን ጥረት ተግባራዊ ማድረግ በሚል የተቀመጠ መፍትሄም ተጠቁሟል።

በረጅም ጊዜ ደግሞ በልማት ሥራ ላይ ትኩረት ማድረግ ነው። ለግብአቱ የሚሆኑ ማዕድናት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ለማምረትና ለማጓጓዝ የሚመቹ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት ዘርፉ ዘላቂ መፍትሄ የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲመቻች በጥናቱ ምክረሀሳብ ተቀምጧል።

ጥናቶችን ወደተግባር በመቀየር በኩል ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ ከዚህ ቀደም ያሉ ተሞክሮዎችንም ኢንጂነር ዘሪሁን አንስተንላቸው፣ ጥናቱ ላይ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲያዝና ጥናቱም በደንብ እንዲዳብር ዘርፉ ላይ በተለያየ ደረጃ እየሰሩ ካሉ ባለድርሻ አካላት እና አስፈጻሚ ተቋማት ጋር ምክክር መደረጉን ገልጸዋል። በዚህ መልኩ የተከናወነው ተግባር ጥናቱ ተግባራዊ ይሆናል የሚል እምነት እንዳላቸው ምላሽ ሰጥተዋል።

በጉዳዩ ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተባባሪ ፕሮፌሰርና የዘርፉ አማካሪ ዶክተር ውብሸት ዝቅአለ የጠየቅናቸው በጥናቱ ላይ መረጃ ባይኖራቸውም ዘርፉ ላይ የሚስተዋለውን ችግር በቅርበት እንደሚያውቁት ይገልፃሉ። አብዛኛው ግብአት ከውጭ በግዥ የሚፈጸም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለግዥ የሚሆን የውጭ ምንዛሪ ማግኘትና የግዥ መጓተት በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ጫና በመፍጠር መዘግየት እንዲከሰት ምክንያት መሆኑን ጠቅሰዋል። የዘርፉን ችግሮች የሚፈቱ መንገዶች ግን መኖራቸውንና መፍትሄው ላይ ትኩረት አድርጎ መስራቱ የተሻለ እንደሆነም ጠቁመዋል።

እንደ ተባባሪ ፕሮፌሰሩ ማብራሪያ፤ ለግንባታው ሥራ የብረት ግብአትን መቀነስ እንጂ ማስቀረት አይቻልም። ብረት አስፈላጊ ግብአት ነው። ለአብነትም ከዓለም ተሞክሮ የኖርዝ ኮሪያን ተሞክሮ አንስተዋል። ሀገሪቱ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ የብረት ግብአት ችግር እንደነበረባት በማውሳት፤ ሀገሪቱ አማራጮችን በመጠቀም የብረት ግብአትን ለመቀነስ ጥረት ማድረጓን ገልጸዋል። እንዲህ ያሉ ተሞክሮዎችን ማየቱ አስፈላጊ እንደሆነ ነው ምክረሀሳብ የሰጡት።

በቅድመ ግንባታ በሚከናወን የዲዛይን ሥራ ላይም ግብአትን ለመቀነስ የሚያስችል አሰራር መጠቀም የሚቻልበት እድል መኖሩንም ዶክተር ውብሸት ገልፀዋል። ለእዚህም ለአዲሱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህንፃ ግድግዳ የዋሉትን ግብአቶች ለአብነት ጠቅሰዋል።

የሀገርንም አቅም ያገናዘበ አካሄድ መከተል ዘርፉ ላይ የሚስተዋለውን ጫና ይቀንሳል የሚሉት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ የግንባታ ግብአት የግድ ብሎኬት ወይንም ኮንክሪት መሆን አለበት የሚል እምነት እንደሌላቸው ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንዳሉት በአፈር ግብአት ከአንድ ወለል በላይ ቤት የገነቡ ሀገራት ተሞክሮ መኖሩንና በኢትዮጵያም ቢሆን በአፈር የተሰሩ ጥሩ ቤቶች መኖራቸውን አመልክተዋል። በብሎኬት ግንባታ ማከናወን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች አስገዳጅ መሆን እንደሌለበትና እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ መፍትሄ መስጠት እንደሚቻል ነው ሀሳብ የሰጡት።

ከሀገር አቅም ጋር አያይዞ መፍትሄ መስጠቱ ከማን ምን ይጠበቃል የሚል ጥያቄም አንስተንላቸው በሰጡት ምላሽ፤ ትልቁ ነገር ግንዛቤ መፍጠርና ይህ ከሆነ በኋላ ደግሞ የአሰራር ሥርአት እንዲኖር ማድረግና እንዲህ ከተሰራ መተግበሩ እንደማያስቸግር ነው ያስረዱት።

‹‹በግንባታ ሥራ ላይ በአስገንቢው በኩል በውበት የተለያየ ምርጫ ወይንም ፍላጎት እንደሚኖር ይገመታል። የግድ በዚህ መንገድ ካልሰራን በሚል ግንባታዎችን በማዘግየት የሀገር ኢኮኖሚ መጉዳት ተገቢ ነው ብዬ አላምንም›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ የጭቃ ቤት በብሎኬት ከተሰራ ቤት ያንሳል ያለው ማነው? የሚል የመከራከሪያ ሀሳብ በተለያዩ መድረኮች ላይ ባገኙት አጋጣሚ ማንሳታቸውን ነው የሚናገሩት። ፍላጎትን ወደ መገደብ መሄድ እንደሚገባ አስረድተዋል። ፕሮጀክት ከሚያሟላቸው ስድስት ነጥቦች ውስጥም አንዱ ከአካባቢ ጋር የተጣጣመ መሆንን እንደሆነም ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የወጪ ንግዱን ፈተናዎች በማለፍ የዘርፉን ዕቅድ ማሳካት ይገባል!

ሀገሪቱ ለጀመረችው ልማት ስኬት የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ሸቀጦችን በጥራትና በብዛት ለዓለም ገበያ በማቅረብ ተወዳዳሪ መሆን ይጠበቅባታል። ይህንን ማድረግ አጠቃላይ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ከማነቃቃት ባለፈ፤ ትርጉም ያለው ዕድገት ለማስመዝገብም ዋነኛ አቅም ነው፡፡

ከዚህ የተነሳም መንግስት ሀገራዊ የውጪ ምንዛሪ ግኝቶችን ማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ስትራቴጂክ ተግባራትን ሲያከናው ቢቆይም፤ በዚህ ዓመት በተለያዩ ሀገራዊና ዓለምአቀፋዊ ምክንያቶች በወጪ ንግድ ላይ የታቀደውን ያህል ውጤታማ መሆን አልተቻለም። ክፍተቱ ሀገሪቱ ካላት የውጪ ምንዛሪ ግኝቶችን ማሳደግ የሚያስችሉ ብዙ አማራጮች አንጻር ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ከተቻለ በመጪዎቹ ዓመታት ሊለወጥ እንደሚችል ይታመናል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከትናንት በስቲያ ባካሄደው 28ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸምን አስመልክቶ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀሩቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ የኤክስፖርት ገቢን በተመለከተ እንዳስታወቁት፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከወጪ ንግድ የሚገኘው ገቢ መሻሻሎች ቢያሳይም፤ በዚህ ዓመት ግን ከአምናው በ11 በመቶ ቀንሷል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ የአግልገሎት ዘርፉ 14 በመቶ፣ ሬሚታንስ በአራት ነጥብ ስድስት በመቶ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ደግሞ በአስር ነጥብ አራት በመቶ ማደጉን፤ ሁሉም ሲደመሩ የውጭ ምንዛሬ ግኝቱ ከአምናው ያነሰ እንዳልሆነም ጠቁመዋል፡፡ በእቅዱ በሸቀጦች ኤክስፖርት የተቀመጠው ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ ሊመጣ ይችል እንደነበርም ተናግረዋል፡፡

በሸቀጥ ኤክስፖርት ላይ ለታየው ቅናሽ የወርቅ ህገወጥ ግብይት፣ የኮንትሮባንድ መስፋፋት፣ የቡና የዓለም ገበያ ዋጋ መቀነስ በምክንያትነት ተጠቁሟል፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶች በርግጥም ችግሮች መሆናቸውን መንግስት ቀደም ሲልም ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ ችግሮቹን ለመፍታት ሰፋፊ ጥረቶች ቢደረጉም፣ የወጪ ንግዱ ግን ቅናሽ የታየበት ሆኗል፡፡

በርግጥ መንግስት በወርቅ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ህገወጥ ተግባር ለመከላከልና ለመቆጣጠር ግብረ ኃይል አቋቁሞ እየሰራ ነው፡፡ ግብረ ኃይሉ እያከናወነ ባለው ተግባር በተለይ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና ጋምቤላ ክልሎች በህገወጥ የወርቅ ዝውውር ላይ የተሰማሩ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎችና ተባባሪ ኢትዮጵያውያን በቁጥጥር ስር እየዋሉ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ መንግስት የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር እየወሰደ ያለው እርምጃ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የሀገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስ በዚህ በኩል ሰፊ ተልዕኮ ተሰጥቷቸው እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ ይህም እንደ ወርቅ ያሉት ማዕድናት በህገወጥ መንገድ እንዳይመረቱና ከሀገር እንዳይወጡ ከማድረጉ በተጨማሪ፣ ወጪ ኮንትሮባንድ ሸቀጥን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህም ሀገሪቱ ከቁም እንስሳቷ፣ ከጫትና ከሌሎችም ምርቶች ማግኘት ያለባትን የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ሌላው የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ምሰሶ ቡና መሆኑ ይታወቃል፡፡ ባለፈው በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ ከቀረበ ቡና ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር በላይ ተገኝቷል፤ ይህም በቡና የወጪ ንግድ ታሪክ የመጀመሪያው ነበር፡፡ በዚህ ላይ በመመስረት ከዚህ የሚልቅ የውጭ ምንዛሬ ከቡና ለማግኘት ቢታቀድም በዓለም አቀፍ ደረጃ የቡና ዋጋ መቀነስ ሳቢያ እቅዱን ማሳካት አልተቻለም፡፡

የቡና ግብይቱን የሚመራው የቡናና ሻይ ባለስልጣን ለተከሰተው የዋጋ መቀነስና ይህን ተከትሎ ለተፈጠረው የውጭ ምንዛሬ ቅናሽ መፍትሄ እያፈላለገ ይገኛል፡፡ ከባለስልጣኑ የተገኘ መረጃ እንዳመለከተው፤ ተጨማሪ የቡና ምርት መዳረሻ ሀገሮችን ለማፍራት እየተሰራ ነው፡፡ የመዳረሻ ሀገሮችን ለማስፋት እያተካሄደ ያለው እንቅስቃሴ ችግር ለመፍቻ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም የሚሆን ተጨማሪ ገበያ ማግኘት የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል፡፡

ሌሎች ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት በሚታወቁት እንደ አበባ፣ ስጋና የስጋ ውጤቶች፣ የቁም ከብት፣ አትክልትና ፍራፍሬ በመሳሰሉት የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለማሳደግ የሚደረጉ ሀገራዊ ጥረቶች ተጠናክረው ከቀጠሉ፤ በዘርፉ ተጨማሪ አቅም መገንባት የሚያስችል አስቻይ ሁኔታ በስፋት ስለመኖሩ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም፡፡

ከውጪ ንግዱ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ትልቅ የልማት አቅም ከመሆኑ አንጻር፤ ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ ሸቀጦችን በጥራትና በብዛት ማምረት፤ ለተመረቱ ሸቀጦች የተሻለ የገበያ መዳረሻ ማፈላለግ፤ እነዚህ ምርቶች ለኮንትሮባንድ ገበያ ተጋላጭ እንዳይሆኑ በጠንካራ ዲሲፕሊን የሚመራ የቁጥጥር ስርአት መፍጠር ወሳኝ ነው፡፡ የገበያ ደንቃራዎችን እና በምርታማነት ላይ ያሉ ፈተናዎችን አሸንፎ መውጣት የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠርም ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ መንግስትና ሁሉም የወጪ ንግዱ ተዋንያን ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል!።


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሳደጉ ንቅናቄ ስኬታማ እንዲሆን

**መርድ ክፍሉ**

በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ በአብዛኛው የትምህርት ስርአቱ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር የተሳሰረ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ በወቅቱም ቤተክርስቲያኗ ማንበብና መጻፍን ጨምሮ መንፈሳዊ አስተምህሮዎችን ያካተቱ የተለያዩ ትምህርቶችን ስትሰጥ ቆይታለች፡፡

ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረ በኋላ ግን የትምህርት ስርአቱ ሀገራዊ ተልእኮ ተቀርጾለት የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት በስፋት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ በዚህም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የተማሩ ዜጎችን በማፍራት ሀገሪቱ አሁን ላለችበት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገት እንድትደርስ የማይተካ አስተዋፅኦ አበርክቷል ።

በቀደመው ዘመን አብዛኞቹ ዜጎች በበቤተክህነት የትምህርት ስርአት ውስጥ ከማለፋቸው የተነሳ አንድ ልጅ እስከ ዳዊት መድገም የደረሰ ትምህርት ካለው በቂ ተደርጎ ይቆጠራል፤ ይህ ደግሞ በአብዛኛው ማንበብና መጻፍን ታሳቢ ያደረገ እንደነበር ታሪክ ያትታል። በዚህ ውሥጥ ያለፉ ዜጎች ለመንግስት ስራ በቂ ሆነው ይቆጠሩ እንደነበርም እንዲሁ።

በአስራ ዘጠነኛው ክፍለዘመን መግቢያ ጀምሮ በሀገሪቱ ማቆጥቆጥ ከጀመረው ዘመናዊነት /ስልጣን/ አንፃር ትምህርት ከመጣበት ባህላዊ መንገድ ወጥቶ ዘመናዊነት እየተላበሰ ሄዷል። የዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤትም የመጀመሪያው ዘመናዊ ትምህርት ቤት በመሆን አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

ይህንኑ ተከትሎ በ1925 ዓ.ም በመላው ሀገሪቱ 20 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተከፍተው ስራ ቢጀምሩም ፤ የተማሪዎች ቁጥር ግን ከስምንት ሺ መብለጥ አልቻለም ነበር፡፡ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን መንግስት ዘመናዊ ትምህርትን በሀገሪቱ ለማስፋፋት የተደረጉ ጥረቶች እውነታውም ቀይረውታል።

ብዛት ያላቸው ዜጎች ወደ ትምህርት ቤቶች በመሄድ የዘመናዊ ትምህርት ተቋዳሽ መሆን ችሏል። በደርግም ሆነ በኢህአዴግ አስተዳደር ዘመን የትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች የትውልድ መቅረጫ ቦታዎች በመሆናቸው የተሟላ መሰረተ ልማት እንደሚያስፈልጋቸው ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። ቤተ መፅሀፍት፣ ቤተ ሙከራ እንዲሁም ለመማር ማስተማር የሚረዱ ግብዓቶች ሊሟሉላቸው ይገባል፡፡ ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ስለትምህርት ሆነ ውጤታማነቱ አፍን ሞልቶ መነጋገር አይቻልም ።

በርግጥ በኢትዮጵያም የትምህርት ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆን በቀደሙት ጊዜያት በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በየአካባቢው ትምህርት ቤቶችን መገንባት ተጠቃሽ ነው፡፡ ለዚህም በመላው ሀገሪቱ ከ50 ሺ የሚጠጉ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው መገኘታቸው ተጨባጭ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። መንግስትና አጠቃላይ ማህበረሰቡ ለትምህርት የሰጡትን ትኩረትም አመላካች ነው።

እነዚህ ትምህርት ቤቶች ባላቸው አቅም ዜጎች ለራሳቸውና ለሀገራቸው ከዛም አልፈው ለዓለም ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ አስችለዋል። ሀገርን በዓለም አቀፍ መድረክ ያስጠሩ ስመ ጥሩ ዜጎችን በማፍራትም ባለውለታዎች ሆነዋል።

አሁን አሁን እነዚህ ትምህርት ቤቶች ዘመኑ የሚጠይቀውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ሂደት ውስጥ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ውሎ አድሯል። እንዲያውም በቅርቡ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መረጃ ከትምህርት ቤቶቹ 99ከመቶ የሚሆኑት ለመማር ማስተማሩ ስራ ውጤታማነት የተሟላ ቁመና የላቸውም።

የትምህርት ሚኒስቴር ጥናት እንደሚያሳየው፤ ለመማር ማስተማር ስራው ብቁ ሆነው የተገኙና በዓለም አቀፍ መስፈርቶች በአራተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡት የመንግስት ትምህርት ቤቶች በቁጥር ስድስት ሲሆኑ አህዙ በመቶኛ ሲሰላ ፤ ከ0 ነጥብ 001 በመቶ በታች ናቸው፡፡

010 በመቶ የሚሆኑት ትምህርት ቤቶች ደግሞ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ ከ89 በመቶ በላይ የሚሆኑት በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ለመማር ማስተማር ስራ ምቹ ያልሆኑ እንደሆኑ በጥናቱ ተቀምጧል።

አብዛኛው ትምህርት ቤቶች የመሰረተ ልማት በተለይ የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ የመብራት፣ የቤተ ሙከራ እንዲሁም የመማሪያ ክፍሎች እጥረቶች አሉባቸው፡፡ እነዚህን ክፍተቶች መንግስት ለብቻው ሊደፍናቸው አይችልም ፤ ልድፈናቸውም ብሎ ቢንቀሳቀስ አራትና አምስት አስርት ዓመታትን የሚጠይቁ ናቸው።

አብዛኛው ህብረተሰብ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ልጆቹን የሚያስተምር ቢሆንም ትምህርት ቤቶቹን በባለቤትነት መንፈስ ማስተዳደር አለመቻሉ፤ ለተፈጠረው ችግር በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው። ይህ እውነታ በአዲስ አበባ ሳይቀር /የተሻለ ግንዛቤ አለው በሚባለው ማህበረሰብ /በስፋት ተስተውሏል።

ትምህርት ቤቶቹ ከደረጃ በታች መሆናቸው ተማሪዎች ማግኘት ያለባቸውን እውቀት እንዳያገኙ ፈተና ሆኗል። ችግሩ በተለይ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በይበልጥ ተስተውሏል፡፡ ይህም በትምህርት ጥራት ላይ መሰረታዊ የሚባል ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል።

ችግሩ አሁን ላይ ሀገራት ተግዳሮት የሆነ ሲሆን፤ ችግሩን ለመሻገርም የነቃ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ የሆነበት ታሪካዊ ምእራፍ ውስጥ ገብተናል፡፡ ለዚህም ሰሞኑን በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አመካኝነት ሀገራዊ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ሀገራዊ ንቅናቄ ተጀምረዋል።

ንቅናቄው የእያንዳንዱን ዜጋ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ከሁሉም በላይ የሚጠይቅ፤ በሀገሪቱ የተፈጠረውንና ዋጋ እያስከፈለን ያለውን ትምህርት ጥራት ችግር በመፍታት፤ እንደ ሀገር የጀመርነው የብልጽግና ጉዞ ስኬታማ እንዲሆን የሚኖረው ፋይዳ ከፍያለ ነው።

የትምህርት መሰረተ ልማት ያሟሉ ትምህርት ቤቶች፤ በእውቀት የበለፀገ ትውልድ በመቅረፅ ካላቸው አስተዋጽኦ አንጻር ንቅናቄም ለመጪው ትውልድ ብሩህ ነገዎች መሰረት የመጣል ያህል ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በንቅናቄው ማስጀመሪያ መርሀግብር ላይ፤ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደተናገሩት፤ በየትኛውም የኢትዮጵያ ጫፍ ትምህርታቸውን የተከታሉ ሁሉ ትናንት የተማሩበትን ትምህርት ቤቶች ዛሬ ባስፈላጊው መንገድ መደገፍ አለባቸው።

ድጋፉን በተግባር ለማሳየትም ሁሉም ሰው በሐሳብ፣ በገንዘብ፣ በጉልበት እንዲሁም ያለውን ሁሉ ለትምህርት ቤቶች ማዋል አለበት፡፡ ትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል በሚደረገው ንቅናቄ ተወዳዳሪ አገር የመገንባት ሂደት በመሆኑ ሁሉም ዜጋ በመገንዘብ የንቅናቄው አካል መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ከዚህ አንጻር ንቅናቄ በሙሉ ልብ መደገፍ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ይህን ሀሳብ ተረድተው ግንባር ቀደም ሊሆኑ ይገባል፡፡ ትምህርት ቤቶቹ አሁን ካሉበት የመሰረተ ልማት ክፍተቶች መታደግ ካልተቻለ በእውቀት የዳበረ ትውልድ መፍጠር አይቻልም ፡፡ ይሕ ደግሞ የሀገር ውድቀት ጅማሪ እና ፍጻሜ ነው።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^እስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# እጆች ሲዝሉ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

**ጉልት ቸርቻሪዋ ...**

ከአስፓልቱ ማዶ፣ ከመንገዱ ዳርቻ፣ ከሰዎች ግርግር መሀል አሻግሬ እያየኋት ነው። የተጎሳቆለ ገጽታዋና ፣ አዳፋ ልብሷ አሁንም ከእሷ ናቸው። የልብሷ መቆሸሽ ጉዳይ ስንፍና ያመጣው ችግር አለመሆኑን አውቃለሁ። እንዲህ ይሆን ዘንድ የእንጀራዋ ውሎ፣ የሥራዋ ባህርይ ያስገድዳል።

ዘንድሮን ግን በትካዜና መከፋት ውስጥ መሆኗ አልጠፋኝም። ከፊቷ እንደነገሩ በማዳበሪያ የዘረጋቻቸውን አትክልቶች ቃኘት እያደረገች በሀሳብ ትዋጣለች። አብዛኞቹ እጇ ላይ መበላሸት ጀምረዋል።እነሱ ላይ እያፈጠጠች መልሳ ትካዜ ውስጥ ትገባለች።

አንዳንዴ ያለችበትን ሁሉ የምትረሳ ይመስላል። እንደ ዕንቅልፍ እልም የሚያደርጋት ድካም አብዝቶ ይፈትናታል። በመሀል እንደመባነን ስትነቃ ደግሞ አላፊ አግዳሚውን በዓይኖቿ ትማጸናለች። የያዘችው ድንች፣ ጎመንና ፣ ቃሪያ ዛሬን ተሸጦ ማለቅ አለበት። እንዲህ ካልሆነ ኪሳራዋ ይበዛል፣ በውድ ዋጋ የገዛችው አትክልት በስብሶ ይባክናል።

ሙሪዳን የማውቃት ከጥቂት ዓመታት በፊት በጉልት ሥራዋ ነው። ደንበኛዬ ነች። ዓይነ ሰፊ፣ እጀ ሙሉ የሚሏት ደግ። እሷ ዘንድ ‹‹መርቂበት፣ትንሽ ጣይበት›› ይሉት ጥያቄ የለም።ማንም ሳይላት ቸሩ እጇ ያዛታል። ጨመርመር፣ ጣል ጣል ማድረግን ታውቅበታለች።

ለእኔም ቢሆን ከምገዛት ላይ መረቅረቅ አድርጋ ስለምትሰጠኝ ምርጫዬ ሆናለች። ይህ ብቻ አይደለም። ብሷቷን፣ ችግሯን ስታወራ በግልጽነት ነው።‹‹አህ!›› ብሎ ጀሮውን ለሰጣት ደግሞ ማንነቷን አትደብቅም። ለሚያደምጣት ሁሉ የውስጧን ተንፍሳ ‹‹እፎይ›› ማለት ትወዳለች።

> **አሁን ሙሪዳ እንደትናንቱ አይደለችም። ደርሶ ዕንባ ያንቃታል፣ በቶሎ ይከፋታል። ሁሌም ስለጎጆዋ እረፍት የለሽ ብትሆንም ኑሮና ሕይወት በእጅጉ እየከበዳት ነው። በየጊዜው የሚጨምረው የቤት ኪራይ ሲያሳስባት ውሎ ያድራል።**

**ማንነት በትጋት...**

ሙሪዳ የኑሮ ውጣውረዱ፣ ቤተሰብ የማስተዳደር ጫናው ዐሻራውን ጥሎባታል። ሁሌም እረፍት የለሽ ባተሌ ናት። ማለዳ ወጥታ ቀኑን ስትለፋ ብትውል ‹‹ደከመኝ››ን አታውቅም። ምሽቱን ቤቷ ስትደርስ የጎጆዋ ጣጣ ይቆያታል። እጆቿን የሚናፍቁ ልጆቿ ደጅ ደጇን እያዩ ይጠብቋታል። ቀሪውን ሰዓት ለእነሱ የሚያስፈልገውን ስትስጥ፣ የጎደለውን ስትሞላ፣ ታሳልፋለች።

በእሷ ዘንድ ‹‹መሸ፣ በጊዜ ልተኛ›› ማለት አልተለመደም። ቤተሰቡ ለዕንቅልፍ ጎኑን ሲያሳርፍ የሌሊት ትጋቷ ይጀምራል። ለነገው ውሎ እንጀራውን፣ ወጡን ታዘጋጃለች። ያልታጠበውን፣ የቆሸሸውን ታፀዳለች፣ የጎደለውን ሁሉ ትሞላለች።

ሌሊቱ ተጋምሶ ውድቅቱ ሲዳረስ ድካምና ዕንቅልፍ ገፍትረው ሊጥሏት ይዞሯታል። መቼም ቢሆን እጅ አትስጥም። ከሁሉም እየተጋፋች ፣ የኑሮ ምሰሶዋን ለማቆም፣ የሕይወት ግዴታዋን ለመወጣት ትግተረተራለች። እሷ ሁሌም ለቤተሰቦቿ የሚነድ ሻማ ሆና ብርሃን መለገስ፣ ጨለማን ማብራት ልማዷ ነው። ለቤቷ፣ ለልጆቿ ካሏት ፈጽሞ አትደክምም።

ባለቤቷ እንደሷው ሮጦ ያድራል። የልጅነት ባሏ ነው። ትውውቃቸው ካገር ቤት ይጀምራል። ጉራጌ ምድር ‹‹እነሞር››ን ለቀው አዲስ አበባ ሲመጡ ሁለቱም ሠርተው የመለወጥ፣ ተለውጠው የማደግ ዓላማን ሰንቀው ነበር።ጥንዶቹ በትዳር ዓመታትን ሲገፉ ‹‹አንተ ትብስ፣ አንቺ›› በሚል መተሳሰብ ነው።

ሁለቱም አብረው ተባብረው ጎጇቸውን አቁመዋል። በሦስት ጉልቻ ዘመናቸው ያገኟቸውን ሦስት ልጆች በወጉ እያሳደጉ ነው። እንደነሱ ሳይማሩ እንዳይቀሩ ትምህርት አስጀምረዋቸዋል። ሁሉም ትምህርት ቤት ውለው ይገባሉ። ባልም ቢሆን እሷ በፈለገችው ጊዜ ከሚስቱ ጎን አይርቅም። ገበያ ስትውል በሀሳብ ያግዛታል። ስታማክረው መፍትሔውን ያመጣል።

መከፋት..

ሙሪዳ ሀሰንን ሳውቃት እንደዛሬው በእጅጉ ተጎሳቁላ አይደለም። የኑሮ ውጣውረዱ የሕይወት ጫናው ቢፈትናትም ፈገግታ በሞላው ገጽታዋ ቀኗን በደስታ ስታበራው፣ ስታደምቀው ነበር።

ከሙሪዳ ጋር እንደልማዳችን ጭውውት ይዘናል። እንዳልኳችሁ ከእሷ ለማውራት ብዙ አይከብድም። በቀላሉ ከማንም ለመግባባት የቀረበች ናት። ገጽታዋን በስጋት እያስተዋልኩ እንደሁልጊዜው ስለኑሮና ሕይወቷ ጠየኳት። እንደልማዷ የሆዷን፣ ልትዘረዝርልኝ፣ የልቧን ልታወጋኝ ተዘጋጅታለች። ጠንካራ እጆቿን አየኋቸው። ከቀድሞ በባሰ ጠቁረዋል፣ ሻክረዋል። ንግግሯን ከመጀመሯ በፊት ገጽታዋ ላይ መከፋት ያየሁ መሰለኝ። እንዲህ መሆኑ አያስገርምም።

አሁን ሙሪዳ እንደትናንቱ አይደለችም። ደርሶ ዕንባ ያንቃታል፣ በቶሎ ይከፋታል። ሁሌም ስለጎጆዋ እረፍት የለሽ ብትሆንም ኑሮና ሕይወት በእጅጉ እየከበዳት ነው። በየጊዜው የሚጨምረው የቤት ኪራይ ሲያሳስባት ውሎ ያድራል። ልጆቿ ሁሌም

እጆች... ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# እጆች...

ከገጽ 16 የዞረ

ሮጠው ለሚያድሩት ወላጆቻቸው ተስፋዎች ናቸው። ጥንዶቹ እናት አባት ናቸውና እስካሁን ‹‹እንዲህም እንዲያም›› እያሉ አኑረዋቸዋል።

ሙሪዳን እንደምንም አረጋግቼ ወደራሴ መልሻታለሁ። ዘንድሮ ከወትሮው በተለየ የከፋትን፣ ያስጨነቃትን እውነት ልታወራኝ ጀምራለች። ጭውውታችንን አንድ ሁለት እያልን በወጉ ከመግፋታችን በአካባቢው ድንገቴ ሩጫና ግርግር ተነሳ። እኛን ጨምሮ በስፍራው ያለ ሁሉ ድንጋጤ ቀደመው ።

ወዲያው ሙሪዳ በአሮጌ ማዳበሪያ ከመሬት የዘረጋችውን አትክልት ከወዲያ ወዲህ ጠቅልላ ከአጠገቤ ተፈተለከች። የፍጥነት ሩጫዋ በእጅጉ አስገረመኝ። ከትከሻዋ ያረፈው ቀላል የማይባል ጓዝ ከወደ አንገቷ አጉብጧታል። አሯሯጧ የእመጫት አይመስልም። በአንድ እጇ ልቧን ደግፋ፣ ድንጋጤ በዋጣቸው ዓይኖች ዙሪያዋን እየቃኘች ነው።

እሷን መሰል ነጋዴዎች ከአጠገቧ ቆመዋል። በርከት የሚሉት በእጅና ትከሻቸው የያዙትን ይዘው ከአስፓልት ማዶ ሊሻገሩ ከመኪኖች ጋር ግፊያ ይዘዋል። ሁሉም በሚባል ሁኔታ ስለራሳቸው የሚያስቡ አይመስልም። ከአዳኞቻቸው ለማምምለጥ አደጋውን ችላ እንዳሉት ያስታውቃል።

ጥቂት ቆይቶ ተመሳሳይ ልብስ የለበሱ አራት ደንብ አስከባሪዎች በአካባቢው ታዩ ። በቅርብ ርቀት ሁለት ፖሊሶች ተከትለዋቸዋል። ከሁለቱ አንደኛው በትከሻው ክላሽ የሚሉትን መሣሪያ አንግቷል። አጭር ስለሆነ መሣሪያው ከቁመቱ ጎልቶ እየታየ ነው።

ሰዎቹ በገበያው መሀል አልፈው ራቅ እንዳሉ ሁኔታዎች ተለውጠው የነበረው እንደነበረው ሆኖ ቀጠለ። ከመሬት ጓዛቸውን ያነሱ መልሰው በቦታው ዘረጉ። አስፓልት ተሻግረው የራቁ በፍጥነት ስፍራቸውን ተቆጣጠሩ። ጀምና አካባቢው በአንድ አፍታ ወደሞቀው ግርግርና ትርምሱ ተመለሰ።

**የልብ ወግ...**

ሙሪዳና እኔ ዳግመኛ ተገናኘን። ሁለታችንም ውላችንን አልረሳነውም። ጅምር ወጋችንን ልንቀጥል ወደቀደመው ስፍራ ተመልሰናል። ሙሪዳ ልታወጋኝ የነበረው አንዱ ስጋት ከደቂቃዎች በፊት ያጋጠመውን ዓይነት ሀቅ እንደነበር እየተከዘች ነገረችኝ ።

የእሷ የዓመታት መተዳደሪያ ከመንገድ ዳር ተቀምጦ አትክልት መቸርቸር ነው። ከዚህ ቀድሞ ለገበያ የምታውለውን ግዢ የምታመጣው ፒያሳ ከነበረው አትክልት ተራ ነበር። የዛኔ በማለዳ ወጥታ ግብይቱን ከጨረሰች ሰፈር በሚያደርሳት ታክሲ ጓዟን ይዛ ትገባለች።

በወቅቱ የነበረው የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝና ለእሷም የሚዋጣ በመሆኑ በገበያ ውለዋ አትራፊ የምትባል ነበረች። ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የአትክልት ገበያው ‹‹ጋርመንት›› ወደተባለው አካባቢ ተዛውሯል። እንዲህ መሆኑ ለምትኖርበት ሰፈር የቀረበ ነውና አልተከፋችም።

ገበያው ወደ ጋርመንት በመዘሩ ብቻ ግን ለሙሪዳ ያቀለለላት ሸክም የለም።ዛሬም እንደቀድሞው ማልዳ ከአትክልት ተራው መድረስ ፣ ተሻምታ፣ ከሌቦች ተጋፍታ የተሻለውን መምረጥ ግድ ይላታል። ገበያው ደግሞ እንደትናቱ አይደለም ።በየቀኑ ሽቅብ የሚጎነው የአትክልት ዋጋ ከሚታመነው በላይ ሆኗል። ይህን ሁሉ አቻችሎ በጉልት ችርቻሮ ትርፍ ይዞ መግባት ፣ የልጆችን ጉሮሮ መዝጋት በእጅጉ አዳጋች እየሆነ ነው።

ሙሪዳ በዚህ ሁሉ ልፋት የገዛችውን አሸክማና በታክሲ አስጭና ለማምጣትም በብዙ ችግርና ፈተናዎች ማለፍ ይኖርባታል። ችግሩ ግን እንዲህ መሆኑ ብቻ አይደለም ። አትክልቱን በታክሲ ይዛ ካለችበት ለማድረስ ከጉልበት ድካሟ በላይ ባለታክሲዎች በየጊዜው የሚጭኑባት ዋጋ የእጇን አቅም እያራገፈው ነው።

ሙሪዳ ዛሬ ባስጫነችበት ዓይነት ዋጋ ነገን ልሞክር ብትል ‹‹በጄ›› የሚላት የለም። በየቀኑ እንደየሰዉ ባህርይ የባለታክሲዎችና ረዳቶቻቸው የክፍያ ዋጋ ይለዋወጣል። እንደምንም ታግላ ከሰፈሯ የምታደርሰውን ሸክም አሁን ላይ በቅርብ አስቀምጣ በአደራ አልያም በክፍያ የምታቆይበት ቦታ የለም።

ቀድሞ ጓዟን የምታኖረው በየቀኑ ለሥራ ከምትውልበት የገበያ ስፍራ በአንዱ ነበር። ዛሬ ግን ፈጽሞ ይህን ለመሞከር አልተቻላትም። ከጥቂት ጊዜያት በፊት ከአካባቢው የፈረሱት በርካታ የገበያ ሱቆች የእሷን ህልውና ጭምር አናግተዋል። ይህ ክፉ አጋጣሚም ከታክሲ ጣራ የምታወርደውን የሞላ ማዳበሪያ በባጃጅ ፣ አልያም በሰው ትከሻ አገላብጣ ወደቤቷ እንድታደርስ አስገድዷታል።

**ኑሮን በፈተና ..**

ሙሪዳ በየጊዜው በድካም የምታመጣውን የአትክልት ማዳበሪያ ከቤቷ አድርሳ መልሳ ወደገበያ ማመላለስ ይጠበቅባታል። ይህ ዓይነቱ የየዕለት ልማድ ደግሞ አሁን ላይ የጤና ችግር እያስከተለባት ነው። ብዙ ጊዜ ወገቧን ያማታል።ራስ ምታት ይፈትናታል። ባስ ባለ ጊዜም ለቀናት በቤቷ ተኝታ ትከርማለች። ይህኔ ለሽያጭ ያመጣቻቸው አትክልቶች ለመበላሸት አይዘገዩም።

ሙሪዳ ህመም ቢጠናባትም። ለራሷ ፊት አትሰጥም። እንደምንም ወገቧን አስራ፣ ጥርሷን ነክሳ ወደሥራዋ ትመለሳለች። አንዳንዴ ምርር ባላት ጊዜ ሁሉን ትታ፣ ቤተሰቦቿን ይዛ ሀገር ቤት ልትገባ ታስባለች። መልሳ ደግሞ ሀሳቧን እርግፍ አድርጋ ከራሷ ትመክራለች። እሷና ባሏ ከገጠር አዲስ አበባ ሲመጡ ራሳቸውን ለመለወጥ፣ ሕይወታቸውን ለማሻሻል ነው። ከእነሱ በፊትም ሆነ በኋላ በርካቶች ከቀያቸው ወጥተው ያሰቡትን ሞልተዋል። ሙሪዳ ይህ ሲገባት ተስፋዋን ታለመልማለች፣ ነገ የተሻለ እንደሚሆን ታልማለች።

የዘንድሮው ክረምት ለሙሪዳና መሰሎቿ የፈተና ጊዜ ሆኗል። እንደአምና ካቻምናው የያዙትን የጉልት አትክልት እንዳሻቸው አይሸጡም። የገበያዎቹ መፍረስ፣ የአካባቢው መለወጥ መድረሻ አሳጥቷቸዋል። የያዙትን ይዘው ከአስፓልቱ ብቅ ሲሉ ቆመጥ የያዙ ደንቦች ፈጥነው ይደርሱባቸዋል። አንዳንዶቹ ጓዛቸውን ጣጥለው ‹‹እግሬ አውጭኝ›› ይላሉ።

የአካባቢው ደንብ አስከባሪዎች በእጃቸው የገባውን ማንኛውንም ነገር አይምሩም። የቻሉትን ሁሉ ተሸክመው ይወስዳሉ። የተቀረውን በእግራቸው እየበተኑ፣ እየረገጡ ያባክኑታል። በዚህ ጊዜ እነሱን ለምኖ ተለማምጦ የሚቀናው አይኖርም።

ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ የብዙዎችን ጉልት ቸርቻሪዎች አንገት ያስደፋል። በ‹‹ሞላ ጎደለ›› የሚመሩትን ሕይወት ያጨልማል። ሙሪዳ ከዝናቡ ተጋፍታ፣ ከፀሐይዋ ተለማምጣ ከአንዱ ጥግ ስትቀመጥ ዓይንና ልቧ አያርፍም። የሚገዟትን መንገደኞች ትቃኛለች። የደንቦችን ኮቴ ታደምጣለች። ድንገት ቢመጡባት የቱን ይዛ ፣ የቱን እንደምትለቅ ታስባለች።

**በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ...**

ሙሪዳና ቤተሰቦቿ የቤት ተከራዮች ናቸው። በቅርቡ ደግሞ ዓመታትን ከኖሩበት መኖሪያ ለመልቀቅ ተገደዋል። አከራዮቹ በየጊዜው የሚጭኑባቸው ኪራይ በእነሱ አቅም የሚቻል አልሆነም። በቅርቡ ከተከሰተው የቤቶች መፍረስ ጋር የተከራዮች አካባቢውን መያዝ በቀደሙት ተከራዮች ላይ ከባድ ጫና አሳርፏል።

አሁንም ሙሪዳ ባለችበት ቤት ምቾት እየተሰማት አይደለም። ዓመታትን ከኖረችበት አንድ ክፍል ወደ ሌላ ጠባብ ክፍል የዞረችው በቅርቡ ነው። ይህን ማድረጓ የኪራይ ጭማሪውን መቋቋም ባለመቻሏ ነበር። አሁንም ግን ከመስከረም ጀምሮ ጨምሪ የተባለችው አንድ ሺህ ብር ዕንቅልፍ ነስቷታል። ቀን መሽቶ ቀን በመጣ ቁጥር በሀሳብ ትዋጣለች።

ጠንካራዋ ሳቂታዋ ሙሪዳ ዘንድሮ የተከፋችበት ጉዳይ እስክትነግረኝ ምክንያቱን ሳላውቅ ቆየሁ። ሁሉን ከተረዳሁ ከገባኝ በኋላም ከልቤ አዘንኩ።ይህ ዓይነቱ ስሜት በእርግጠኝነት የእኔ ብቻ አይሆንም። በየስፍራው ራሳቸውን ለማሸነፍ፣ ኑሯቸውን ታግለው ለመጣል የሚጥሩ ነፍሶች የኑሮ ውድነቱ እንደበዛባቸው የአደባባይ ምስጢር ነው።

**እንደ መልዕክት...**

ሙሪዳን የመሰሉ የሚሠሩ እጆች፣ ለትጋት የሚሮጡ እግሮች ያሏቸው ትጉዎች ከፍጥነታቸው እንዳይገቱ ፣ ከሕይወታቸው እንዳይታጎሉ ያሻል። አዎ! ነገ ሳይሆን ዛሬ የትኩረት ዓይኖች ይመልከቷቸው ፣ መልካም ልቦናዎች ከልብ ይጎብኟቸው እንላለን።


## በድጋሚ የወጣ የግንባታ ጨረታ ማስታወቂያ
## የግዥ መለያ ቁጥር 006/2015

የከምባታ ጠምባሮ ዞን ፋይናንስ መምሪያ የዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት በ2016 በጀት ዓመት የሴቴናል ኮለኔል ተከተል ወዴቦ መታሰቢያ ሀውልት ግንባታ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለማስገንባት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም፡-

1. ደረጃቸው BC/GC-7 እና ከዚያ በላይ የሆኑ
2. የዘመኑን ፈቃዳቸውን ያሳደሱ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡና የታክስ መለያ ቁጥር ያላቸው፣
3. በዘርፉ የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የምትችሉ፣
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ/ 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
5. ተጫራቾች ለሥራው የተዘጋጀውን ጨረታ ሠነድ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ21 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 300/ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል ዘወትር በሥራ ቀናት በፋይናንስ መምሪያ ቢሮ ቁጥር 15 ቀርበው መውሰድ ይቻላል፡፡
6. የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን ቴክኒካልና ፋይናንሻል አንዳንድ ኦርጅናልና ሁለት ኮፒ በማሸግና በአንድ ኤንቨሎፕ ውስጥ በማድረግ ጨረታው በወጣበት በ22ኛው ቀን ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ እስከ 8፡30 ሰዓት ማስገባት አለባቸው፡፡ ነገር ግን 22ኛው ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ በቀጣይ የሥራ ቀን ይከፈታል፡፡ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 8፡30 ሰዓት ታሽጎ 8፡45 ሰዓት ይከፈታል፡፡ መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ወይም ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ፡- 0465541393/0019/0360 ዱራሜ፣

**በደቡብ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ የከምባታ ጠምባሮ ዞን ፋይናንስ መምሪያ የግዥና ን/አስ/ር ዳይሬክቶሬት**

## የቤት ኪራይ የጨረታ ማስታወቂያ

በመንግስት ሰራተኛ ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር በጋምቤላ ቅ/ጽ/ቤት ከዚህ በታች መስፈርቶችን የሚያሟላ ለቢሮ አገልግሎት አከራዩች አወዳድሮ ለ3 አመት ለመከራት ይፈልጋል፤

**በዚህም መሰረት፤**

1/የባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ፕላን ያለው

2/ቤቱ ይዞታ ለቢሮ አገልግሎት አቺ የሆነ ደረጃውን የጠበቀ

3/ሁለት ክፍሎች ቢያንስ 5X7 የሆነና ተጨማሪ (አንድ ክፍል 5X5) የሆነ

4/የጽ/ቤቱ ሀላፊ ቢሮ 4X3 ሆኖ በአመቺ ሁኔታ የተሰራ

5/ሌሎች 5 የስራ ክፍሎች እያንዳንዳቸው 4X3 ስፋት ያለው

6/የጥበቃ ቤት ያለውና ከመንገድ ያልራቀ

7/የተሟላ ፅዳጀ ቤት፤ውሀና መብራት ያለው እንዲሁም ከመኪና አስፓልት ያልራቀ ሆኖ በወሩ የሚከራይበት ዋጋ እና የአመቱን ዋጋ በመግለጽ በተራ ቁጥር የተገለጸውን ማስታወቂያ ማስረጃ እና ግብር ከፋይነት (Tin Number ) በማያያዝ በታሸገ ፖስታ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር በደቡብ ምእራብ ሪጅን ጋምቤላ ቅ/ጽ/ቤት ቀርበው በማስገባት እንዲወዳደሩ ተጋብዘዋል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በጨረታው አይገደድም ተጫራቾች የቢሮ ኪራይ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ከጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቀርባችሁ መውሰድ ትችላላችሁ፡፡

ለጡረተኞች ምቹ የሆነና የሚያቀርቡት ዋጋ VAT እና TOT ማካተት ወይም ያለማካተት በመግለጽ በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር በደቡብ ምእራብ ሪጅን ጋምቤላ ቅ/ጽ/ቤት መቅረብ አለበት፡፡

**የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የደቡብ ምዕራብ ሪጂን ጋምቤላ ቅ/ጽ/ቤት**

# ስፖርት





## አዲስ አበባ ስታዲየም ከ2 ዓመት በኋላ ውድድር ያስተናግዳል

ብርሃን ፈይሳ

አዲስ አበባ ከተማ ለዘመናት የኢትዮጵያ ስፖርት ማዕከል በመሆን ዘልቃለች፡፡ የሀገሪቱን ስፖርተኞች በከተማዋ እንደ ማግኔት እየሳበ የዘለቀው ስፍራ ደግሞ አዲስ አበባ ስታዲየም ነው፡፡ በእርግጥ የስፖርት ቤተሰቡም ስለ ስፖርት ፍቅር ሲል ከዚህ ስፍራ ሳይርቅ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ አንጋፋው ስታዲየም ስፖርትን ብቻም ሳይሆን በርካታ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁነቶችንም ሲያስተናግድ የቆየ ስፍራ ነው፡፡

የእግር ኳስ ስፖርትን ለረጅም ዓመታት ተሸክሟል፤ አፍሪካ ዋንጫንና ሌሎች አህጉር አቀፍ ውድድሮችን ከማስተናገድ አንስቶ የፕሪሚየር ሊጉ እና የበርካታ ውድድሮች ጅማሬ ይኸው ስታዲየም ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንን ጨምሮ ክለቦች ለአሸናፊነት የሚያደርጉትን ትንቅንቅ ያሳዩበት፣ አንጋፋ ተጫዋቾች ተሸኝተው አዳዲስ ትውልዶች የሚተኩበትም ነው፡፡ ድል የቀናቸው ፈንድቀው የተረቱ ያነቡበት፤ ደማቅና አስደማሚ የቡድን ድጋፍ የለመደ ስታዲየምም ነበር፡፡ እርግጥ ነው አስጊ የስፖርታዊ ጨዋነት ችግሮችም በየጊዜው መስተዋላቸው አይዘነጋም፡፡

በአትሌቲክስ ስፖርትም ቢሆን ከጀማሪ አንስቶ ኢትዮጵያን እስካስጠሩ አትሌቶች ድረስ አቅማቸውን የፈተሹበት ስታዲየም ነው፡፡ ከታዳጊ እስከ አዋቂ በስፖርት ፍቅር የተነደፉ የከተማዋ ነዋሪዎች የተመላለሱበት ስታዲየምም ነው፡፡ አሁን ግን ይህ ሁሉ ለአዲስ አበባ የስፖርት ቤተሰብ ትዝታ ነው፡፡ ምክንያቱም በከተማዋ ብሔራዊ ቡድኑን ከተመለከተ፣ ክለቡን ከደገፈ እንዲሁም ሀገር በበጎ ያስጠራውን የአትሌቲክስ ውድድር ካጣጣመ ሁለት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የተለመደው ድምቀትና ለዛ ያለው ድጋፍም ደብዘዝ ማለቱ፤ ደጋፊውም አብዛኛውን ጨዋታ በቴሌቪዥን መስኮት መመልከቱ አልቀረም፡፡ የእግር ኳስም ሆነ የአትሌቲክስ እንዲሁም በሌሎች ስፖርቶች የሚከናወኑ ውድድሮችም አማራጮችን ለማማተር ተገደዋል፡፡



**የስታዲየሙ ሁለተኛ ምዕራፍ እድሳት 65 በመቶ ተጠናቋል፣**

የኢትዮጵያ ስፖርት መናኸሪያ የሆነው ይህ ታሪካዊ ስታዲየም ከስፖርት ወዳዱ ሕዝብ ሊለያይ የቻለው በጥገና ምክንያት ነው፡፡ በተጫጫነው እርጅና እንዲሁም በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) መስፈርትን ባለማሟላቱ ወደ ጥገና የተገባ ቢሆንም፤ በአንድ ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል የሚል ተስፋም ተጥሎበት ነበር፡፡ ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ጊዜው ተራዝሞ የተነፋፈቁት ውድድሮችና የስፖርቱ ቤተሰቡ ዳግም የመዋሃድ ተስፋን ያገኙት ከሰሞኑ ነው፡፡ ስፖርቱን በመምራት ላይ የሚገኘውና የስታዲየሙ ባለቤት የሆነው የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በመጪው ዓመት 2016 ዓ.ም መጀመሪያ የስታዲየሙ ጥገና ተጠናቆ የቤትኪንግ ኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግን ለማስተናገድ ዝግጁ እንደሚሆን አስታውቋል፡፡

ለመገናኛ ብዙኃን በተዘጋጀው የጉብኝት መርሃ ግብር በርካታ ሥራዎች መከናወናቸው የተስተዋለ ሲሆን፤ እድሳቱን አስመልክቶም ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሜዳ ፈሳሽ ማስወገጃና የሳር ተከላ ሥራ፣ የተጫዋቾች መልበሻ ክፍሎችን ጨምሮ የተለያዩ ግልጋሎት የሚሰጡ ክፍሎች፣ የካፍ ቢሮ፣ የሚዲያ ክፍልና የVIP ላውንጅ ሥራዎች፣ የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የውስጥ አጥርና የተመልካች መተላለፊያ መንገድ፣ … ሥራዎች በመገባደድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ወቅትም 22ሺ የሚሆኑ የስታዲየሙ ወንበሮች በመገጠም ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህንን ተከትሎም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጄላ መርዳሳ፤ ግንባታው የተጀመረው ጥገና ለማድረግ ቢሆንም ስታዲየሙ በእርጅና ምክንያት በመጎዳቱ እድሳት እየተደረገለት በመሆኑ ረጅም ጊዜ እንደወሰደ ይጠቁማሉ፡፡ የእድሳቱ ሁለተኛ ምዕራፍ ሥራም 65 ከመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ደረጃውን በጠበቀ መልክ እንዲጠናቀቅ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ቀሪዎቹ ሥራዎችም በመጪዎቹ ወራት ተጠናቀው በአዲሱ ዓመት ፕሪሚየር ሊጉን ለማካሄድ ዝግጁ ይሆናሉ ሲሉ አረጋግጠዋል፡፡

ቀሪው ሥራ የመም እድሳት ሲሆን፤ ለዚህም የሚሆነውን በጀት በእቅድ ተይዞ ለአትሌቶች ዝግጁ ይሆናል፡፡ የቪአይፒ ወንበሮች ገጠማ፣ በማታ ጨዋታዎችን ለማከናወን የሚረዳ መብራት፣ የስክሪን እና የጄኔሬተር ገጠማ፣… በቀጣይም የመኪና ማቆሚያን ጨምሮ በስታዲየሙ ዙሪያ ያሉ ሥራዎች የሚከናወኑ እንዲሁም ጥራቱን በሚመለከት የካፍ ባለሙያዎች የሚታይ እንደሚሆንም ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡